# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

81ኛ ዓመት ቁጥር 209 መጋቢት 29 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# በርዕሰ መስተዳድሩ የሰላሳ ቀን ዕቅድ መሰረት በሸኔ ታጣቂዎች ላይ የተቀናጀና ጠንካራ እርምጃ እየተወሰደ ነው

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የክልሉን ሰላም በማስፈን ወደ መደበኛ እንቅስቃሴ ለመመለስ በኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር የሰላሳ ቀን ዕቅድ መሰረት በሸኔ ታጣቂዎች ላይ የተቀናጀና ጠንካራ እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል የፀጥታና አስተዳደር ምክትል ቢሮ ኃላፊ ኮሎኔል አበበ ገረሱ አስታወቁ፡፡

ኮሎኔል አበበ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ ሰሞኑን በጨፌ ጉባዔ ላይ ሽብር ቡድኑን በአንድ ወር ውስጥ አደብ ለማስገዛት ጠንካራ እርምጃ እንዲወሰድ ባስቀመጡት አቅጣጫ መሰረት በክልሉ አራት ወሳኝ አካባቢዎች ላይ ጠንካራና የተቀናጀ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል፡፡

እንደ ምክትል ቢሮው ኃላፊ ገለጻ፤ ሽብር ቡድኑ በስፋት በመንቀሳቀስ በንጹሃን ዜጎች ላይ ሞትና በደል ያደረሰባቸው በወለጋ፣ በጉጂ፣ በምዕራብና ሰሜን ሸዋ አካባቢዎች በአሁኑ ጊዜ የክልሉና የፌዴራል የፀጥታ አካላት በሽብር ቡድኑ ላይ የተቀናጀ እርምጃ እየወሰዱ ይገኛሉ፡፡

በተጀመረው ኦፕሬሽን በርካታ የሽብር ቡድኑ አባላት ተደምስሰዋል፡፡ የተመዘገቡ ድሎች በዝርዝር ለህዝብ ይፋ ይደረጋሉ፡፡

ሸኔ ከአሸባሪው ህወሓት ጋር በመሆን ኦሮሚያን የብጥብጥ ቀጠና በማድረግ አገር ለማፍረስ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ የተናገሩት ኮሎኔል አበበ፤ ኦሮሚያ ብሎም ኢትዮጵያን ማፍረስ ከምናባዊ እሳቤና ከቀን ቅዥት ስሌት በዘለለ መቼም ቢሆን ሊሳካ የማይችል

በርዕሰ መስተዳድሩ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል



ኮሎኔል አበበ ገረሱ



## «የዋጋ ንረትን በዘላቂነት ለመግታት የአገሪቱን ማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መፈተሽ ያስፈልጋል»

- አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ

ገጽ 4



ፎቶ ፡- ሀዱሽ አብርሃ

# «በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የልማት ፕሮጀክቶችን በአግባቡ መምራት የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል»

- ዶክተር ፍጹም አሰፋ
የፕላንና ልማት ሚኒስትር

**ዘላለም ግዛው**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የልማት ፕሮጀክቶች አስተዳደር ዙሪያ የሚስተዋለውን የሐብት ብክነት በአግባቡ መምራት፣ ማስተዳደርና በተለዩበት የትኩረት መስክ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል አሰራር እየተዘረጋ መሆኑን የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ ገለጹ።

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የልማት ፕሮጀክቶች አስተዳደር ዙሪያ በሚመክረው ውይይት ላይ የተገኙት ዶክተር ፍጹም እንደገለጹት፤ ተቋማቱ በፕሮጀክቶች አስተዳደር ዙሪያ የሚስተዋለውን የሐብት ብክነት በአግባቡ መምራት፣ ማስተዳደርና በተለዩበት የትኩረት መስክ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል አሰራር እየተዘረጋ ይገኛል።

የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለትምህርት መስፋፋት ባለፉት ዓመታት የላቀ ድርሻ ቢኖራቸውም፤ ኢንቨስትመንቱ የተመራበት አግባብ ላይ ከፍተኛ ክፍተት መታየቱን አመልክተዋል። የፕላንና ልማት ሚኒስቴር፤ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የልማት አመራር ፕሮጀክት የሚያግዝ ልዩ የመንግሥት ኢንቨስትመንት ረቂቅ መመሪያ መዘጋጀቱን ጠቁመዋል።

የተጠኑ ጥናቶች እንደሚያመለክቱትም ባለፉት ዓመታት የተገነቡ ዩኒቨርሲቲዎች የመሰረተ ልማት ጥናት ችግር እንዳለባቸው፣ የተገነቡትም በአግባቡ

«በከፍተኛ የትምህርት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







ዜና



አቶ ተስፋዬ በልጅጌ

# የኅብረተሰቡ ጥያቄዎች መፍትሔ እንዲያገኙ ሁሉም ጥረት ማድረግ እንዳለበት የምክር ቤት አባላት አሳሰቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኅብረተሰቡ ጥያቄዎች መፍትሔ እንዲያገኙ ሁሉም ጥረት ማድረግ እንዳለበት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት አሳሰቡ።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር ሰሞኑን ያካሄዱትን ውይይት አስመልክተው በሰጡት ሐሳብ ከኅብረተሰቡ የተነሱትን ጥያቄዎችን መፍትሔ ለመስጠት ሁሉም ባለድርሻ አካላት ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበዋል።

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ሰሞኑን በየምርጫ ክልላቸው ተገኝተው ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር በአንገብጋቢ እና ወሳኝ ወቅታዊ ጉዳዮች ከተወያዩ በኋላ ሪፖርታቸውን የጋራ ለማድረግ መክረዋል።

የምክር ቤት አባላቱ በየምርጫ ክልላቸው የሚገኘው ሕዝብ ሐሳቡን በነጻነት እንዲያነሳላቸው ገልጸው ከየማኅበረሰቡ የተነሱትን ጥያቄዎች በየደረጃው ካሉ አስፈጻሚ አካላት ጋር በመነጋገር ግብረ-መልስ ጭምር እየሰጡ መምጣታቸውን አስረድተዋል።

ሕዝቡ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረት እየጨመረ መምጣቱን፣ የተጀመሩ የመሠረተ-ልማት ፕሮጀክቶች በጊዜ አለመጠናቀቃቸውን፣ በየአካባቢው የሚነሱ የልማት ጥያቄዎች መኖራቸውን፤ የመብራት፣ የውሃና የቴሌኮሙኒኬሽን እንዲሁም የመድኃኒት አቅርቦት ተደራሽነት ችግር መኖሩን መገለጹን አስረድተዋል።

በአንዳንድ አካባቢዎች ስንዴን በመስኖ ለማምረት የማዳበሪያ፣ የነዳጅ እጥረት እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች መኖራቸውን እንደጠቆማቸው ተናግረዋል።

የምክር ቤት አባላቱ ከሕዝቡ የሚነሱ ጥያቄዎች እንደከዚህ ቀደሙ በማወያየት ብቻ ይቀራል የሚል ጥርጣሬ ስላለ ሪፖርቱን በማጠናከር በየደረጃው ላሉ አስፈጻሚ አካላት በመላክ ክትትል እና ቁጥጥራቸው ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ በልጅጌ እንዳሉት የምክር ቤቱ አባላት ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር በሰላምና ጸጥታ ጉዳይ፣ በዋጋ ግሽበትና በኑሮ ውድነት፣ በመልካም አስተዳደር ፣ በመሠረተ-ልማት እና በአጠቃላይ የልማት ጉዳዮች ላይ በየምርጫ ክልላቸው መክረዋል።

አቶ ተስፋዬ ከሕዝቡ የተነሱት ጥያቄዎች በመንግሥት ብቻ የሚመለሱ እንዳልሁኑ ጠቁመው፤ በሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ መፍትሔ ሊመጣ እንደሚችል አመላክተዋል።

"የሕዝቡን ጥያቄዎች መንግሥት አይፈታቸውም" የሚለውን ጥርጣሬ ለማስወገድ የምክር ቤት አባላት የክትትል እና ቁጥጥር ሥራቸውን አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ነው አቶ ተስፋዬ ያስገነዘቡት።

በኅብረተሰቡ የተነሱትን የመልካም አስተዳደር ችግሮች፤ የመብራት፣ የውሃ እና የቴሌኮሙኒኬሽን ተደራሽነትን፣ የኑሮ ውድነትን፣ የመድኃኒት አቅርቦት ችግርን፣ የማዳበሪያ ዋጋ መጨመር እና ሌሎችንም ጥያቄዎች ለመመለስ መንግሥት የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደ መሆኑንም ዋና የመንግሥት ተጠሪው ገልጸዋል።

የኑሮ ውድነት የተፈጠረው በዓለም-አቀፍ ክስተቶች ማለትም በአቅርቦት እና ፍላጎት አለመመጣጠን ቢሆንም፣ እንደ ስንዴና ዘይት የመሳሰሉትን የምግብ ሸቀጦች እጥረት ለመፍታት መንግሥት ከውጭ ገዝቶ እያስገባ ስለሆነ ችግሩ እንደሚቃለል እምነታቸው እንደሆነ ተናግረዋል።

የማኅበረሰቡን ጥያቄዎች በቀጣይነት ለመመለስም ምክር ቤቱ እቅድ አውጥቶ መሥራት እንዳለበት ጠቁመው፣ ለምላሹ ግን ሁሉም ባለድርሻ አካላት መረባረብ እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

# ከሦስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ከጅቡቲ ወደ ሀገር ውስጥ ማጓጓዙን ኮርፖሬሽኑ ገለጸ

**በኃይሉ አበራ**



አዲስ አበባ፡- የ2014/15 ዓ.ም የሰብል ዘመን የአፈር ማዳበሪያ እስከ መጋቢት 27 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ሦስት ሚሊዮን 186 ሺህ 995 ኩንታል ከጅቡቲ ወደ ሀገር ውስጥ መጓጓዙን የኢትዮጵያ ግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ኢግሥኮ) አስታወቀ።

በኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን የኮሙኒኬሽን ኃላፊ አቶ ጋሻው አይችሉህም ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት፤ እስከ መጋቢት 20 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ጅቡቲ ወደብ የደረሰ የአፈር ማዳበሪያ ኤን ፒ ኤስ እና ኤን ፒ ኤስ ቢ መጠን 372 ሺህ 403 ሜትሪክ ቶን ወይም ሦስት ሚሊዮን 724 ሺህ 30 ኩንታል ነው።

ጅቡቲ ወደብ ከደረሰው የአፈር ማዳበሪያ ውስጥ እስከ መጋቢት 27 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ሦስት ሚሊዮን 186 ሺህ 995 ኩንታል ወደ ሀገር ውስጥ ተጓጉዞ በየክልሉ ለሚገኙ ዩኒየኖች እየተሰራጨ መሆኑን አመላክተዋል።

እስከ መጋቢት 29 ቀን 2014 ዓ.ም 58 ሺህ 12 ሜትሪክ ቶን ወይም 580 ሺህ 120 ኩንታል የጫነች መርከብ ጅቡቲ ወደብ ትደርሳለች ተብሎ እንደሚጠበቅም ጠቁመዋል። እንዲሁም ሚያዝያ 1 ቀን 2014 ዓ.ም 60 ሺህ ሜትሪክ ቶን ወይም 600 ሺህ ኩንታል የጫነች መርከብ ጅቡቲ ወደብ ትደርሳለች ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

እንደ አቶ ጋሻው ገለጻ፤ የ2014/15 ዓ.ም የሰብል ዘመን የአፈር ማዳበሪያዎቹ በየቀኑ ወደ ሀገር ውስጥ እየተጓጓዙ ሲሆን በዩኒየኖች አማካኝነት ለአርሶ አደሮች እየተሰራጨ ይገኛል። ጅቡቲ ወደብ ከደረሰው የአፈር ማዳበሪያ በየቀኑ በአማካይ ከ70 ሺህ ኩንታል በላይ በከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎችና በእቃ ማጓጓዣ ባቡር ጭምር እየተጓጓዘ ነው ብለዋል። የአፈር ማዳበሪያውን ከጅቡቲ ወደብ ወደ ክልሎች በማጓጓዝ ለዩኒየኖች የሚያስረክበው የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት (ኢባትሎአድ) መሆኑን ገልጸዋል።

በተመሳሳይም ኮርፖሬሽኑ የግብርና ምርትን የሚያሳድጉ ምርጥ ዘር፣ የአፈር ማዳበሪያና አግሮ ኬሚካሎችን ለአርሶና አርብቶ አደሩ እንዲሁም በእርሻ ልማት ለተሰማሩ ባለሃብቶች በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች ባቋቋማቸው የግብርና ግብዓት መሸጫ ጣቢያዎች እያቀረበ መሆኑን አስታውሰዋል።

ግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ለምርት ዘመኑ የሚያስፈልግ አግሮ ኬሚካሎች ማለትም ጸረ አረም፣ ጸረ ሰብል በሽታ፣ ጸረ ተባይና ጸረ የመጋዘን ነፍሳት በቂ ክምችት እንዳለው አመላክተዋል።

ለ2014/15 ዓ.ም የምርት ዘመን የብርዕና የአገዳ ሰብሎች እንዲሁም ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ቦለቄ የመሳሰሉ ጥራጥሬዎች ምርጥ ዘር ለተጠቃሚዎች እያሰራጨ መሆኑን ጠቁመዋል። በምርት ዘመኑ 200 ሺህ ኩንታል ምርጥ ዘር ለማሰራጨት እየሠራ ነው ያሉ ሲሆን እስከ መጋቢት 21 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ 48 ሺህ 247 ኩንታል የምርጥ ዘር ለተጠቃሚዎች መሰራጨቱንም አመላክተዋል።

# ባንኮቹ ተወዳዳሪ ሆነው ለመሥራት ዝግጅት እያደረጉ መሆናቸውን ገለፁ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት የውጭ ሀገራት ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው እንደሚሰሩ ማሳወቁን ተከትሎ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ እናት ባንክና አቢሲኒያ ባንክ በፋይናንሱ ዘርፍ ላይ ተወዳድረው ለመሥራት ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን ገለፁ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተጠባባቂ ኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አልሰን አሡፋ፤ ኢትዮጵያ በዘርፉ ራሷን ዘግታ የምትኖር ሀገር አይደለችም፤ ሌሎች ባንኮች ሀገር ውስጥ ገብተው እንደሚሠሩና በገበያ ውስጥ ውድድር እንደሚኖር ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በፅኑ ያምናል ብለዋል።

ለዚህም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመዝለቅ የእራሱን ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ንግድ ባንክ ከዚህ በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ የጣሊያንና የእንግሊዝ የመሳሰሉ የውጭ ባንኮች ገብተው እንዲሠሩ ተፈቅዶ በነበረበት ጊዜም ተወዳድሮ የሠራና ልምድ ያካበተ ባንክ ነው ያሉት አቶ አልሰን፤ መንግሥት የባንኮቹ መምጣት ይጠቅማል፣ ለሀገሪቷ ዕድገት ይበጃል ብሎ እስካመነ ድረስ ባንኩ ተወዳድሮ ለመሥራት ዝግጁ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ አልሰን ከሆነ፤ ባንኩ እስከ ቀበሌ ድረስ የዘለቁ በርካታ ቅርንጫፎች ያሉትና ከደንበኞቹ መካከል የዲጂታል ባንኪንግ የግብይት ተጠቃሚዎቹን ቁጥር እያሳደገ የመጣ ነው። በተጨማሪ ከ37 ሺህ በላይ በዘርፉ የሠለጠነ ቋሚ የሰው ኃይል ያለው ባንክ በመሆኑ ተወዳዳሪነቱ በግዙፍ አቅም የታጀበ ነው።

በተጨማሪም ሥርዓቱን ለማዘመን በትኩረት እየሠራ ይገኛል። ባንኩ ከአንድ ነጥብ አንድ ትሪሊየን በላይ ካፒታል ያለው ባንክ በመሆኑ በፋይናንሱ ዘርፍ ተወዳዳሪነት ላይ ያለስጋት ለመሥራት ያግዘዋል ብለዋል።

የእናት ባንክ የቅርንጫፎች ሥራ ማስተባበሪያና ሀብት ማሰባሰቢያ ዳይሬክተር ወይዘሮ በዓለምላይ አየነው በበኩላቸው በመንግሥት በኩል የተወሰነውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ ባንካቸው ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ገልፀዋል።

ከ60 በመቶ በላይ በሚሆኑ ሴት የአክሲዎን ባለድርሻዎች የተቋቋመው እናት ባንክ ከውጭ ባንኮች ጋር ተወዳዳሪ ሆኖ ለመሥራት የሚያስችለውን አመቺ ሥርዓት እየዘረጋ መሆኑን ተናግረዋል።

ዳይሬክተሯ አያይዘውም ከተመሰረተ ዘጠኝ ዓመት የሞላው ባንኩ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለመሆን የውስጥ አሠራርንና አቅም ከማጎልበት ባሻገር አገልግሎቶቹን ይበልጥ በቴክኖሎጂ ለማዘመንና ዝግጅት ላይ መሆኑን አስታውቀዋል።

የአቢሲኒያ ባንክ ብድር ፖርትፎሊዮ ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ ኃይሌ በበኩላቸው መንግሥት የሀገር ውስጥ ባንኮች ራሳቸውን አጠንክረውና አዘምነው ከውጭ ባንኮች ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ መሥራት እንደሚገባቸው መግለጹን ተከትሎ ባንካቸው የተጠናከረ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

ባንኩ ለዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ወሳኝ ናቸው በተባሉ ሦስት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይም በትኩረት እየሠሩ መሆኑን ተናግረዋል።

የባንኩን ካፒታል (ጠቅላላ ሀብት) ማሳደግ፣ ጠንካራ የሰው ኃብት ልማት ሥራ ማጎልበትና አዳዲስ እንዲሁም ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን መተግበር አቢሲኒያ ባንክ ለተወዳዳሪነቱ ሲል ያተኮረባቸው አንኳር ጉዳዮች መሆናቸውን አቶ ቴዎድሮስ አስታውቀዋል።

መንግሥት የሀገር ውስጥ ባንኮችን በፖሊሲና በመሳሰሉት ጉዳዮች ሊደግፍ እንደሚገባ ያስረዱት ዳይሬክተሩ፤ የውጭ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸው ለቴክኖሎጂና የዕውቀት ሽግግር ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ በተጨማሪ የቀጥታ ወጪ ንግድን ለመሳብና ለውጭ ምንዛሪ ግኝት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል።

# በርዕሰ መስተዳድሩ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሴረኞች ህልም ነው ብለዋል።

በቡድኑ ላይ እርምጃ እየተወሰዱ ባሉባቸው የሚገኙ የክልሉ ነዋሪዎች ከጸጥታ አካላት ጎን መሰለፋቸውን የጠቀሱት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ስንቅ በማቀበል፣ ጥቆማ በመስጠትና ቀጥታ እርምጃ በመውሰድ ህዝቡ እያደረገ ያለው ተሳትፎ የሚደነቅና ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት በጎ ተግባር መሆኑን አስገንዝበዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ የክልሉ መንግሥት ሽብተኝነትና ጽንፈኝነት ለክልሉም ሆነ ለአገር ህልውና አደገኛ መሆኑን በጽኑ ያምናል። በአሸባሪው ሸኔ ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ሲጠናቀቅ በሌሎች አካባቢዎች ያለውን የሰላም ችግር ለመፍታት በሚደረገው እንቅስቃሴ ክልሉ የበኩሉን ድርሻ እንደሚወጣም አስታውቀዋል።

በአንዳንድ ክልሎች የአገር ሰላምና የህዝቦች አንድነት አደጋ ላይ የሚጥሉ የሽብር ተግባርና አስተሳሰብ በስፋት እየተስዋለ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሌሎች ክልሎችም ሰላም ለማስፈን ጠንካራ እርምጃ እንደሚወስዱ ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።

የኦሮሞ ህዝብ ከሌሎች ወንድም ህዝቦች ጋር በመሆን አገር የመገንባት ታሪክ እንጂ ጽንፈኛና ሽብርተኛን የማስታመም ህልውና የለውም ያሉት ኮሎኔል አበበ፤ በሽብርተኛው ሸኔ ላይ የጀመረውን የማያዳግም እርምጃ በመሰሎቹ ላይም እንደሚወስድ አስታውቀዋል።

የሽብር ቡድኑ ታጣቂዎች በድርጊታቸው ተጸጽተው ወደ ሰላማዊ ኑሮ የመመለስ ፍላጎት ካላቸው የክልሉ መንግሥት የሰላም በሩአሁንም ክፍት መሆኑንም አመልክተዋል።

# ቡድኑ በሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ እያካሔደ ያለውን የጥናት ሂደት ለጋራ ግብረ ኃይሉ አቀረበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የምርመራና ጥናት ቡድኑ በአፋርና አማራ ክልሎች የተፈጸሙ ሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ እያካሔደ ያለውን የጥናት ሂደት ለሚኒስትሮች የጋራ ግብረ ኃይል አቀረበ።

ከፍትሕ ሚኒስቴር፣ ከፌዴራል ፖሊስና ከመከላከያ ሚኒስቴር የተዋቀረው የምርመራና ጥናት ቡድን በአፋርና አማራ ክልሎች የተፈጸሙ ሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ እያካሔደ ያለውን ጥናት ሂደት ትናንትና ለሚኒስትሮች የጋራ ግብረ ኃይል አቅርቧል።

የሚኒስትሮች የጋራ ግብረ ኃይል በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የተከሰተውን ግጭት ተከትሎ ተፈጽመዋል የተባሉ ወንጀሎችን አስመልክቶ እስካሁን የተካሄዱ የምርመራና የመልሶ ማቋቋም ሥራዎችን ገምግሟል።

በተለይም በጦርነቱ የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እና ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ገቢራዊነት ላይ በምርመራ ቡድኑ የቀረበለትን ሪፖርት ተመልክቷል።

የሰሜኑን ግጭት ተከትሎ በሶስቱም ክልሎች ማለትም በአማራ፣ አፋርና ትግራይ ክልሎች የተፈፀሙ ወንጀሎችን እንዲሁም የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች ምን እንደሚመስሉ ገምግሟል።

የምርመራና ጥናት ቡድኑ ሥራውን በጀመረባቸው በአማራና አፋር ክልሎች የተፈፀሙ ወንጀሎችን የማጣራትና ወንጀለኞቹን ለፍርድ የማቅረብ ሂደት ያለበት ደረጃ በዝርዝር ታይቷል።

እስካሁን ወንጀሎችና ወንጀሎቹ በማንና እንዴት ተፈፀሙ ከሚለው ጋር በተገናኘ በርካታ የአይን ምስክሮችን ለማነጋገር መቻሉን የምርመራ ቡድን አሳውቋል።

በቂ ማስረጃ በማሰባሰብ ወንጀለኞች ላይ ክስ ለመመስረት ሂደት መጀመሩ ተገልጿል። በሂደቱ የተገኙ ስኬቶችና ድክመቶችም ላይ ግምገማ ተደርጓል።

የተመድ የሰብዓዊ መብት ተቋምና የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ባደረጉት የጋራ ምርመራ የተሰጡትን ምክረ ሃሳቦችን ለመተግበር ኢትዮጵያ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ የሚኒስትሮች ግብረ ኃይል መቋቋሙ ይታወቃል።



## ‹‹ለአምስት ቀናት ታስረው የነበሩት እህል ጫኝ መኪናዎቻችን ከእስር ተለቀዋል››

**- ባለንብረቶች**

## ‹‹መኪናዎቹ ከእስር የተለቀቁት እህሉን ለህብረት ሥራ ማህበራት እንዲሸጡ በማድረግ ነው››

**- የአዲስ ከተማ ክፍል ከተማ አስተዳደር**

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ልዩ ስሙ እህል በረንዳ በሚባለው አካባቢ እህል ጫኝ መኪናዎቻችን ያለ አግባብ ታስረውብናል ብለው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ቅሬታቸውን ያቀረቡ ባለንብረቶች መኪናዎቻቸው ከአምስት ቀናት እስር በኋላ እንደተለቀቁላቸው ገለጹ። 60 እህል ጫኝ መኪናዎች ከእስር የተለቀቁት እህሉን ለህብረት ሥራ ማህበራት እንዲሸጡ በማድረግና ዳግም በህግ ወጥ ተግባር እንዳይሰማሩ መሳሰቢያ በመስጠት ጭምር መሆኑንም የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አስተዳደር አስታውቋል”

የመኪና ባለንብረቶቹ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍል ነጋዴዎች የላኩላቸውን እህል በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ልዩ ስሙ እህል በረንዳ በሚባለው አካባቢ በመጫን ሥራ ላይ ተሰማርተው እያለ ታስረው የነበሩት እህል ጫኝ መኪናዎቻቸው ተለቀውላቸዋል።

ባሳለፍነው ሳምንት ቅሬታቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸው የነበሩትና የእህል ጫኝ መኪና ባለንብረቶች ወኪል የሆኑት አቶ ወንድወሰን አያሌው እንደገለፁት፣ ያለ አግባብ ታስረው የነበሩት የእህል ጫኝ መኪናዎቻቸው ከእስር ተለቀውላቸዋል።

እህል ጫኝ መኪናዎቹ በመታሰራቸው ምክንያት የሥራ እንቅስቃሴያቸው እንደተስተጓጎለባቸው ገልጸው የነበሩት አቶ ወንድወሰን፤ አሁን መኪናዎቻቸው በመለቀቃቸው ወደ ቀድሞ እንቅስቃሴያቸው መመለሳቸውን ጠቁመዋል።

የዘመድ መኪና ታስሮበት ቅሬታውን አቅርቦ የነበረው አቶ ሞገስ ታምራት በበኩሉ እንደገለፀው፤ ያለ አግባብ ታስረው የነበሩት እህል ጫኝ መኪናዎቻቸው ከእስር ተለቀውላቸዋል።

ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለቅሬታው ምላሽ እንዲሰጡት ጥያቄ አቅርቦላቸው የነበረው የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የንግድ ክትትልና ቁጥጥር ባለሙያ አቶ ዋሲሁን አዱኛ በበኩላቸው እንደገለፁት፤ ከ60 በላይ እህል ጫኝ መኪናዎች ከእስር ተለቀው ለባለንብረቶቹ ተመልሰዋል።

እንደ አቶ ዋሲሁን ገለፃ፤ የታሰሩት መኪኖች ከእህል በረንዳው ቅጥር ውጭ የቆሙና የሽያጭ ፍቃዳቸውም ክፍለ ሀገር የነበረ ቢሆንም ክፍለ ከተማው አሁን ላይ ያለውን የዋጋ ንረት ለመቆጣጠር በማሰብ መኪናዎቹ የጫኑትን እህል ለህብረት ሥራ ማህበራት እንዲሸጡ በማድረግ ከእስር እንዲለቀቁ አድርጓል።

የእህል ጫኝ መኪናዎቹን ከታሰሩበት የለቀቅነው በማስጠንቀቂያ እንዲሁም ከዚህ በኋላ በመሰል ህገወጥ ተግባር ላይ እንዳይሳተፉ በማሳሰብ ጭምር መሆኑን የገለጹት አቶ ዋሲሁን፤ እህል ጫኝ መኪናዎችን ከእስር በመፍታት የጫኑትን እህል ለህብረት ሥራ ማህበራት እንዲሸጡ የማድረጉ እርምጃም ህጋዊ ሳይሆኑ ሥራውን አየር ባየር ለሚሰሩ ህገ ወጦችን አደብ የሚያስገዛ ተግባር መሆኑንም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት “እህል ጫኝ መኪናዎቻችን ያለ አግባብ ታስረውብናል” - ባለንብረቶች ‹‹መኪናዎችን ያሰርነው በወቅቱ መረጃ ማቅረብ ባለመቻላቸው ነው” - አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በሚል ርዕስ የባለንብረቶቹን ቅሬታ እንዲሁም የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማን ምላሽ ባሳለፍነው ዓርብ መጋቢት 23 ቀን 2014 ዓ.ም በዜና መልክ ማቅረቡ ይታወሳል።

## የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ጠቅላላ ጉባዔያቸውን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ማካሄዳቸውን ገለጹ

**- በብሔራዊ መግባባት ላይ የሚጠበቅባቸውን እንደሚያደርጉ ተናግረዋል**

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላላ ጉባዔያቸውን በዴሞክራሲያዊ መንገድ በማካሄድ ሥራ አስፈፃሚ አካላትንና የፓርቲዎቻቸውን መሪዎች መምረጣቸውን ህብር ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ እና የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ (ኢሶዴፓ) ገለጹ።

በብሔራዊ መግባባት ረገድም የሚጠበቅባቸውን ለማድረግ በየፓርቲዎቻቸው ጉባዔ ላይ መምከራቸውን ተናግረዋል።

ህብር ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ያካሄደውን አንደኛ መደበኛ ጉባዔ እና የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ (ኢሶዴፓ) ያካሄደውን አራተኛ መደበኛ ጉባዔን ተከትሎ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሁለቱንም ፓርቲዎች አነጋግሯል።

የህብር ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት እና የውጭ ግንኙነት ኃላፊ አቶ አበራ በቀለ ፓርቲያቸው አንደኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔውን መጋቢት 25 ቀን 2014 ዓ.ም ማካሄዱን ተናግረዋል።

አንደኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔውን “ዘላቂ ሠላም፣ ቀጣይና ፍትሃዊ ልማት፣ ሃቀኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ በአሣታፊና አካታች ብሔራዊ መግባባትና ሀገራዊ እርቅ” በሚል መሪ ሃሳብ መካሄዱን ገልጸዋል። በጉባዔው ውስጠ ደንቦችን የማረም፣ ሥራ አስፈጻሚዎችን የመምረጥ እና ቀጣይ አቅጣጫዎችን የማስቀመጥ ሥራዎች ተሠርተዋል ብለዋል።

ፓርቲው ባካሄደው ጉባዔ 25 ቋሚ እና አምስት ተጠባባቂ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን፤ አምስት የኦዲት እና ቁጥጥር ኮሚሽን አባላትን እና ዘጠኝ የሥራ አስፈፃሚ አካላት ተመርጠዋል ብለዋል።

በፓርቲው የሥራ አስፈፃሚ ምርጫ ውስጥ ጨምሮ አቶ ግርማ በቀለ የፓርቲው ሊቀመንበር፤ ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት ምክትል ሊቀመንበርና ጥናትና ስትራቴጂ ኃላፊ፤ አቶ አበራ በቀለ የሕዝብ ግንኙነትና የውጭ ጉዳይ ኃላፊ፤ አቶ ዳዊት ተማም የሕግና አባላት ጉዳይ ኃላፊ፤ ወይዘሪት ምዕራፍ ይመር አስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ እና አቶ ይድነቃቸው አዲስ የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ እንዲሁም አቶ ሽመልስ እንግዳ ዋና ፀሐፊ፣ አቶ ታምራት አሰፋ ምክትል ፀሐፊ እና ወይዘሮ እፀገነት ተስፋዬ የማህበራዊ ጉዳይ ኃላፊ ሆነው ተመርጠዋል።

በምርጫ ቦርድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ማቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ፓርቲው ማሟላት ያለበትን የጉባዔተኞች ቁጥር ቀደም ሲል ከነበረው 115 ወደ 615 አሳድጓል።

የማዕከላዊ ኮሚቴ አባሎችንም ከ45 ወደ 25 ቋሚና አምስት ተጠባባቂ ያወረደ ሲሆን፣ በአጠቃላይ 30 ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት እንዲኖረው ደንቡን አሻሽሎ ተግባራዊ ማድረጉን ኃላፊው ገልጸዋል። በተመሳሳይ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቁጥርም ለአሠራርና ለሥራዎች ቅልጥፍና እንዲመች ታስቦ ከ11 ወደ ዘጠኝ መቀነሱን ተናግረዋል።

የፓርቲው የቀጣይ የትግል ትኩረት አቅጣጫም በሀገሪቱ እውነተኛ የብሔራዊ መግባባት እና አገራዊ እርቅ ዕውን ለማድረግ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ መሥራት መሆኑን ገልጸዋል።

በተጨማሪም በጉባዔው ወጣቱ ላይ ትኩረት ያደረጉ ውይይቶች ተካሂደዋል። ወጣቶች ከአልባሌ ሥፍራ እንዲርቁና በአካልና በሥነ ልቦና የዳበሩ እንዲሆኑ ከዚህ ቀደም ከነበረው የህልውና አደጋ በመማር ከወትሮው የተለየ ዝግጁነት መደረግ እንዳለበት ሕብር ፓርቲ ያምናል ተብሏል።

በዚህም በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ንቁና ዝግጁ ለማድረግ ከ18 ዓመት ጀምሮ ወታደራዊ ሥልጠና ለወጣቱ እንዲሰጥ በፖለቲካ ፕሮግራማችን ላይ በተጨማሪነት አጽድቀናል ብለዋል ኃላፊው።

ህብር ፓርቲ ከፖለቲካ ሥልጣን ይልቅ የሀገርና የሕዝብ ህልውና ይቀድማል በማለት በብሔራዊ መግባባትና በብሔራዊ እርቅ ዙሪያ ከፍተኛ ሥራ መሥራት እንዳለበት ተነጋግሯል። ሀገር እንደ ሀገር ሕዝብም እንደ ሕዝብ መቀጠል የሚችለው ብሔራዊ መግባባትና ብሔራዊ እርቅ ሲከናወን ነው የሚል ፅኑ አቋም ላይም በፓርቲው ደረጃ ተደርሷል ብለዋል አቶ አበራ።

በቀጣይም በብሔራዊ መግባባትና ብሔራዊ እርቅ ሂደት ሲከናወን በቁርጠኝነት ለመሥራት አቅጣጫ ማስቀመጡን አቶ አበራ ገልጸዋል።

በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ ምክትል ሰብሳቢ (ኢሶዴፓ) ዶክተር ራሄል ባፌ ፓርቲው አራተኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉበዔውን መጋቢት 24 ቀን 2014 ዓ.ም እንዳካሄደ ገልጸዋል።

ጉባዔው በአዲሱ የምርጫ ቦርድ አዋጅ መሠረት ውስጠ ደንቡ ላይ የሚታረሙ ጉዳዮችን መርምሯል፤ የጠቅላላ ጉባዔውን ውሳኔ የሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ መክሮ የወሰነ ሲሆን የፓርቲውን አመራሮች፣ ሥራ አስፈጻሚዎች፣ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴዎችን እና የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን መርጧል ብለዋል።

በዚህም መሰረት የፓርቲው ሊቀመንበር ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣ ምክትል ሊቀመንበር ዶክተር ራሔል ባፌ፣ ፀሐፊ ሣራ መሐመድ እና ምክትል ፀሐፊ አቶ ተክሉ ሸዋ እንዲሁም ሌሎችን ያካተተ 11 የሥራ አስፈጻሚ አካላት ተመርጠዋል ብለዋል። ለማዕከላዊ ኮሚቴም 36 ሰዎች እንደተመረጡ ተናግረዋል።

አዲሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ማቋቋሚያና መተዳደሪያ አዋጅ መሠረት የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ቁጥር ወደ 500 ከፍ ማድረጋቸውንና ከዚህ ቀደም ፓርቲው በየአምስት ዓመት ለማካሄድ ወስኖት የነበረው መደበኛ ጉባዔ ከአዋጁ ጋር በተጣጣመ መንገድ በየሦስት ዓመት እንዲካሄድ ተወስኗል።

ምርጫውም ሆነ ጉባዔው በዴሞክራሲያዊ መንገድ መካሄዱን ምክትል ሊቀመንበሯ ተናግረዋል።

በጠቅላላ ጉባዔው ላይ ብሔራዊ መግባባትን በተመለከተ ውይይት እንደተደረገና አገር አቀፍ የብሔራዊ መግባባት ሂደቱን ስኬታማ ለማድረግ ፓርቲው የበኩሉን ለመወጣት ዝግጁ እንደሆነ ዶክተር ራሄል ገልጸዋል።

# ‹‹ለሃይማኖት መገናኛ ብዙሃን ፈቃድ መሰጠት መጀመሩ አገራዊ አንድነትን ለማጠናከር የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ያስችላል››

*-የሃይማኖት መገናኛ ብዙሃን የሥራ ኃላፊዎች*

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ለሃይማኖት መገናኛ ብዙሃን ፈቃድ መሰጠት መጀመሩ አገራዊ አንድነትን ለማጠናከር የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ያስችላል ሲሉ የሃይማኖት መገናኛ ብዙሃን የሥራ ኃላፊዎች ገለጹ።

ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተያየታቸውን የሰጡ የሃይማኖት መገናኛ ብዙሃን የሥራ ኃላፊዎች እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን ለሃይማኖት መገናኛ ብዙሃን ፍቃድ መስጠት መጀመሩ አገራዊ አንድነትን ለማጠናከር በሚደረገው ጥረት ውስጥ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ያስችላል ።

በኢትዮጵያውያን ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል የሚዲያና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ መሳይ አለማየሁ እንደገለጹት፤ የሃይማኖት መገናኛ ብዙሃን ፈቃድ እንዲያገኙ መደረጉ የሃይማኖት ተቋማት ለምዕመኖቻቸው የዕምነታቸውን አስተምሮ በሚገባ ለመግለጽ ያስችላቸዋል።

የሃይማኖት መገናኛ ብዙሃኑ በባለስልጣኑ ህግ እንዲመሩና ፈቃድ እንዲያገኙ መደረጉ አላማቸውን እንዳይስቱና በትክክለኛው መንገድ እንዲጓዙ ያደርጋል ያሉት አቶ መሳይ ፤በተለይም አንድ ዜጋ መልካም ስብዕና አስተሳሰብ እንዲኖረው ማድረግ የሚቻለው ዕምነቱን አጥብቆ እንዲይዝ ማድረግ ሲቻል መሆኑን ገልጸዋል።

ለአገራዊ ሰላምና መቻቻል፣ አንድነትንና ህብረትን ለማምጣት በሚደረገው ጥረት የሃይማኖት ብሮድካስት ትልቅ ሚና እንዳላቸው የገለጹት አቶ መሳይ ፤ በአንድ የመንግሥት ሚዲያ ውስጥ የመንግሥትን አቋም የሚናገረውን ያህል በአንድ የሃይማኖት ሚዲያ ደግሞ የሚከተሉትን እምነት ማንጸባረቅ መቻል አስፈላጊ መሆኑን አስገንዝበዋል።

የሃይማኖት መገናኛ ብዙሃን ትውልድን በመለወጥና በማነጽ ለአገር አንድነትና ብልጽግና ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ ሲሉ ገልጸዋል።

የሚንበር ቴሌቪዥን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አዩ ባለም በበኩላቸው ባለፉት ዓመታት የሃይማኖት የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ከፍተኛ ጫና ሲደርስባቸው ነበር። አሁን ላይ እንደማገኛውም መገናኛ ብዙሃን ፈቃድ ማግኘታቸው መልካም የሚባልና ባለስልጣን መስሪያ ቤቱን የሚያስመሰግነው ነው። መገናኛ ብዙሃኑ ማህበረሰብን በማረጋጋት፣ ግብረ ገብ ትውልድ እንዲፈጠር በማድረግ ደርሻቸው ከፍተኛ በመሆኑ እስካሁን ያልተጠቀምንባቸው ሀብቶች ናቸው ብለዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንዳሉት፤ ሁሉም ሃይማኖቶች ያሏቸውን እሴቶች ለተከታዮቻቸው በማስተማር፣ በስነ ምግባር እንዲታነጹ ማድረግ ይችላሉ። የሰው ልጅ በስነ ምግባር ሲታነጽ ለጠብ፣ ለጭቅጭቅ፣ አንዱ ሌላውን ለማሳነስና ለመግፋት የሚያባክነው ጊዜ አይኖርም። በንግግር፣ በምክንያታዊነት የሚያምን፣ሙስናን፣ በደልን የሚጸየፍ እኩልነትን የሚቀበል፤ ሰብዓዊነት የሚሰማው ማህበረሰብ ለመፍጠር የበኩላቸውን ሚና መወጣት ያስችላቸዋል።



መሳይ አለማየሁ



አዩ ባለም



መ/ር አቤል አሰፋ

የሚንበር ቴሌቪዥን በትኩረት ከሚሰራባቸው ስድስት የትኩረት ነጥቦቹ አንዱ አብሮነትና ሰላም ላይ በጋራ መስራት ነው ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ከየትኛውም የእምነት መገናኛ ብዙሃን ጋር በጋራ እንደሚሰሩ ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲን የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ድርጅት የዲጂታል ሚዲያ ዋና ክፍል ኃላፊ መምህር አቤል አሰፋ እንዳሉት፣ የሃይማኖት ብሮድካስት መመሪያ አለመውጣቱ መገናኛ ብዙሃኑ የውጭ ምንዛሪ እንዳያገኙና የሚዲያ ቴክኖሎጂ ግብዓትን ከውጭ አገር በቀላሉ ወደ አገር ውስጥ በማስገባት ለመንፈሳዊና ማህበራዊ አላማዎች እንዳይጠቀሙ አድርጎ ቆይቷል።

በመገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን ለሃይማኖት መገናኛ ብዙሃን ፈቃድ መስጠት መጀመሩ በመላ አገሪቱ እንደልብ ተንቀሳቅሶ ለመስራት የብሮድካስት አዋጅ የማስፈጸም ደንቡ ከለላና ሽፋን የሚሰጥ ነው።

እንደ አገር እየተከሰቱ ያሉ ችግሮችን ለማርገብ፣ አንድነትና ሰላም እንዲሰፍን፣ በሕዝቦች መካከል መከባበር፣ መፈቃቀር፣ እንዲኖር ግጭቶች እንዲቆሙ፣ የሃይማኖት መገናኛ ብዙሃን ሚናቸውን እንዲወጡ የሚያስችል እንደሆነም መምህር አቤል ገልጸዋል።

# ‹‹የዋጋ ንረትን በዘላቂነት ለመግታት የአገሪቱን ማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መፈተሽ ያስፈልጋል››

**- አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ**

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- እየጨመረ የመጣውን የዋጋ ንረትን በዘላቂነት ለመግታትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቅረፍ የአገሪቱን ማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ፈትሾ ማስተካከል እንደሚያስፈልግ የኢኮኖሚ ምሁሩ አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ ገለጹ። ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ባለባት አገር 25 ሚሊዮን የሚያወጡ መኪናዎችንና ውድ ሸቀጦች ወደ አገር ቤት እንዲገቡ መፍቀድ ተገቢ አለመሆኑን ገልጸዋል።

አቶ ዘመዴነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ የተስተዋለው የዋጋንረት ኢትዮጵያን በእጅጉ ጎድቷታል። እየጨመረ የመጣውን ዋጋ ንረትን በዘላቂነት ለመግታትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቅረፍ የአገሪቱን ማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ፈትሾ ማስተካከል ያስፈልጋል።

በአገሪቱ እየተስተዋለ ያለው የምግብ ሸቀጦች ዋጋ ጭማሪ ህብረተሰቡን ጫና ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል ያሉት አቶ ዘመዴነህ፤ የዓለም የተከሰተውን የዋጋ ንረት ተከትሎ በኢትዮጵያ የሚስተዋለውን ከፍተኛ ዋጋ ጭማሪ በዘላቂነት ለመግታትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቅረፍ የአገሪቱን ማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ፈትሾ ማስተካከል ያስፈልጋል ብለዋል።

በዓለም ላይ የሸቀጦች የዋጋ ንረት በቀጣዩ ወራቶች የመጨመር አዝማሚያ እንደሚኖረው አመልክተው፤ መንግሥት በተቻለው መጠን በመሰረታዊ የፍጆታ ሸቀጦች ላይ የሚያደርገውን ድጎማ ማጠናከር እንደሚኖርበት አስገንዝበዋል።

የዋጋ ንረትንና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የግብርና የኢንዱስትሪ ምርትና ምታማነትን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ገለጸው፤በተለይ መንግሥት በበጋ ስንዴ የጀመረውን ተስፋ ሰጭ እንቅስቃሴ በሌሎች ምርቶችም ማስፋት ለነገ የማይባል ጉዳይ መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ያላትን የመሬት ሀብት በአግባቡ ማልማት ከቻለች ዘይት ጨምሮ ለሌሎች አገራት የመላክ አቅም እያላት ከውጭ ዘይትና ስንዴ ማስገባቷ የሚያስቆጭ ጉዳይ መሆኑን የተናገሩት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፣ አሁንም ቢሆን የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን በመሳብ ትላልቅ መካናይዝ እርሻዎችን በማስፋት የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ብሎም የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቅረፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዋን ፈትሻ ማስተካከል ይጠበቅባታል ብለዋል።

የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቅረፍ በጥቁር ገበያ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ከማድረግ ጎን ለጎንም በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚኖሩ ዳያስፖራዎች በህጋዊ መንገድ ገንዘባቸውን ሲልኩ የተሻለ ምንዛሪ የሚያገኙበትን የፖሊሲ ለውጥ ማድረግ ጠቃሚ መሆኑንም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ያለመታደል ሆኖ ቤንዝን፣ ዘይት፣ ስንዴ፣ ብረታብረትና ሌሎች ሸቀጦችን በብዛት ከውጭ ታስገባለች ያሉት የምጣኔ ሀብት ምሁሩ፣ ከዛሬ ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የእነዚህ ሸቀጦች ዋጋ መጨመሩ በተለይ የነዳጅ ዋጋ በበርሜል 85 የአሜሪካን ዶላር በላይ ጭማሪ ማሳየቱ በሁሉም ሸቀጦች ላይ የሚፈጥረው የዋጋ ንረት ከፍተኛ መሆኑን አመልክተዋል።

ለዋጋ ግሽበቱና ለኑሮ ወድነቱ አንዱ መንስኤ የሆነው የውጭ ምንዛሪ እጥረት መሆኑን ገልጸው፤ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ባለባት አገር 25 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ መኪናዎችና ሌሎች እጅግ ውድ ሸቀጦች ወደ አገር ውስጥ መግባት እንደሌለባቸው ጠቁመዋል። እነዚህን እጅግ ውድ ሸቀጦች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ በጊዜያዊነትም ቢሆን መከልከል ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ አቶ ዘመዴነህ ገለጻ፣ አንዳንድ የአዲስ አበባ ሱፐርማርኬቶች ብርቱካን እንኳ በውጭ ምንዛሪ ገዝተው ነው ለገበያ የሚያቀርቡት።ከዚህ አኳያ ስለ ውጭ ምንዛሪ እጥረት በድፍረት መናገር ይከብዳል። በብርቱካን ምክንያት ሌሎች መሰረታዊ ነገሮች ለመግዛት የውጭ ምንዛሪ ከምናጣ ብርቱካኑ ቢቀር የሚጎዳን ነገር የለም።

የገበያ ስርዓቱም ሥራ ላይ ያሉ አንዳንድ ድንጋጌዎች በአመዛኙ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ የነበሩ በመሆናቸውን አስታውሰው፤በዚህ ምክንያትም አስመጪና ላኪዎች በተወሰኑ ሰዎች የተያዘ በመሆኑ እንደሌሎች አገራት የሸቀጦችን ዋጋ የሚወስኑ ሸማቾች ሳይሆን እነዚህ ግለሰቦች መሆናቸውን ተናግረዋል።

ዋጋ ግሽበት ለኢትዮጵያ በዱብዳ የወረደ ጉዳይ ሳይሆን ከለውጡ በፊት ጭምር እንደነበር አስታውሰው፤ በዓለም ላይ የተከሰተው የኮሮና ወረርሽኝና የራሺያ-ዩክሬን ጦርነት የዋጋ ንረቱን ይበልጥ እንዳባባሰው አመልክተው፤ አሸባሪው ህወሓት በከፈተው ጦርነት ምክንያትም በተለይ በአማራና በአፋር ክልሎች በቂ ምርት አለመመረቱና መንግሥትም ለኢኮኖሚ ወይም ለሌሎች መሰረተ ልማቶች በድጎማ የሚውል ከ100 ቢሊዮን ብር በላይ ለጦርነቱ ወጪ ማድረጉ የዋጋ ንረቱን እንዳባባሰው አስረድተዋል።

በአገሪቱ በአቅርቦትና በፍላጎት መካከል የተፈጠረው አለመጣጣም ለዋጋ ንረቱ መሰረታዊ ችግር መሆኑን ጠቅሰው፤ በግጭቶችና በድርቅ ምክንያት የተረጂ ቁጥር ማሻቀቡን ተደምሮ የኑሮ ወድነቱን ማባባሳቸውን አስገንዝበዋል።

ባለፈው ወር ብቻ ሲታይ በአገሪቱ የተመዘገበው ጥቅል የዋጋ ግሽበት 35 በመቶ ሲሆን በተለይ የምግብ ሸቀጦች የዋጋ ጭማሪ ደግሞ 40 በመቶ በላይ መሆኑ የኑሮ ውድነቱን አሳሳቢ መሆኑን ጠቁመው፤ በተለይ ሰው ሰራሽ የምርት እጥረት እንዳይከሰት ምን ያህል ሸቀጦች እንደሚያመጡና በስንት ዋጋ እንደሚሸጡ በቴክኖሎጂ የታገዘ የቁጥጥር ስርዓት መፍጠር እንደሚገባም አመልክተዋል።

# ‹‹በከፍተኛ የትምህርት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጥቅም ላይ እየዋሉ እንዳልሆነና መንግሥት ለዘርፉ ያወጣው ሃብት ለብክነት የተጋለጠ መሆኑን እንደሚያሳይም ተናግረዋል።

ዘርፉን የሚመራ ፖሊሲ ማበጀት በመፍትሄነት ከሚወሰዱ ትግበራዎች አንዱ መሆኑንም ነው የጠቆሙት። ዩኒቨርሲቲዎች በተለዩ የትኩረት መስኮች ላይ አተኩረው ማቀድ እንደሚጠበቅባቸውም ተናግረዋል።

ትምህርት ሚኒስቴር የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎችን በተልዕኮና ትኩረት መስክ አደራጅቷል፤ ተግባሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ኢንቨስትመንት በአግባቡ ለመምራት በዋና ፖሊሲ ሰነድነት ጥቅም ላይ በማዋል ፕሮጀክቶችን ስርዓት ለማስያዝ እንደሚያግዝ ታምኖበታል ብለዋል።

የመመሪያው ዋና ዓላማ በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የሚገኘውን ሐብትና ተጨማሪ ኢንቨስትመንቶችን ወደ ዕድገትና ልማት በሚፈለገው ፍጥነትና መጠን ለመለወጥና ለማሸጋገር ያለመ መሆኑ ተገልጧል።

ተግባሩ ዩኒቨርሲቲዎቹ በተሰጣቸው ተልእኮ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል መሆኑንም ነው የጠቆሙት።

በዘርፉ ያለውን ደካማ የመንግሥት ኢንቨስትመንት አስተዳደር ለማሻሻል ከፍተኛ ፋይዳ እንደሚኖረው የገለጹት ዶክተር ፍጹም፤ በውይይቱ የሚገኙ ግብአቶችን የመንግሥት ኢንቨስትመንት አስተዳደር መመሪያን ለማዳበር የሚረዳ ሃሳብ እንደሚገኝም አመልክተዋል።

ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ በርካታ የሪፎርም ሥራዎች ሲደረጉ መቆየታቸውን አስታውሰው፤ የመንግሥት ኢንቨስትመንት አመራርና አስተዳደር የፌዴራል መንግሥት ፕሮጀክቶች አስተዳደር አዋጅ የህግ ማዕቀፍ ጸድቆ ወደ ሥራ መግባቱን፣ አዋጁ የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች ከሃሳብ ማመንጨት አንስቶ ፕሮጀክቶቹ የሚመሩበትንና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ማስቀመጡን ተናግረዋል።

ፕላንና ልማት ሚኒስትር አዋጁን የሪፎርሙ አካል አድርጎ ማጸደቁንና ፕሮጀክቶች ከሃሳብ ጀምሮ እስከፍጻሜው ድረስ ጥራታቸውን የጠበቁና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ገለልተኛ የሆነ የአዋጭነት ግምገማ በማድረግ የገንዘብ ምንጭ እንዲሆኑ ማስቻል በአዋጁ የተቀመጠ ስልጣንና ኃላፊነት መሆኑንም ገልጸዋል።

በተለይ የመንግሥትን ሃብት በከፍተኛ ሁኔታ የሚወስዱ እንደመንገድ፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የመስኖ ፕሮጀክቶች ናቸው፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመንግሥትን ሃብት በከፍተኛ ደረጃ ከሚወስዱት አንዱ እንደመሆኑ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶታል ብለዋል።

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በበኩላቸው፤ በለውጡ ሂደት የመንግሥትን ሃብት በአግባቡ መያዝ እንደሚገባ አስረድተዋል። ሚኒስቴሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ልዩ የትኩረት መስክ ኖሯቸው በማስተማር እውቀትን ትርጉም ባለው መስክ ለማስፋት እየሰራ መሆኑንም ተናግረዋል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ባለፉት 20 ዓመታት ሲተገበር የነበረው ሰፊ የማስፋፋት ሥራ ውጤት ቢኖረውም የጥራት ችግር መኖሩንና ይሄንን ችግር ማጥራት አስፈላጊ ነው።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ በዚህ ዙሪያ ከስርዓተ ትምህርት ቀረጻ አንስቶ በርካታ ተግባራት እየተሰሩ ይገኛሉ። የመውጫ ፈተና መስጠት፣ ዩኒቨርሲቲዎች ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግና የትምህርት ጥራት ጉድለትን የማስተካከል ሥራ በትኩረት እየተተገበረ ነው።

ያለውን ውስን አገራዊ ሃብት ጥራት ያለው ትምህርት ለማዳረስና ዩኒቨርሲቲዎች የልሕቀት ማዕከል የሚሆኑበትን አካሄድ የሚያግዝ ሊሆን ይገባል።

በትምህርት ዘርፉ ጥራትን በማምጣት በእውቀት ላይ የተመሰረተ ተወዳዳሪ፣ የኢኮኖሚ ችግርን የሚፈታ ባለሙያ ማፍራት ይገባል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢትዮጵያና አሜሪካን ታሪካዊ ግንኙነት የሚያሻክሩት የኤች.አር 6600 እና ኤስ 3199 ረቂቅ ህጎች በአስቸኳይ ሊሰረዙ ይገባል!

በዘመነ ቅኝ ግዛት ምዕራባውያን ወደ አፍሪካ ሲተምሙ ይናገሩት የነበረው ማሳመኛ ስልጣኔን ልናስተዋውቃችሁ፤ ብርሃንን ልናበራላችሁ፣ ወዘተ. የሚሉ የብልጣብልጥ ቃላት ነበሩ። በወቅቱ እነዚህን አማላይ ቃላት ከኃይል ጋር ቀምረው አፍሪካን ሲቀራመቱ፤ ስልጣኔውም ሆነ ብርሃን የሚሉት ዲስኩር ከኢትዮጵያውያን ጆሮ ሊገባ፤ ከአገር ክብርና ሉዓላዊነታቸው ከፍ ብሎ ሊሰማቸው ባለመቻሉ የምዕራባውያኑ ሕልም በኢትዮጵያ ላይ ቅዠት ሆነ። ይሁን እንጂ ይሄን ሕልም ሆኖ የቀረ ፍላጎታቸውን እውን ለማድረግ ጊዜን ጠብቀው መሞከራቸው፤ ወቅት አይተው መፈተሻቸው አልቀረም።

በዚህም በቀጥታ ከሚያደርጉት ጥረት በተጓዳኝ የውስጥ ጉዳይ አስፈጻሚዎችን በመመልመልና በማሰልጠን ትጥቅና ስንቅ አስይዘው በነጻ አውጪ ስም በከተማም በጫካም ያላሰለሰ ትግል በማድረግ ታላቋን ኢትዮጵያ ለማዳከም፤ ከባሰም ወደ ትናንሽ ግዛትነት እንድትሸነሸን ለማድረግ ሰርተዋል። በዚህ ረገድ የልባቸውን ተገንዝቦ የሰራላቸው፤ በጥቅም አገሩን አሳልፎ እንደሚሰጥና ለእነሱ ጥቅም ማስጠበቂያ ሁነኛ አጋር ሆኖ የዘለቀላቸው የትናንቱ አገር መሪ የዛሬው አሸባሪ ሕወሓት ነበር።

እነዚህ የውጭ በተለይም የምዕራባውያኑ መንግስታት እንደ ዘመነ ሕወሓት በኢትዮጵያ ላይ ከፍ ያለ አዛዥነት ኖሯቸውና ፍላጎታቸውን አሳክተው አያውቁም። ቡድኑ የሞግዚት አስተዳደራቸው ሆኖ የአገርና ሕዝብ ጥቅምና ደህንነት አሳልፎ የሰጠ ጉዳይ አስፈጻሚ ነበር። ለዚህም ነው ዛሬ ላይ በሕዝብ ተጠልቶ ከማዕከላዊ መንግስት ሥልጣኑ በተገፋ ማግስት ጩኸቱን ለእነዚሁ መንግስታት ማሰማቱና እነዚህ መንግስታትም የቡድኑን እልቅና ለማስቀጠል የሚያስችላቸውን ጓዳ ጎድጓዳ መቧጠጥና መዳከር የጀመሩት።

ይሄን እውነት በማሳያ ለማንሳት ያህል፤ የመጀመሪያው ጉዳይ አሸባሪው ሕወሓት በ27 ዓመታት የስልጣን ዘመኑ በኢትዮጵያውያን ላይ ሲፈጽም የኖረው ከፍ ያለ ጭቆናና ሰብዓዊ ጥሰት በታሪክም በሕግም ተጠያቂ የሚያደርገው ሃቅ ነው። ይሁን እንጂ ለዴሞክራሲና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ከእኛ በላይ የሚሰራ፤ ከእኛ በላይም የሚቀረቀር የለም ሲሉ የሚደመጡት የምዕራቡ ዓለም መንግስታትና ድርጅቶች፤ የዚህን ቡድን የከፋ ጭቆናና በሰው ልጆች ላይ የተፈጸመ ግፍ በአፍ እንኳን ለማውገዝ አልፈለጉም።

ሌላው ጉዳይ፣ በእነሱ ላይ ቢሆን ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ የሚገመት ቢሆንም፤ የሽብር ቡድኑ ከማዕከል ወጥቶ ወደ ክልል ገብቶ በተወሸቀ ማግስት አገርን ለማፍረስ ባለው እኩይ ዓላማ በሰሜን እዝ የአገር መከላከያ ሰራዊት አባላት ላይ የፈጸመውን ተግባር በዝምታ አልፈውታል። ይባስ ብሎ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት ያለ የሌለ ሃብትና ኃይላቸውን ፈሰስ የሚያደርጉት እነዚህ አካላት፤ የሕወሓት ቡድን በኢትዮጵያ እያደረገ ካለው ጥፋትና የሽብር ተግባር አንጻር የአገሪቱ ከፍተኛው አካል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቡድኑን በሽብርተኝነት በፈረጀ ማግስት የምዕራቡ ዓለም መንግስታትና ተቋሞቻቸው ለአሸባሪው ቡድን ጥብቅና ቆመው ሲሞግቱና ሲሰሩ ተመለከትን። በዚህም የሽብር ቡድኖችን ለማጥፋት ሲታትሩ የምናውቃቸው አሜሪካ እና ግብረአበሮቿ ከነግብረሰናይ ተቋሞቻቸው ለሽብር ቡድኑ ማንሰራራት ቀን ከሌሊት ሲሯሯጡ ታዘብናቸው።

ይህ የሚያሳየው ደግሞ እነዚህ መንግስታት ስለ ዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብት፤ ስለ ሽብርተኝነትና ሌላም ጉዳይ የሚሰሩትም፣ የሚናገሩትም ለራሳቸው ጥቅምና ፍላጎት እንጂ እውነትም ለሰላም፣ ዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብት መከበር ስላላቸው ተቆርቋሪነት አለመሆኑን ነው። ይሄንንም ለእነርሱ ጥቅምና ፍላጎት መጠበቅ ምቹ ያልሆነ መንግስት በተፈጠረባቸው አገራት ላይ በሚያሳድሩት ጫና መገንዘብ ይቻላል። የሕወሓትን ከስልጣን መወገድ ተከትሎ በኢትዮጵያ እውን በሆነው መንግስት ላይ እያሳደሩ ያለው ጫናና ማስፈራሪያም የዚሁ አካሄዳቸው ዐብይ ማሳያ ነው።

ምክንያቱም ትናንት በኢትዮጵያ በኃይል ገብተው መያዝና ማዘዝ ያቃታቸውን አገርና መንግስት በሕወሓት ዘመን ለማሳካት እድል ያገኙ ቢሆንም፤ ዛሬ ላይ ያንን እድላቸውን ተነጥቀዋል። የሕወሓት መንኮታኮት ያሳጣቸው ጥቅም እንቅልፍ አሳጥቷቸዋል። እናም ሕወሓት ማንሰራራት የሚችልባቸውን አማራጮች ተጠቅመው ወደ ስልጣን ለመመለስ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ጫና ማሳደርን ሥራዬ ብለው ይዘዋል። በዚህ ረገድ አሜሪካ ስታደርግ የቆየችው ኢትዮጵያን ከአግዋ ማገድን ጨምሮ የተለያዩ ማዕቀቦችን የመጣል ጫና ተጠቃሽ ነው።

ይህ ሁሉ እገዳና ማዕቀብ ግን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ሊያንበረክክና እጅ ለመጠምዘዝም አላስቻለም። እናም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኤች.አር6600 እና ኤስ3199 የተሰኙ ረቂቅ ሕጎችን በጥቂት እንደራሴዎቿ አማካኝነት ነድፋ የኢትዮጵያን መንግስት የማሽመድመድና የሽብር ቡድኑን ወደ ስልጣን ለመመለስ ሲሰሩ ቆይተዋል። እነዚህ ረቂቅ የሕግ ማዕቀፎችም በቅኝ ግዛት ዘመን ሲጠቀሙበት የነበረውን አይነት ስልጣኔንና ብርሃንን ይዞ ወደ አፍሪካ የመግባት ዕቅድ ሁሉ "በኢትዮጵያ ሰላምን የማስፈን፤ ዴሞክራሲን የማረጋገጥና የሰብዓዊ መብት እንዲከበር የማድረግ" ዓላማ ያለው ስለመሆኑ አሽሞንሙነው ይናገሩለታል።

እውነታው ግን ከዚህ በተቃራኒው ነው። ምክንያቱም ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ጥቅማቸውን ባስጠበቁባቸው ጊዜያት ጭቆና፣ የሰብዓዊ ጥሰት፣ ሞትና ሰቆቃ በበዛባቸው ጊዜያት ለማስመሰል እንኳን ቃል ያልተነፈሱት እነዚህ ኃይሎች፤ ዛሬ ላይ በኢትዮጵያ ላይ እንዳሻቸው እጃቸውን ጭነው ፍላጎታቸውን ማስፈጸም ሲሳናቸው በዴሞክራሲና በሰብዓዊ መብት ሽፋን የቀደመ ጉዳይ አስፈጻሚያቸውን ወደ ስልጣን ለመመለስ ያላቸውን ፍላጎት ማስፈጸሚያ መሳሪያ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ የሽብር ቡድኑን የጥፋት ተግባር አውግዘው፤ በሕዝብ ከተመረጠው መንግስት ጋር በጋራ ተጠቃሚነት መርህ አብረው ሊሰሩ፣ የሰላምና ዴሞክራሲ እንዲሁም የልማት አጋርነታቸውን ሊያረጋግጡ ይገባ ነበር።

ሆኖም እነዚህን ረቂቅ ሕጎች ለማጸደቅ በብርቱ ሲሰሩ ቆዩ። ይሁን እንጂ ሂደቱ በኢትዮጵያውያን ብርቱ ተቃውሞ የገጠመው ከመሆኑ ባለፈ፤ አሁን ላይ በኢትዮጵያ ያለው ተጨባጭ እውነታ ሕጉን ለማጽደቅ ተጨባጭ ምክንያት እንዳይኖር አድርጓል። በአጠቃላይ የኢትዮጵያንና የአሜሪካን የቆየና ታሪካዊ ግንኙነት ሊያበላሹ የሚችሉትን እነዚህን ኢፍትሃዊ ረቂቅ ህጎችን መሰረዝ ሁነኛ መፍትሄ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ለዚህም ሲባል እንደ ቀድሞው ሁሉ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ድምጹን ሊያሰማና በቃ ሊል ይገባል!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የሕዝብ ብሶት ገንፍሉ አደባባይ ሳይወጣ የሚጨበጥ ለውጥ ይምጣ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

በቅርቡ አንድ ልብ የሚነካ ንግግር በአንድ የቴሌቪዥን መስኮት ተመለከትኩ። «በግድ ብሉ እያልኩ አሞላቅቄ ያሳደኳቸውን ልጆች ምግብ ፈልገው ሲያለቅሱ የምሰጣቸው አጣሁ» የሚል። ንግግሩ የተደመጠው ከመኖሪያ ቀያቸው በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ ተፈናቅለው በመጠለያ ጣቢያ ከሚገኙ አንዲት እናት አንደበት ነው። ልጅ ራበኝ ብሎ ምግብ ሲጠይቅ ቆርሶ አልያም ፈትፍቶ ለመስጠት እጅ ከማጠር በላይ ለእናት ምንም የሚያስጨንቅ ነገር እንደሌለ ለመረዳት እናት መሆን ግድ የሚል አይደለም።

የእኚህ እናት ንግግር ለሚዲያ ስለበቃ ለአብነት አነሳነው እንጂ፤ አሁን አሁን በኢትዮጵያ መሰል አሰቃቂ ድምጾች በየቦታው ከፍ ብለው መደመጥ ከጀመሩ ውለው አድረዋል። ችግሩ ጎልቶ የሚታየው በጦርነትና በድርቅ በእጅጉ በተፈተኑ አካባቢዎች ቢሆንም፤ በአገሪቱ በተፈጠረው ከፍተኛ የኑሮ ውድነት ምክንያት የአብዛኞቻችን ጓዳ በችግር እየፈተነ ነው። በተለይም በዝቅተኛ ደመወዝ ተቀጥረው ለሚሰሩ እና በአነስተኛ የጡረታ፣ እንዲሁም ያለምንም ገቢ የሚኖሩ ወገኖች የሕይወት መራራነት ከዕለት ዕለት ማየሉን ቀጥሏል።

"ልጆቼን ምን ላብላቸው"፣ "ይህን ገንዘብ ምኑን ከምን አድርጌ ልኑርበት"፣ "የቤት ኪራይ ከየት አምጥቼ ልክፈል"፣ "ጎዳና መውደቄ ነው"፣ የሚሉና ሌሎችም የሰቆቃ ድምጽ ለጆሯችን እንግዳ፤ ለሕይወታችንም ሩቅ አልሆኑም። በቅርቡ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቃለ ምልልስ ያደረጉት የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ካሣሁን ፎሎ ይህን ሀሳብ የሚያጠናክር ገለጻ አድርገው ነበር። ምክንያቱም እርሳቸው ባቀረቡት ገለጻ መሰረት፤ ከሁለት ዓመታት በፊት የወጣው የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል የሚወስን የደመወዝ ቦርድ ይቋቋማል ይላል። ሆኖም እስካሁን ድረስ ቦርዱ ተቋቁሞ የተቀመጠ ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ባለመኖሩ፤ ከአንድ ሺህ ብር በታች ደመወዝ የሚከፈላቸው ሰራተኞች ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም።

ይህ ገንዘብ ደግሞ የቤት ኪራይ መክፈል፣ የምግብና ተያያዥ ወጪዎችን መሸፈን ቀርቶ አምስት ሊትር ዘይት እንኳን መግዛት አያስችልም። በመሆኑም ብዙ ሠራተኞች ምሳ ቋጥረው መሄድ ስለማይችሉ ጾማቸውን ሥራ መዋል እየተገደዱ ነው። ከዚህም ባለፈ አብዛኛው ሰራተኛም በአሁኑ ወቅት ዝቅተኛ የቤት ኪራይ ፍለጋ ከመስሪያ ቤቱ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን ርቆ ይኖራል። ይህ አይነቱ ሰራተኛ ከመኖሪያ ቤቱ ማልዶ ወጥቶ ሥራ ውሎ ምንም አይነት ምግብ ሳይበላ ወደ ቤቱ ሲመለስ የግለሰቡ ሕይወት ምን ያህል አሰልቺና አሰቃቂ እንደሆነ ማብራሪያ የሚያስፈልገው አይደለም። አኗኗራችንም ወደየት እያመራ እንደሆነ ግራ የሚያጋባ ነው።

በቅርቡ የአገር ውስጥ ጋዜጠኞች የደብረ ብርሃን እና ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ጎብኝተው ነበር። በዚህ ወቅት የሠራተኞች ሮሮን ልብ ብሎ ላዳመጠ ሰው ምናልባትም ሥራ አለኝ ለማለት ካልሆነ የእነዚህ ሰዎች ገቢ ከሥራቸው አንጻር ፍጹም ተቀባይነት የሌለው ነው። ሠራተኞቹ "...እጃችን ላይ እየደረሰ ያለው ከአንድ ሺህ ብር ያልበለጠ ገንዘብ ነው፤ በዚህ ገንዘብ የቤት ኪራይ ከፍለን፣ የምግብና ሌሎችንም ወጪዎች ሸፍነን ለመኖር ፈተና ሆኖብናል" ሲሉ ነበር የተደመጡት። የሚመለከተው አካል ሕይወታቸውን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል ዘላቂ መፍትሔ ይፈልግላቸው ዘንድም በምሬት ነበር የተናገሩት።

የእነዚህን ሰራተኞች ድምጽ ያደመጡትና ምላሻቸውን የሰጡት የየፓርኮቹ ኃላፊዎች ደግሞ፤ የሠራተኞችን ተጠቃሚነት ለማሻሻል ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ባለመቀመጡ ይህ ጉዳይ እንዲሻሻል ለማድረግ ፈተና እንደሆነባቸውም ነው ሲገልጹ የተሰማው። ይህ ደግሞ ለችግሩ ከፍ ባለ አካል መለስ ሊሰጠው እንደሚገባ ያሳየ ሲሆን፤ መንግሥት እነዚህን ዜጎች መስማት ከፈለገ የግድ አደባባይ እስኪወጡ መጠበቅ የለበትም። በወቅቱ ገበያ አምስት ሊትር ዘይት ለመግዛት አቅም በሌለው ደመወዝ ሕይወታቸውን እየገፉ ያሉ እልፍ ዜጎችን ጥያቄ ለመመለስም ከአንገት ሳይሆን ከአንጀት መሥራት ይኖርበታል።

ዜጎች አገሪቱ ያለችበትን አጣብቂኝ ከግምት በማስገባት የልጆቻቸውን የማያባራ የዳቦ ጥያቄ፣ የራሳቸውንም በልቶ የማደር ትግል ተቋቁመው መንግሥት መፍትሔ እስኪሰጣቸው በትዕግስት እየጠበቁ ነው። ይሁን እንጂ ጊዜ ለማይሰጠው ጥያቄ አፋጣኝ መልስ እንዲሰጡ የሚጠበቅባቸው አንዳንድ የሥራ ኃላፊዎች ግን ከስግብግብ ነጋዴዎች ጋር በመመሳጠር የሕዝብን ሸክም እያከበዱ ነው የሚል ቅሬታም ይሰማል። በቅርቡ በአዲስ አበባ እና በሌሎችም የክልል ከተሞች በተደረጉ የሕዝብ ውይይቶች አመራሩ የሕዝቡን የኑሮ ጫና ከማቃለል ይልቅ አባባሽ እየሆነ ነው የሚል ወቀሳ ተደጋግሞ መደመጡም የዚህ ብሂል አንድ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው።

ገዢው ፓርቲ ብልጽግና ከመጋቢት 2 እስከ መጋቢት 4 ቀን 2014 ዓ.ም ባካሄደው አንደኛው ጠቅላላ ጉባኤ ወቅት የኑሮ ውድነቱን ለማቃለልና የዜጎችን የኑሮ ጫና ለማቃለል ተጨባጭ እርምጃዎች እንደሚወሰዱ ቃል ገብቷል። ይሄን መነሻ በማድረግ ከጉባኤው ማግስት ለፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት በተሰጠ አቅጣጫ መሰረት ሕብረተሰቡ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች ቀርቦ ለማዳመጥ እንዲቻል በየደረጃው ሕዝባዊ ውይይቶች ተደርገዋል። በዚህ ወቅት በርካታ ችግሮች የተነሱ ቢሆንም የኑሮ ውድነት መፍትሔ ይበጅለት፣ እና ከሁሉም በፊት የዜጎች የመኖር ዋስትና ይረጋገጥ የሚሉ ሀሳቦች ሚዛን ደፍተው ተስተውሏል። መንግሥትም ለዜጎች ጥያቄ በሂደት መፍትሔ እንደሚሰጥ ቃል ገብቷል።

ይሁን እንጂ ብዙዎች መንግሥት በተለያየ ጊዜ እርምጃ እንደሚወስድና ለሕዝቡ እንደሚያሳውቅ ቃል የገባቸው አያሌ ጉዳዮች የውሃ ሽታ ሆነው በመቅረታቸው፤ አሁን ላይ የተገቡ ቃሎች ወደ ተግባር ስለመቀየራቸው ስጋት አላቸው። ይህ ስጋት ደግሞ ያለምክንያት አይደለም፤ ይልቁንም የሚወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች በጊዜው ተተግብረው መፍትሄ የማይመጣ ከሆነ የቤት ኪራይ መክፈል ካልተቻለ ወደ ጎዳና፣ የቤተሰቡን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ አዳጋች ሲሆንም ወደ ዝርፊያና ሌሎች ሕገወጥ ተግባራት ሊያመራ ከሚችል አሳሳቢ ጉዳይ በመነሳት ነው።

በመሆኑም የኑሮ ውድነት እንደ ከዚህ ቀደሙ በእናጣራለን እና እርምጃ እንወስዳለን ሽንጋይ ቃላት ሊታለፍ የሚችል አይደለም። መንግሥት ለሕዝቡ በገባው ቃል መሠረት በአጭርና በረጅም ጊዜ ሊሠሩ የሚገባቸውን የቤት ሥራዎች በመሥራትና ሕዝቡን በማስተባበር የገባውን ቃል ወደ ተግባር ለማሸጋገር ዛሬውኑ የሚታይና የሕዝቡን ሸክም ሊያቀል የሚችል ተግባራዊ እርምጃ መጀመር አለበት። "የሚበላውን ያጣ ሕዝብ መሪዎቹን ይበላል" እንዲል፣ ይህ ካልሆነና ሕዝቡ የእለት ጉርሱን ማግኘት ሲያቅተው በቀላሉ ለችግር ፈጣሪ ኃይሎች ፊት መስጠቱ፤ የእለት ጉርሱን ማሟላት ሊያገኝበት በሚችለው አግባብ መሰማራቱ፤ ገፋ ሲልም ለአመጽና ተቃውሞ መነሳቱ እንደማይቀር ከጎረቤት አገራት ልንማር ይገባል። እናም የሕዝብ ብሶት ገንፍሎ አደባባይ ሳይወጣ የሚጨበጥ ለውጥ ሊመጣ የግድ ይሆናል። ለዛሬው አበቃሁ፤ ቸር ያቆየን፤ ሰላም!

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ‘ደላላ’ - “አራተኛው መንግሥት!?”

**በቁምላቸው አበበ ይማም ( ሞሼ ዳያን )**
**fenote1971@gmail.com**

በአገራችን የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት ተጃምለው የአብዛኛውን ኢትዮጵያዊ የዕለት ተዕለት ኑሮ አሳር እያደረጉት ነው። ከኢኮኖሚያዊ ቀውስነት ባሻገር ወደ መልካም አስተዳደርና ፖለቲካዊ ጥያቄ እያደገ ነው። በደምሳሳው የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ችግሮ አደባባይ አውጥተዋል። ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአንድ በኩል በአቦሰጥ የኑሮ ውድነቱን የፈጠረው የአቅርቦትና የፍላጎት አለመጣጣም ነው ይለንና መፍትሔው ምርታማነትን ማሳደግ ነው ቢልም፤ ግብርናውን የሚመለከተው ተቋም ደግሞ የምርት እጥረት የለም በማለት፤ ምርት በየአመቱ እየጨመረ መሆኑን አኃዛዊ መረጃዎችን እየጠቀሰ ይሞግታል።

በሌላ በኩል አርሶ አደሩ የገበያ ትስስር አልተፈጠረልኝም እያለ ሲያማርር በሚዲያ ይደመጣል። ከአዲስ አበባ በመቶዎች ኪሎ ሜትር ርቀት ሽንኩርትና ቲማቲም በአስራ ምንአምን ብር እየተሸጠ፤ አዲስ አበባ ሲደርስ ከእጥፍ በላይ የሚሸጥበትና ሲብስም ከገበያ የሚጠፉበት ምክንያት ብዙውን ሸማች ግራ ያጋባል። በዚህ መልኩ ኢኮኖሚውን ተብትበው የያዙት ችግሮች እንዳሉ ሆነው፤ በአምራቹና በሸማቹ መካከል የተፈጠረው የገበያ ሰንሰለት መርዘም፤ ከማሳ፣ ከጉልት አንስቶ እስከ ጅምላና የውጭ ንግድ የተሰገሰገው እንደ እንጉዳይ የፈላ ደላላ ለኑሮ ውድነቱ ግንባር ቀደም ተከሳሽ ሲሆን ከውጭ የሚገባው ንግድ በጣት በሚቆጠሩ አስመጪዎች እጅ መውደቁና ምርትን መያዝና ገበያውን ማሻጠር ሌላው ተወቃሽ ሆኖ ይነሳል።

ያም አለ ይህ ኢኮኖሚው የሥርዓትና የሕጋዊነት በገበያ መርህ የመመራት መዋቅራዊና ተቋማዊ ችግር ያለበት መሆኑ አያጠያይቅም። 80 በመቶ አርሶና አርብቶ አደር ባለበት አገር የምርት አቅርቦት ችግር አለ ቢባል ውሃ አያነሳም። ሆኖም ግብርናችን በተበጣጠሰ መሬት ሜካናይዝድ ባልሆነ አግባብ በአለበት ሲረግጥ መኖሩ የሚካድ አይደለም። ዳሩ ግን ከአምራቹና ከሸማቹ ቁጥር የማይተናነሰው ደላላ ገበያውን አንቆ አላላውስ ከማለት አልፎ በመዳፉ ስር ማድረጉ በእንቅርት ላይ ቆረቆር ሆኗል። በነጻ ገብያ ስም ገበያው ስድ መለቀቁና የትርፍ ሕዳግ አለመወሰኑ እና የመሠረታዊ ሸቀጦች ዋጋ አለመተመኑ ሌላው ችግር ነው። የአገራችን ኢኮኖሚ በአዳም ስሚዝ የኢኮኖሚክስ ሀ ሁ በፍላጎትና አቅርቦት ሳይሆን በደላላ የሚዘወር ነው። ገበያው ካለበት መዋቅራዊ ችግር ባልተናነሰም በገበያው የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ ክፍተት መኖሩ ችግሩን አወሳስቦታል። በዓለማችን ባልተለመደና ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በአገራችን የተሰገሰገው ደላላ በገበያውና በኢኮኖሚው ላይ አዛዥና ናዛዥ ሆኗል። ደላላው በመንግሥት ውስጥ ያለ የገበያ መንግሥት ሆኗል። ምንም አይነት ጊዜያዊና ዘላቂ መፍትሔ ቢቀመጥ ደላላውን ከኢኮኖሚ መዋቅር ማስወጣትና በሕግና በሥርዓት እንዲመራ ካልተደረገ ከዚህ የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት አዙሪትና ቀለበት ሰብሮ መውጣት አይቻልም።

“አራተኛው መንግሥት “(The Fourth Estate) የሚለው ስያሜ ሀረግ ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ ላይ የዋለው የዛሬ 234 ዓመታት በሀገረ እንግሊዝ ነው። አንዳንድ የታሪክ መዛግብት ደግሞ ከዚህ ግማሽ ክፍለ ዘመን ቀድሞ እንደነበረም ያወሳሉ። በዛ ጊዜ ሶስቱ መንግሥታት በመባል ይታወቁ የነበሩት፤ 1ኛ.ቤተ ክርስቲያኗ፣ 2ኛ.መሳፍንቱ፣ 3ኛ.ተራው ሕዝብ ሲሆን፤ 4ኛ.ጋዜጠኞችና መገናኛ ብዙኃን ነበሩ። አራተኛው መንግሥት የሚለውን አባባል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙት የታላቋ ብሪታኒያ የፓርላማ አባል ኤድሞንድ ቡርክ ሲሆኑ፤ አመቱም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1787 እንደሆነ የታሪክ ድርሳናት ከትበው አቆይተውናል። ከዚህ ቀደም ባሉት ዓመታት ንግስቷ፣ የሕግ ባለሙያዎች (lawyers) እና ዝቅተኛው መደብ (ላብ አደሩ /proletariat) እንደ አራተኛ መንግሥት ይቆጠሩ ነበር። ከጊዜ በኋላ ስያሜው ወደ ጋዜጠኞችና ሚዲያ ቋሚ መጠሪያነት ተሸጋግሯል። በተመሳሳይ ሁኔታ በሒደት ሶስቱ መንግሥታት ቀደም ሲል ከነበራቸው ስያሜ ወደ ሕገ አውጭ፣ ሕግ ተርጓሚ እና ሕግ አስፈፃሚ መለወጣቸውን እነዚሁ ድርሳናት ያስረዳሉ። እነዚህ የመንግሥት አካላት መንግሥታቸውን የመቆጣጠሪያ ሚዛንና የመመዘኛ መድለው(check & balance) በመሆን ያገለግላሉ። ሚዲያው አራተኛው መንግሥት መባሉ በአንድ አገር ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳይ ምን ያህል ከፍ ያለ ቦታና ሚና እንዳለው ያሳያል።

በምዕራባውያን በተለይ በእንግሊዝና በአሜሪካ ሚዲያው ከሶስቱ የመንግሥት አካላት ተርታ መሰለፍ ችሏል። በአህጉራችን በደቡብ አፍሪካ፣ በጋና እና በናይጄሪያ እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ በኬንያ፣ በኮት ዲቯር እና በሌሎች አገራት ሚዲያው የአራተኛው የመንግሥት አካልነት ሚናቸውን፣ ኃላፊነታቸውን ከነውስንነተቻው እየተወጡ ነው። እንደ አለመታደል ሆኖ አገራችን የጎለበተ፣ ጥንታዊ የአገረ መንግሥት ልምምድ ቢኖራትም ሚዲያችን ግን አራተኛው የመንግሥት አካል ለመባል ገና ብዙ ብዙ ይቀረዋል። ስለሆነም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር የመንበሩን አለመያዝ ተረድተው ይመስላል በአንድ መድረክ በአገራችን የገነነውን ሙስና አራተኛው መንግሥት በማለት እንደገለፁት ሁሉ፤ እኔም በአገራችን አሉታዊ ተፅዕኖው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ የመጣውን፤ በጊዜ ሀይ ካልተባለ ለአገራችን ህልውና አደጋ እየደቀነ ያለውን፤ የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከጉልት እስከ ጅምላ ንግድ፤ በአጠቃላይ ማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊ ሕይወታችንን እየናጠ ያለውን፤ አደገኛ እየሆነ የመጣውን፣ በሰዓት የተጠመደ ቦንብ (time bomb) ይገልፅልኛል ብዬ ስላመንሁ”ድለላ!?”ን ሳልወድ አምባሻ ሳልቆርስ “አራተኛው መንግሥት!?” ብየዋለሁ።

አዎ ! ከላይ ስለ ሀረጉ ስረወ ቃል ሳትት ፅንሰ ሃሳቡ በቀደመው ዘመን ንግስቷን፣ የሕግ ባለሙያን፣ ሰራተኛውን ለመግለፅ ይውል እንደነበረው ሁሉ፤ እኔም ዛሬ ድለላ በአገራችን ከደቀነው ወቅታዊና ከቡድ ተፅዕኖ አኳያ አራተኛው የመንግሥት አካል ብለው ያንስበት ይሆን እንደሁ እንጅ አይበዛበትም። እንዲያውም ከሕግ አውጭው፣ አስፈፃሚውና ተርጓሚው እንዲሁም ከሚዲያው በላይ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን፣ ጓዳ ጎድጓዳችንን አንዳንድ ጊዜም አልጋ ተጋሪያችንን፣ አንሶላ ተጋፋፊያችንን እስከ መወሰን ከፍ ሲልም ውሃ አጣጫችንን እስከመምረጥ ስለተሸጋገረ “ድለላ!?” 1ኛው የመንግሥት አካል ቢባል ያንሰው ይሆናል እንጅ አይበዛበትም። አዎ! ደላላ ስንበላ የሚበላ፣ ስንጠጣ የሚጠጣ፣ ስንለብስ የሚለብስ፣ ስንገዛ የሚገዛ፣ ስንሸጥ የሚሸጥ፣ ስንከራይ የሚከራይ፣ ስንወስብ የሚወስብ፣... ምን አለፋችሁ ስንሰራ ካለመስራቱ፣ ስንራብ ካለመራቡ፣ ስንታረዝ ካለመታረዙ፣ በችጋር ስንገረፍ ካለመገረፉ፣ በኑሮ ወድነት ስንሰቃይ ካለመሰቃየቱ፣ በዋጋ ግሽበት ኪሳችንንና ቦርሳችን ሲገለበጥ ካለመገልበጡ በስተቀር የማይገባበት የሕይወታችን ቅንጣት፤ የማያንኳኳው በር የለም። ታዲያ አይደለም 4ኛው፣ 1ኛው መንግሥት ቢሆን ይበዛበታል!? ደላላ በሶስቱም የመንግሥት አካላት ማለትም በሕግ አውጭው፣ ተርጓሚውና አስፈጻሚው እንዲሁም በሚዲያው የሰራ አካላት የተሰራጨ አደገኛ ሕመም ነው።

በእያንዳንዳችን ሕይወት አዛዥ ናዛዥ የሆነው “ድለላ!?” የቃሉ ትርጉም ምን ማለት ይሆን!? ምንም እንኳ በሥነ ልሳን አስተምህሮ በስያሜውና በተሰያሚው መካከል የባህሪ ግንኙነት እንደሌለ ቢበየንም፤ የቃሉ ግብርና ምግባር ስለተማታብን፣ ስለተጣረሰብን ትርጉሙን እንመልከት። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በ1993 ዓ.ም ያዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት፤ “ደላላ”ን፡- ‘ገንዘብ እየተከፈለው ተፈላላጊዎችን (ሻጭና ገዥን፣ አከራይና ተከራይን፣...) አገናኝ፣ አስማማ፤’ በማለት ይተረጉመዋል። በመደለል ስራ ላይ የተሰማራ ሰው፤ አታላይ፣ በውሸት አግባብቶ ለማሳመን የሚሞክር፤ “ድላል”ን ደግሞ ለደላላ የሚከፈል ገንዘብ በማለት ይተረጉማል። የደስታ ተክለወልድ ዘሀገረ ወግዳ በ1970 ዓ.ም የአማርኛ መዝገበ ቃላት ደግሞ፤ ደለለ፡- አሞኘ፣ አታለለ፣ ሸነገለ፣ የማያደርገውን አደርጋለሁ አለ፤ ደላላ፡- አመልካች፣ ጠቋሚ፤ ድላል፡- ለጠቋሚ፣ ላስማማ የሚሰጥ ገንዘብ ሲል ይተረጉመዋል። ይሄኛው ትርጉም ከቀደመው ይልቅ የአገራችንን ደላላ ቁልጭ አርጎ ይገልፀዋል።

የእንግሊዝኛውን ትርጉም ‘broker’ ስረወ ቃል ስንመለከት “brocour” ከሚለው የፈረሳይኛ ቃል የመጣ ሲሆን፤ ከ14ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የቋንቋው አካል መሆኑን ሜሪያም ዌቢስተር የእንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት ያወሳና ትርጉሙም፡-{bro·ker: a person who helps other people to reach agreements, to make deals, or to buy and sell property (such as stocks or houses)} ነው ይለናል። የአማርኛውም ሆነ የእንግሊዝኛው መሰረታዊ ትርጉም ተቀራራቢ ቢሆንም፤ “ድለላ” ሲነሳ አብሮ ማታለል፣ መሸንገል፣ ማሞኘት፣ በውሸት አግባብቶ ማሳመን፤ የሚሉ አሉታዊ አንድምታዎች ግዘፍ ከመንሳት አልፈው “ድለላ” በተነሳ ቁጥር ቀድመው ወደ አዕምሯችን የሚመጡት እነዚህ አሉታዊ ብያኔዎች ናቸው። በአገራችን ያለውን አብዛኛውን ደላላም ይገልፁታል ተብሎ ይታመናል። ሆኖም እጅግ ያነሱና በጣት የሚቆጠሩ ቢሆኑም ታማኝ፣ ሀቀኛና መልካም ሥነ ምግባር ያላቸው ደላሎች መኖራቸው ግን ሊዘነጋ አይገባም። ድለላን ከመንግሥት አካላት ተርታ ከማሰለፍ አልፌ እንደ 1ኛው መንግሥት የቆጠርሁበትን አብይት መግፍኤዎችንና መገለጫዎችን ላነሳሳ፤

### 1.ኢኮኖሚያዊ፡-

ኢኮኖሚያችን ከሌሎች አገራት ለየት ያደርገዋል ብዬ ከማምንባቸው ግርምቶች ቀዳሚው፤ በአዳም ስሚዝ የኢኮኖሚክስ ሀ ሁ ዝቅተኛ መስፈርት በሆኑት ፍላጎት/ demand እና አቅርቦት/supply አለመዘወሩ ነው። ከጉልት እስከ ጅምላ ንግድ፣ ከጎጥ እስከ ፌዴራል፣ ከሽንኩርት ማሳ እስከ አትክልት ተራ፣ ከሚዛን ተራ እስከ እህል በረዳ፣ ከአንድ ክፍል ጭቃ ቤት እስከ ተንጣለለ ቪላና ፎቅ፣ ከአንድ ጥማድ መሬት እስከ ጋሻ መሬት፣ ከአራጣ ብድር እስከ ባንክ ብድር፣... ከታች እስከ ላይ በተሰገሰጉ ህልቁ መሳፍርት ደላሎች ሳምባ የሚተነፍስ ኢኮኖሚ መሆኑ ነው። አንድ ወዳጄ በዚያ ሰሞን እንዳጫወተኝ ከሆነ የደላላ እጅ ሀይ ባይ በማጣቱ እረዝሞ እረዝሞ በአንድ ወቅት አገራችን በምትፈርማቸው ብድርና እርዳታ ሳይቀር ፈርቅ እስከመያዝ ደርሶ ነበር። እግራችን እስኪቀጥን ብንዞር የደላላ እጅ ያልገባበት የኢኮኖሚ ዘርፍ የለም። ከላይ ከትርጉሙ እንደተመለከትነው የድለላ ስራ ሻጭና ገዥን ማገናኘት ለዚህም ድላል (የአገልግሎት ክፍያ) መቀበል ቢሆንም፤ የአገራችን ደላላ ግን በዓለም ታይቶም ተሰምቶም በማያውቅ ሁኔታ ዋጋ ቆራጭ፣ ተማኝ፤ ገብያ መሪ እስከመሆን ደርሷል።

አሁን ያለው የእህል፣ የአትክልት፣ የሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ፤ የመኪና የንግድም ሆነ የኪራይ ቤት ክፍያ፣ የመሬት ዋጋ፣... የተቆረጠው፣ የተተመነው በገበያ ሳይሆን በደላላ ነው። በዚህም ገበያ አመጣሽ ሳይሆን፤ ደላላ ዘራሽ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት አስከትሏል። በዚህ የተነሳ ዜጋው በኑሮ ውድነት ፍዳውን እያየ ነው። የሸቀጡ፣ የምርቱ፣ የአገልግሎቱ አምራች፣ አቅራቢም የሚገባውን ጥቅም እያገኘ አይደለም። ከሸማቹም፣ ከሻጩም በሁለት ቢላዋ እየበላ ያለው ሕገ ወጥ ደላላው ነው። ዛሬ በመላው አገራችን ያሉ አርሶ አደሮችም ሆኑ አርብቶ አደሮች በተደጋጋሚ የሚያነሱት ጥያቄ የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸውና ለምርታቸው፣ ለገበያ ከሚቀርቡ እንስሳትም ሆነ ተዋጽኦ ተገቢውን የድካማቸውን ዋጋ እንዲያገኙ ሲወተውቱ፣ ሲማፀኑ በየሚዲያው ብንሰማም፣ ብንመለከትም መፍትሔ ባለማግኘታቸው ዋጋ የሚቆርጥላቸው ደላላው ነው። በምርቱ ተጠቃሚዎች እነሱ ሳይሆን ደላላው ነው። አርባ ምንጭ ገበሬው ኪሎ ሙዝ ሰባት ብር እንዲሸጥ፤ አዲስ አበባ ላይ ደግሞ 40 ብር እንዲሸጥ የወሰነው ገበሬው ሳይሆን ደላላ ነው። አርሶ አደሩም ሆነ አርብቶ አደሩ የድካሙ፣ የላቡ ተጠቃሚ ካለመሆኑ ባሻገር፤ ደላላ አመጣሽ የሆነው የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት የኢኮኖሚውን ወደለየለት ቀውስ እያንደረደረው ነው። ሕገ ወጥ ደላላው ያለ አዛዥ ናዛዥ ገበያውን በብቸኝነት መቆጣጠሩ፤ መንግሥት በነፃ ኢኮኖሚ ስም መነሻ ዋጋ ተመን እና የትርፍ ሕዳግን / profit margin/ አለመወሰኑ፤ ከሕገ ወጥ ደላላው ጋር እሳትና ጭድ ሆኑ የኑሮ ወድነቱን እያቀጣጠለ፤ በዜጋው ላይ ብሶትን፣ ምሬትን ተስፋ መቁረጥን እየከዘነ ይገኛል። በዚሁ ከቀጠለ ወደለየለት ፖለቲካዊ ቀውስ የማያመራበት ምክንያት የለም። በዓለማችን የነፃ ገበያ አባት የምንላቸው ምዕራባውያን ሳይቀሩ የትርፍ ሕዳግንም ሆነ የመነሻ ዋጋ ደረጃን እየወሰኑ፤ ገበያውን እየተቆጣጠሩ ባለበት፤ እኛ ለዛውም ያልሰለጠነውን ኢኮኖሚ ስድ መልቀቃችን ዛሬ ለምንገኝበት ምሬትና እሮሮ ዳርጎናል።

### 2.ማሕበራዊ፡-

ባለፉት ዓመታት ምሳሌ፣ አርዓያ የሚሆን ቤተሰብ፣ ተቋም፣ መሪ በየደረጃው አለመፈጠሩ፤ የግብረ ገብ ትምህርት አለመሰጠቱ፤ ፈሪሀ እግዚአብሔር (ፈጣሪ) ያለው ትውልድ አለመታነፁ ዛሬ ለምንገኝበት የማሕበራዊ ቀውስ አፋፍ አድርሶናል። ውሸት፣ ሌብነት፣ ዘረፋ፣ ማጭበርበር፣ መካድ፣ ጥሎ ማለፍ፣... ነውር መሆናቸው ቀርቶ የሚያሸልሙበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። የዚህ ትውልድ፣ ማሕበራዊ ቀውስ ውጤት የሆነው አብዛኛው ደላላም መዋሸትን፣ ማታለልን፣ በአቋራጭ መክበርን ሙያ እስከማድረግ ተግቷል። ገንዘብ እስካገኘ ድረስ ለዜጋው ለወገኑ ደንታ ቢስ ሆነ። እህት ወንድሞቹን በማይጨበጥ ተስፋ እየደለለ ለስደት፣ ለመከራ ዳርጎ በበርሀ፣ በባህር አለቁ። በአረመኔዎች እጅ ወድቀው የአካላቸውን ክፍል አጡ። ሕገ ወጥ ድለላው በዚህ የሚያበቃ አይደለም።

በአገራችን እየተስፋፋ በመጣው የወሲብ ንግድም ግንባር ቀደም ተዋናይ ነው። ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ልጃገረድ ሕፃናትን ሳይቀር ለሕገ ወጥ የወሲብ ንግድ እስከማቅረብ፣ የዩኒቨርሲቲ ሴት ተማሪዎችን ለዚህ ሕገ ወጥ ተግባር እየመለመለ የፎቶ አልበም አዘጋጅቶ የሚያቀርብ አረመኔ ደላላ በየዩኒቨርሲቲዎቻችን በሮች ማግኘት እየተለመደ መምጣቱ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ዛሬ ዛሬ ደግሞ አዲስ የድለላ ዘርፍ ማለትም ስለ የማህፀን ኪራይ /surrogacy/ ደላሎች መስማት ከጀመርን ውለን አደርን፤ ልጅህን ለልጄ ማለት እየቀረ ተጋቢዎች ራሳቸው ወስነው ትዳር መመስረት እየተለመደ ቢመጣም፤ አሁን ሶስት ጉልቻ በደላላም ተጀምሯል። ምን አለፋችሁ ድለላ ያልገባበት የሕይወታችን ቅንጣት የለም። በእንቅርት ላይ እንዲሉ በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች እየተሸረሸረ በመጣው ማሕበራዊ ተራክቦ ላይ ሥነ ምግባር የሌለው ሕገ ወጥ ደላላ በአናቱ ተጨምሮበት ቀውሱን እያባባሰው ነው።

### 3.ፖለቲካዊ፡-

ሕገ ወጥ ደላላው በኢኮኖሚው የሚስተዋሉ መዋቅራዊ፣ ተቋማዊ ችግሮችን በማበባስ የሕዝቡን የዕለት ተዕለት ኑሮ ፈታኝ እያደረገው ይገኛል። በዓል በመጣ ቁጥር የሚስተዋሉ እጅግ የተጋነኑ የዋጋ ጭማሬዎችን እዚህ ላይ በአብነት ማንሳት ይቻላል። በቋሚነት የኑሮ ወድነቱን፣ የዋጋ ግሽበቱን በማባባስ ዜጋውን ለብሶት፣ ለምሬት እየዳረገ ነው። እዚህም እዚያም ለሚስተዋሉ ግጭቶች በአንድም በሌላ በኩል የዋጋ ግሽበቱና የኑሮ ውድነቱ የፈጠረው ተስፋ መቁረጥ እንደ ክብሪት ሆኖ በማገልገል ላይ መሆኑን የተለያዩ አካላት እያነሱ መሆኑ፤ የሕገ ወጥ ደላላ እጅ ከኢኮኖሚው አልፎ በማሕበራዊ መዋቅራችን ከፍ ሲልም ከሌሎች መግፎኤዎች ጋር ተዳብሎ አገራዊ ቀውስ በመለፈፍ፣ በመጥራት ላይ መሆኑን ተገንዝቦ ከዚህ በላይ ሳይረፍድ፣ ሳይቃጠል በቅጠል ሊባል ይገባል።

### እንደ መውጫ

ራሳቸውን ሕጋዊ ብለው የሚጠሩትም ሆነ ሕገ ወጥ ደላላዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በዜጋው፣ በአገሪቱ ላይ እያሳደሩት ያለውን አሉታዊ ዘርፈ ብዙ ተፅዕኖ ለማስወገድ መንግሥት የዘነጋውን፣ ችላ ያለውን ኃላፊነቱን ዛሬ ነገ ሳይል መወጣት ሊጀምር ይገባል። በድለላ የሚዘወረው ኢኮኖሚ ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሽ የሆነው ሸማች፣ ሕዝብም ኢኮኖሚውን ከድለላ ምርኮ ነፃ ለማውጣት የድርሻውን ማበርከት ይጠበቅበታል። የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የችግሩን አሳሳቢነት በመገንዘብ የሚመለከታቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶችን መጠየቅና ከጥልቅ እንቅልፋቸው መቀስቀስ ይጠበቅበታል። የዘርፉ ልሒቃንም የአደጋውን ስፋት በጥናት ተንትነው ሊያስረዱ ይገባል።

ከዚህ ጎን ለጎን መንግሥት በየደረጃው ከጎጥ እስከ ፌዴራል፣ ከሽንኩርት፣ ከቲማቲም እስከ ጅምላ ንግድ ገበያውን፣ የንግድ ሥርዓቱን በኔት ወርክ ተደራጅቶ እያተራመሰ ያለውን ሕገ ወጥ የድለላ ኃይል ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በቃህ!!! ሊለው ይገባል። መንግሥት በአጭር ጊዜ መሰረታዊ ሸቀጦችን አገልግሎቶችን ሙሉ በሙሉ ከደላላ ነፃ በማድረግ፤ ሸማቹና ሻጩ ያለደላላ በገበያ ሥርዓት በቀጥታ እንዲገበያዩ መደላደሉን ሊፈጥር ይገባል። ከዚህ በመቀጠል የገበያ ሰንሰለቱን ከሕገ ወጥ ደላላ መዳፍ ፈልቅቆ ነፃ አውጥቶ ሕግን ማስከበር ይጠበቅበታል። በመቀጠል ሕጋዊ ደላላው የሚገዛበት ሕገ ደንብ እና እንደአስፈላጊነቱ የሥነ ምግባር መመሪያ ሊዘጋጅ ይገባል። የደላላ ክፍያና ድለላ የሚፈቀድባቸውና የሚከለከልባቸው ምርቶችና አገልግሎቶች በሕግ በማያሻማ ሁኔታ መለየት አለባቸው።

# ወቅታዊ

# በቁጠባ መጠቀም የማንችል ከሆነ በቀጣይ ነዳጅ በኮታ ልንሰጥ የምንችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል

-አቶ ገብረመስቀል ጫላ
የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር

ዕፀገነት አክሊሉ



ስድስተኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አንደኛ የሥራ ዘመን አምስተኛ መደበኛ ስብሰባውን ከትናንት በስቲያ ሲያደርግ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴርን የስምንት ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አቅርቧል። በወቅቱ በርካታ የምክር ቤት አባላት የኑሮ ውድነቱን የሚያባብሱ ሕገወጦች ላይ ተገቢው እርምጃ አልተወሰደም፤ በዚህም የተነሳ የሸቀጦች ዋጋ መቆጣጠር አልተቻለም፣ በነዳጅ ላይ ከፍተኛ እጥረት ይስተዋላል ፣ የሚሉና ሌሎች ጥያቄዎችን አንስተዋል። የንግድና ቀጠናዊ ትስሰር ሚኒስትሩ አቶ ገብረመስቀል ጫላም ለተነሱት ጥያቄዎች መልስ ሰጥተዋል።

እኛም የምክር ቤቱን ውሎ መሰረት በማድረግ ከተነሱ ጥያቄዎች ውስጥ ጥቂቱን በማንሳት የተሰጣቸውን ምላሽ ይዘን ቀርበናል፤ መልካም ንባብ።

**ጥያቄ፡-የአገሪቱ ኢኮኖሚ የሚመራበት የንግድ ፖሊሲ ሥርዓት ዝግጅት በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? የተለያዩ ዘርፎች አዋጅ ወጥቶላቸዋል ነገር ግን አዋጁን ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያና ደንብ ያልወጣላቸውና ወደ ስራ እንዲገቡ ያልተደረገበት ምክንያት ምንድን ነው? ለአብነት የተሻሻለው የንግድ ሕግ በአዋጅ ደረጃ ነው ያለው ፤**

**አቶ ገብረመስቀል፡-** በ1952 ዓ.ም በኢትዮጵያ የወጣ የንግድ ሕግ አለ፤ ይህ ሕግ የተሟላ እና ብዙ ህጎችንም በውስጡ የያዘ እንዲሁም በርካታ መንግሥታትን ያገለገለ ነው። ነገር ግን ዘመኑ የቴክኖሎጂ ከሆነ በኋላ ህጉ ይህንን መሸከም የማይችል በመሆኑ ባለፉት የተወሰኑ ዓመታት እንዴት አድርገን ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር እናጣጥመው የሚለው ሲጠና ነበር።

ይህንን ህግ ለማሻሻል ጥናት በሚደረግበት ጊዜ ጎን ለጎን የሚወጡ አዋጆች ደንቦች መመሪያዎች እየተሻሻሉ ነበር። በመሆኑም አሁን ላይ ህጉን በምናይበት ጊዜ ከሞላ ጎደል አሁን ያለውን አሰራር የሚሸከም ነው። አንድ መመሪያ በተለይም ከንግድ ህጉ ጋር የተያያዘና የሚሻሻል አለ።

በመሆኑም የንግድ ሕጉ አሁንና ቀድሞ በነበረው ልዩነቱ ምንድን ነው? የሚለውን በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያሉ እንዲሁም በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች እንዲያውቁት በየክልሎቹ ሥልጠና እየተሰጠ ነው። በመሆኑም ይህ የንግድ ሕግ የተሻሻለው ከዲጂታላይዜሽንና ከዘመናዊነት አንጻር ከኦን ላይን ሲስተም ጋር የተያያዘ ጉዳይ ካልሆነ በቀር በመሰረታዊነት የሚቀየር ነገር አልተገኘም።

በሌላ በኩልም በዚህ ስምንት ወራት ውስጥ እቅድ ይዘን በፖሊሲ ጉዳይ ላይ የሰራናቸው ሥራዎች አሉ። ለምሳሌ የንግድ ፖሊሲ እኛ ስንመጣ ያልተጀመረ ነበር፤ አሁን ጀምረን አጠናቀን በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ አቅርበናል። ሌላው ብሔራዊ የጥራት ፖሊሲ ሲሆን ይህም በመጠናቀቅ ላይ ከመሆኑም በላይ ሕብረተሰቡ እየተወያየበት ነው።

**ጥያቄ፡- በፍጆታ እቃዎች ላይ የመንግሥት ድጎማን በተመለከተ ማለትም ዘይት ስንዴ ስኳርና ሌሎችም ከቀረጥ ነጻ የማስገባትና በዘርፉም የተሰማሩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደጎም የተሻለ እንዲያመርቱ እየተደረገ ነው። ነገር ግን ለተጠቃሚው ሕብረተሰብ ፍትሃዊ ስርጭት የሌለ በመሆኑ ሕብረተሰቡ ለከፍተኛ የኑሮ ውድነትና የዋጋ አለመረጋጋት ችግር ተዳርጓል። ይህንን ሁኔታ ለማሻሻል ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ ገብረመስቀል፡-** ከመሰረታዊ ሸቀጦች ጋር በተያያዘ መንግሥት በተለይም ዘይት ስኳር ስንዴ በማቅረብ የሕብረተሰቡን ፍላጎት ለማሟላት ትልልቅ ውሳኔዎችን ወስኗል። ለምሳሌ ዘይትን ለማምረት ወደ 4 መቶ ሚሊዮን ዶላር መድቦ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ዘይት ከቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲያስገቡ ሆኗል። ይህ ቢሆንም ፍላጎቱ ትንሽ ባለመሆኑ ውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲያስገቡ እድል ተሰጥቷል። የውጭ ምንዛሪ የሂሳብ ቁጥር (አካውንት) ያላቸው ኢትዮጵያውያን እንዲያስገቡ ፍቃድ ተሰጥቷል።

የኑሮ ውድነትን ለማስተካከል በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንዴት ችግር እንደሆነ የሚታወቅ ቢሆንም አንዳንድ ነገሮችን በማስረጃ አስደግፌ መናገር እፈልጋለሁ። በአሁኑ ጊዜ በተለይም በዩክሬንና በራሺያ መካከል የተፈጠረው ጦርነት ትልልቅ የዓለምን ንግድ የሚያዛቡ ሁኔታዎችን እየፈጠረ ነው። ለምሳሌ ዩክሬን ከፍተኛ የሆነ የምግብ ዘይት የምታቀርብ አገር ናት፤ በአሁኑ ጊዜ ትልልቅ ፋብሪካዎቿ ማምረት በማቆማቸው ምክንያት በአገራችን ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ የዘይት እጥረት ተከስቷል። ይህ ብቻም አይደለም። ራሺያም በተመሳሳይ ፋብሪካዎቿ እያመረቱ ባለመሆኑ ብዙ ነገሮች ከገበያ እየጠፉ ያሉበት ሁኔታ ነው ያለው።

በሌላ በኩል በዚህ ጦርነት ምክንያት ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያዎች በተለይም ወደዩክሬን የሚያደርጉትን በረራ አቋርጠዋል የንግድ እንቅስቃሴውም ተገድቧል። ይህ ጦርነት በዚህ ከቀጠለ በተለይም ምርትን ለዜጎቻቸው የማቅረብ ችግር ሊያጋጥም ይችላል በሚል አንዳንድ ዘይት አምራች አገሮች ምርቶቻቸውን የመያዝ ሁኔታን እያሳዩ ነው። በመሆኑም መሰረታዊ ሸቀጦች በዓለም አቀፍ ደረጃ እጥረት አስከትሏል።

በመሆኑም ይህ ጥላ በአገራችንም እየታየ ነው። ለዚህ ዋናው ምክንያት ደግሞ አብዛኛውን የሸቀጥ ምርታችንን ከውጭ የምናስገባ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ገቢ ምርቶች አቅርቦት ላይ ጫና ይፈጥራል። በመሆኑም መሰረታዊ ችግሮቹ እንግዲህ ዓለም አቀፍ ጫናው እንዳለ ሆኖ ኢትዮጵያ ሰፊና ትልቅ አገር ስትሆን ፍላጎቶቿም በዛው ልክ ሰፊ ናቸው። ይህንን ፍላጎት የሚመጥን የአቅርቦት ችግር አለ።

በሌላ በኩል የአገር ውስጥ የገበያ እንቅስቃሴ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተከትሎ በተፈጠሩ በርካታ ኬላዎች ምክንያት አላስፈላጊ ቀረጥ እየበዛ በመምጣቱ በምርቶች ላይ የተጋነነ ዋጋ ጭማሪ እየታየ ነው። ሌላው ስር የሰደደ ሌብነት አለ፤ ለዚህ ሌብነት ደግሞ የምርት እጥረት መኖሩ ለሌቦች ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ በየደረጃው ባሉ የመንግሥት መዋቅሮች ውስጥም የሚታይ በመሆኑ ይህንንም መፍታት ያስፈልጋል ፤ ሌላው ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ላይ የተከሰተውን የምርት እጥረት ተገን በማድረግና ሊቀጥል ይችላል በሚል አቅራቢዎች ምርቶቻቸውን ደብቀዋል። በመሆኑም በእነዚህና ሌሎች ምክንያቶች የምግብ ሸቀጥ ዋጋ ንሯል፤ የኑሮ ውድነት ከፍ ብሏል።

> በጊዜ ሂደት የገበያውን ሁኔታ እያስተካከልን የነዳጅ የመሸጫ ዋጋ ቢያንስ ከአካባቢው አገሮች ጋር እንዲስተካከል ማድረግ ያስፈልጋል።

ይህንን ለማስወገድ ደግሞ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ሲሆን በዚህም የአቅርቦትን ችግር ለመሙላት በተለይም ከዘይት ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል ተገዝቶ በተለያዩ ምክንያቶች አገር ውስጥ ያልገባ 10 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሊትር ዘይት በተቻለ ፍጥነት ወደ አገር ውስጥ እየገባ ነው።

ሌላው የዓለም የአቅርቦት ሁኔታ እጥረት የሚታይበት ቢሆንም ካለበት ቦታ እንዲመጣ መንግሥት ያለውን ሀብት ቅድሚያ ሰጥቶ መድቦ ተጨማሪ የምግብ ዘይት እንዲገባ ስምምነት ተደርሶ ግዢ እየተፈጸመ ነው። በአዲስ አበባና በአዳማ አካባቢ በተካሄደው ኦፕሬሽን 3 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሊትር ዘይት ተይዞ ወደስርጭት እንዲገባ ሆኗል። በመሆኑም ከዘይት ጋር በተያያዘ ያለው ሁኔታ ይህ ነው።

**ጥያቄ፡- ነዳጅን በሚመለከት በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ እየታየ ያለው የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ አለመረጋጋት በነዳጅ አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል፤ በመሆኑም አሁን ያለውን የነዳጅ አቅርቦት እጥረትና የዋጋ መዋዠቅ ለመቋቋም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ምን እያደረገ ይገኛል?**

**አቶ ገብረመስቀል፡-** ነዳጅ ከዚህ ቀደም ድፍድፉ በርሜል ስድስት ዶላር ነበር። አሁን ግን 106 ዶላር ደርሷል። እነዚህ ሁሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዋጋቸው

# ወቅታዊ

እየናረ ያሉ ነገሮች ኢትዮጵያ ላይ ቀጥተኛ የሆነ ጫናን እየፈጠረ ነው። ይህም ቢሆን ግን መንግሥት ካለው ሀብት የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥቶ ለሕዝቡ መሰረታዊ የሚባሉ የፍጆታ እቃዎችን ለማሟላት ጥረት እያደረገ ነው።

በአሁኑ ወቅት በክልሎች አካባቢ ጉምሩክ የሚያውቃቸው ኬላዎች ካልሆኑ በቀር ሁሉም ኬላዎች እንዲነሱ ሆኗል። በመሆኑም አሁንም ገመድ አስረው መኪና የሚያስቆሙ ከጉምሩክ እውቅና ውጪ ያሉ ሁሉ ሕገወጦች ናቸው።

ሌብነትንም ቢሆን ለመቋቋም ብሎም እንደዚህ አይነት ሰው ሰራሽ የዋጋ ንረትን በሚፈጥሩ አካላት ላይ እርምጃ እየተወሰደ ነው። የሕግ ክፍተቶችንም በደንብ በማየት እንዲስተካከሉ ማድረግ ያስፈልጋል። በየደረጃው ያለው የመንግሥት መዋቅር እየተመሳጠረ አንዳንድ ጊዜ ምርቱ ታች ድረስ የደረሰ ቢሆንም እንኳን ሕዝቡ ጋር እንዳይደርስ በሚያደርጉ ላይ የማጥራት ስራ እንሰራለን። ጠንከር ያለ እርምጃ እንዲወሰድም እንሰራለን። በጠቅላላው የንግድ ሥርዓቱን በማዘመን ከሌቦች ከአሻጥረኞች ለመከላከል በተለይም የስርጭት ሥርዓቱን በዘመናዊ ሁኔታ ማስኬድ ሲስተም መዘርጋት ይጠይቃል። ይህንንም ለመስራት የተለያዩ ጥረቶች ይደረጋሉ።

ነዳጅ ከአጭር ጊዜ አንጻር የአቅርቦት ችግር የለብንም። ምክንያቱም ለተራዘመ ጊዜ የሚቆይ ውል ገብተን ነው የምንሰራው፤ በመሆኑም በተፈጠረው የዓለም ሁኔታም ቢሆን የአቅርቦት ችግር አይገጥመንም። የሚገጥመን የዋጋ ልዩነት ነው። ይህንን የዋጋ ልዩነት መዋዠቅ ለማስተካከል ሁለት መሰረታዊ ውሳኔዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተወስኗል።

አንደኛው እኛ ደሃ አገር ብንሆንም ነዳጅን ከውጭ አገር ከሶስት ቢሊዮን ዶላር በላይ አውጥተን ነው የምናስገባው። ነዳጅ ለኢኮኖሚ ለምርትታማነት ያለውን ፋይዳ በመረዳት የምንሸጠው ደግሞ ከዋጋው ከ 50 በመቶ በላይ ሰብረን ነው። ይህም ቢሆንም ግን ዋጋው ከጎረቤት አገሮች መሸጫ ዋጋ ጋር ተመሳሳይ ስላልሆነ እኛ ጋር 30 ብር የሚሸጥ ናፍጣ አሁን ላይ ጅቡቲ 100 ብር ስለሚሸጥ እኛ ከጅቡቲ የተነሳው ነዳጅ ጫኝ መኪና ተመልሶ ጅቡቲና ሶማሌ ላንድ ነዳጁን እያራገፈ ስለሆነ ዋናው ጉዳይ የነዳጅን ዋጋ ወደ ዓለም አቀፍ ዋጋ ጠጋ ማድረግ ነው። አለበለዚያ እኛ ሁል ጊዜ ነዳጅን በዶላር እየገዛን ዋጋው ከፍ ወዳለ አገር በኮንትሮባንድ እየወጣ ነው። በመሆኑም ይህ ሁኔታ በዝርዝር ተጠንቶ የዋጋ ማሻሻያ ሊደረግ ያስፈልጋል።

ዋጋ ማሻሻያ በሚደረግበት ጊዜ ዝቅተኛው የሕብረተሰብ ክፍል በተለይም ከትራንስፖርት ጋር ተያይዞ እንዲሁም የሚያስከትለውን የኑሮ ውድነት ጫና ለማቃለል የሕዝብ ትራንስፖርት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች የታለመ ድጎማ እንዲያገኙ ውሳኔ ተላልፏል። በመሆኑም በጊዜ ሂደት የገበያውን ሁኔታ እያስተካከልን የነዳጅ የመሸጫ ዋጋ ቢያንስ ከአካባቢው አገሮች ጋር እንዲስተካከል ማድረግ ያስፈልጋል።

ሌላው በተለይ ቤንዚንን ከኢታኖል ጋር በማቀላቀል የምናስገባውን የነዳጅ መጠን በተወሰነ ደረጃ ማሻሻል ይቻላል፤ ይህም በቀጣይ እየታየ የሚሄድ ነው። ነዳጅ ውድ ምርት ነው። እኛ ግን እንደ ውድ ምርት አናየውም። በመሆኑም እያንዳንዱ ተሽከርካሪ ያለው ዜጋ ነዳጅን በቁጠባ መጠቀም መቻል አለበት። በቁጠባ መጠቀም የማንችል ከሆነ በቀጣይ ነዳጅ በኮታ ልንሰጥ የምንችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። በመሆኑም ይህ እንዳይሆን ለነዳጅ የሚወጣውም ገንዘብ የአገሬ ነው በማለት በቁጠባ መጠቀሙ ይሻላል። ከዚህ ባሻገርም ቅዳሜና እሁድ የሕዝብ ትራንስፖርት መጠቀም እንዲሁም የእግር ጉዞን መልመድ ልንገባ ካልነው ችግር ይታደገናል።

ነዳጅ እንደ መሰረታዊ ሸቀጥ መንግሥት የሚቆጣጠረው ነው። ዋጋ ይወሰናል። ማንም ከዛ ዋጋ በላይ ከሸጠ ሕገወጥ ነው። ይጠየቃል። ስርጭቱንም ብንመለከት አዲስ አበባ እንኳን ከሚገባው ነዳጅ 45 በመቶውን ብቻ ነው የሚጠቀመው ፍትሃዊ አድርገን እናሰራጭ ብንል አንዳንድ ቦታ ላይ ነዳጅ ያጥራል። ሌላው ጋር ደግሞ ሳይሸጥ ቁጭ ይላል ፤ በመሆኑም ተጠቃሚን ፍላጎት ያደረገ የነዳጅ ስርጭትን ነው የምንጠቀመው።

> እያንዳንዱ ተሽከርካሪ ያለው ዜጋ ነዳጅን በቁጠባ መጠቀም መቻል አለበት። በቁጠባ መጠቀም የማንችል ከሆነ በቀጣይ ነዳጅ በኮታ ልንሰጥ የምንችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።



ይህ ፍላጎትን ተከትሎ እንዲሄድ እንዴት ነው መቆጣጠር የምትችሉት የሚል ጥያቄ ሊመጣ ነው፤ ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ቁጥጥር የሚካሄደው በየጊዜው ምርመራ ይደረጋል። ዘንድሮ እንኳን በኦሮሚያና ሶማሌ ክልል ላይ አምና ተመሳሳይ ወቅት ከተጠቀሙት ከፍ ያለ የነዳጅ አጠቃቀም ታይቶ ነበር። በመሆኑም ይህንን ከሚመለከታቸው ጋር ተነጋግረን ኮታ ገደብን። ነገር ግን ሶማሌ ክልል ላይ አሁን ካለው የድርቅ አደጋ ጋር ተያይዞ የክልሉ መንግሥት ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ጥቂት ድርቁን ታሳቢ ያደረገ መጠነኛ ጭማሪ ተደርጓል።

**ጥያቄ፦ በግብርና ምርቶች ላይ የሚታየውን ሕገወጥነትና ኮንትሮባንድ ንግድ ምክንያት መንግሥት ማግኘት የሚገባውን ገቢ ከማጣቱም በላይ የአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት በሚፈለገው ደረጃ ላይ ለመድረስ ከፍተኛ እንቅፋት ሆኗል ይህንን ችግር በዘለቄታዊ መልኩ ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ምን ያህል ቅንጅታዊ አሰራር እየተሰራ መሆኑ ቢገለጽ?**

**አቶ ገብረመስቀል፦** በግብርና ምርቶች ኮንትሮባንድ የተነሳ አገራችን የሚገባበትን ጥቅም እያገኘች አለመሆኑ እየተነገረ ነው። ነገር ግን ዘንድሮ ብቻ ከውጭ ንግዳችን ያገኘነው የምንዛሪ መጠን ታይቶም ተሰምቶም የማያውቅ እጅግ በጣም ብዙ ነው። በዚህም 4 ቢሊዮን እንገባለን ብለን እየሰራን ነው፤ እንደምንገባም አመላካች ነገሮች አሉ። በመሆኑም የውጭ ምርታችን ከፍተኛ መሻሻል እያሳየ ነው። ነገር ግን ኢኮኖሚው ባደገ መጠን የወጪ ምርት ገቢ እየመጣ ነወይ ከተባለ አይደለም። ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ምክንያቶች ሊነሱ ይችላሉ፤ ነገር ግን ሕገ ወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ አንዱ ነው።

እነዚህን ነገሮች ለማስወገድ የተለያዩ ሥራዎችን እየሰራን ነው አንደኛው ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት ውስጥ ያልገቡ ምርቶች አሉ። ለምሳሌ ሽምብራ፣ ኑግ፣ ባቄላ፣ ዳጉሳ እና ለውዝ ሲሆኑ እነዚህ ግን ያለሕግና ሥርዓት እንደተፈለገ የሚሸጡና የሚወጡ ምርቶች ነበሩ። ዘንድሮ ግን እነዚህ ምርቶች እንደሌሎች ወጪ ምርቶች ወደአስተዳደር ሥርዓት እንዲገቡ ሆኗል። በመሆኑም በኮንትሮባንድ ማውጣት አይቻልም።

በተመሳሳይ የቁም እንስሳቱንም ቢሆን እንደ ሌሎች ወጪ ምርቶች ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ አልተወሰነላቸውም ነበር ፤ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ስራው አንዴ ወደ ግብርና ሌላ ጊዜ ወደ ንግድ እየመጣ ያልተረጋጋበት ሁኔታ ነበር። በመሆኑም እያንዳንዱ የቁም እንስሳ አይነቱ ክብደቱ ተለይቶ ምን ያህል ገንዘብ ሊያመጣ ይገባል የሚለው ተወስኖ መመሪያ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተገብቷል። ይህ ከሆነ በኋላ በአንድ ወር ውስጥ ከቁም እንስሳት ብቻ 2 ሚሊዮንና ከዛ በላይ ገቢ እየመጣ ነው። ይህ ገቢ ደግሞ በፊት በኮንትሮባንድ ይወጣ የነበረ ገቢ ነው ማለት ነው።

በመሆኑም ሕገ ወጥ ኬላዎች እንዲነሱ ኮንትሮባንድ ላይ ከፍተኛ የሆነ ቁጥጥር እንዲደረግ ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በቅንጅት እየሰራን ነው። ከዚህ ሌላ መላው ሕብረተሰብ በኮንትሮባንድ ላይ ያለውን አመለካከት እንዲያሰፋ በማድረግ ለውጥ ለማምጣት እየተሰራ ነው።

ከውጭ ንግዳችን የምናገኘው ገቢ እያደገ ነው። ነገር ግን በሚፈለገው ልክ ነወይ ቢባል አይደለም። በተለይም ተቋማዊ አቅምን ከመገንባትና አስተሳሰብን ከማሳደግ አንጻር የሚሰሩ ሥራዎች አሉ እነሱንም አጠናክረን እንቀጥላለን።

**ጥያቄ፦ አገራችን ከአገዋ የገበያ እንድትሰረዝ መደረጉ ምን ዓይነት ተጽዕኖ አሳደረ? ይህንን እድልስ የሚተኩ ሌሎች አማራጮች እየታዩ ነወይ ?**

**አቶ ገብረመስቀል፦** አገዋ በዓመት እስከ 258 ሚሊዮን ዶላር ከጨርቃጨርቅና ጫማ በመላክ የምናገኘውን ገንዘብ ነው። ከጥር 1 ቀን ጀምሮ ያጣነው። ይህንን የአሜሪካን መንግሥት ከግምት እያስገባ አስተያየት እንዲያደርግ በኤምባሲም በኩል ሥራዎች እየተሰሩ ነው። ተስፋ አልቆረጥንም። ከዛ በተረፈ ግን በተለይም በአውሮፓና በኤዢያ አገሮች ነባር ደንበኞች አሉን ፤ በእነሱ ላይ ትኩረት አድርገን እየሰራን ነው፤ ከዚህ በተጨማሪ ጎረቤት አገሮች የእኛን ጫማ ስለሚፈልጉ አፍሪካ አገሮች ደግሞ ጨርቃጨርቅ ምርቶችን ስለሚፈልጉ እነዚህ ላይ ሰፋ ያለ ስራ እንሰራለን። ጎን ለጎንም ደግሞ አዳዲስ ገበያዎችን የማፈላለግ ነባር ገበያዎችን ደግሞ የማጠናከር ስራዎችን እየሰራን ነው። በቀጣይም ደግሞ ከአሜሪካን ኤምባሲ ጋር እየተነጋገርን ነው።

**ጥያቄ፦ ያለበቂ ምክንያት ዋጋ የሚጨምሩ ነጋዴዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ባለመደረጉ ሕብረተሰቡን ለከፍተኛ የኑሮ ውድነት ሲዳረግ ችሏል። በመሆኑም ከፍተኛ የዋጋ ንረት በታየባቸው የሲሚንቶ ቆርቆሮና ብረት በመሳሰሉ ምርቶች ላይ የዋጋ ማረጋጋት ለማድረግ ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ ገብረመስቀል፦** ከሲሚንቶ ከብረት ከቆርቆሮና ከሌሎች ግብዓቶች ጋር በተገናኘ ሕገወጥነት የሚስተዋልባቸው ነጋዴዎች ላይ እርምጃ እየተወሰደ ነው። ለምሳሌ አሁን ካለው የሲሚንቶ ዋጋ ጭማሪ ጋር በተያያዘ ብንመለከት ችግሩ የተፈጠረው ከምርት አቅርቦት ችግር ጋር በተያያዘ ነው። ዋና ዋና ሲሚንቶ አምራች የሆኑ ፋብሪካዎች በአቅማቸው ልክ እያመረቱ አይደለም። ስለዚህ የምርት አቅርቦት ችግር ተፈጥሯል። ችግሩን ለመፍታት የድንጋይ ከሰል የሚባለው ግብዓት በውጭ አገር እስከ 3 መቶ በመቶ ድረስ ጭማሪ አሳይቷል። በአገር ውስጥ ግን 50 በመቶ ያህል ብቻ ነው ጭማሪ ያሳየው። በመሆኑ የማዕድን ሚኒስቴር የግብዓት ሰንሰለቱን ለማስተካከል ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው።

በዚህም የድንጋይ ከሰልን በብዛት ለማምረት ከውጭም የአገር ውስጥ ባለሀብቱም እንዲሰማራበት ለማድረግ የተለያዩ የማሳመን ስራዎች እየተሰሩ ነው። ሌላው የድንጋይ ከሰል ከሚወጣባቸው አካባቢዎች ምርቱን ለመጫን ከፍተኛ የሆነ የጸጥታም ችግር መኖሩ ከፍተኛ የሆነ ማነቆ ሆኗል። እነዚህ ችግሮች በሲሚንቶ አቅርቦት ላይ ጫና አሳድረዋል። ለጊዜውም የጸጥታ አካላት በየአካባቢው ያሉ የንግድ ቁጥጥር ግብረ ሃይል የንግዱ ማህበረሰብ በጋራ ቁጥጥር ማድረግና ሌባውን ማጋለጥ መቻል አለባቸው።

ብረትም በዓለም ላይም ጨምሯል። ያሉን ፋብሪካዎች መቶ በመቶ እንኳን ቢያመርቱ በአገሪቱ ያለውን ፍላጎት ለማሟላት አንችልም። በመሆኑም ከብረት ጋር በተያያዘ የአገር ውስጥ ፋብሪካዎች እንዲያመርቱ ማድረግ ከውጭም የሚገባበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል። በጠቅላላው እነዚህን ምርቶች በምናነሳበት የንግድ ሕጉ በሚፈቅደው ልክ ሥርዓቱን መቆጣጠር መቻል አለብን።

ከዛ ውጪ ግን ምርቱን በማከማቸትና በመደበቅ ገበያውን በሚያውኩ አካላት ላይ ጠበቅ ያለ እርምጃን በየደረጃው እንወስዳለን።

**ጥያቄ፦ አገራችን እየገጠማት ያለውን ዓለም አቀፋዊ ተጽዕኖ ለመቋቋም ቀጠናዊ ትስስር አቋራጭ መንገድ መሆኑ የሚታወቅ ነው ፤ በመሆኑም ይህንን ሁሉን አቀፍ ለማድረግ ምን እየተሰራ ይገኛል?**

**አቶ ገብረመስቀል፦** የተጀመሩ ስራዎችን በተቻለ ፍጥነት እያስኬድን ነው። በተለይም የአፍሪካ የነጻ የንግድ ቀጠና ሥርዓት ከፈረሙት አገሮች ኢትዮጵያ አንዷ ናት ፤ አሁን ደግሞ ከ5 ሺ በላይ የሚሆኑ እቃዎችን በምን ዋጋና በምን አይነት ጥራት እንደሚቀበሉ ዝግጅታችንን አጠናቀናል ፤ በዚህ ማዕቀፍ ኮሜሳም አለ። በዚህም ላይ ሰፊ ስራ እየተሰራ ነው ያለው። ስለዚህ እነዚህን ስራዎች አጠናክረን የምንቀጥልበት ነው የሚሆነው።

**ስለ ሰጡን ቃለ ምልልስ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስም እናመሰግናለን፡፡**

**አቶ ገብረመስቀል፦** እኔም አመሰግናለሁ

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ኢንዱስትሪ ፓርኩ በጦርነት ማግስት

ፋንታነሽ ክንዴ





ፎቶ፡- በናኦል አየለ

ጦርነት በሰዎች ማህበራዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። ከሕይወት መስዋዕትነት ጀምሮ ማህበራዊና ስነልቦናዊና ቀውስ ይፈጥራል። በአገሪቱ ከአንድ ዓመት በላይ የዘለቀው ጦርነትም በዜጎች ሕይወት ላይ እጅግ አስከፊ ጠባሳ ጥሎ አልፏል።

በጦርነት ቀጠና አካባቢ የነበሩ በርካታ ዜጎች የሕይወት መስዋዕትነት ከፍለዋል። ከቤት ንብረታቸውና ከቀያቸው ተፈናቅለዋል። ስደት፣ ረሃብና ጉስቁልናም ደርሶባቸዋል። ዜጎች በጦርነቱ ከደረሰባቸው ማህበራዊና ስነልቦናዊ ቀውስ ባለፈ በአካባቢው የደረሰው የንብረት ውድመት ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም።

በጦርነቱ ቀጠና ውስጥ በነበሩ አካባቢዎች በርካታ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ወድመዋል። በውድመቱ ግንባር ቀደም ተጠቂ ከሆኑት ተቋማት መካከልም መኖሪያ ቤቶች፣ ፋብሪካዎች፣ የህክምና ተቋማት፣ የትምህርት ተቋማት፣ የዕምነት ቦታዎችና ሌሎችም ይገኙባቸዋል። የጦርነቱ ሰላባ ከሆኑት መካከልም የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ አንዱ ሲሆን የዛሬው ቅኝታችን ትኩረቱን በአሁኑ ወቅት ፓርኩ ከደረሰበት ጉዳት ለማንሰራራት እያደረገ ባለው ጥረት ላይ ያተኩራል።

ፋብሪካው ከደረሰበት ውድመት መልሶ ለማገገም በሚያደርገው ጥረት ውስጥ ገበያ የማጣት ስጋት ከፊት ለፊቱ ተደቅኗል። በፓርኩ የሚገኙ ካምፓኒዎች፣ አብዛኛው ምርታቸውን በአጎዋ አማካኝነት ወደ አሜሪካ ገበያ ይልኩ የነበሩ በመሆናቸውና በአሁን ወቅት ደግሞ ዕድሉ የተዘጋ በመሆኑ የገበያ ስጋት ስለመኖሩ በቅርቡ በኢንዱስትሪ ፓርኩ በተደረገው ጉብኝት ተገልጿል።

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በአፋርና አማራ ክልሎች የፈጸመውን ወረራ ተከትሎ በርካታ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት ባደረሰበት ወቅት ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰባቸው ተቋማት አንዱ ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ነው። እስካሁን በተደረገው ጥናትም ፓርኩ በወረራው ከግማሽ ቢሊዮን ብር በላይ የሚሆን አጠቃላይ ውድመት እንዳደረሰበት ጥናቶች ያሳያሉ።

ጥናቱ አሁንም ያልተቋጨና የቀጠለ በመሆኑ የደረሰው ጉዳት ከፍ የማለት እድሉ ሰፊ ነው። በጦርነቱ ተንቀሳቃሽ የሆኑ ንብረቶች በሙሉ የተዘረፉ ሲሆን፤ ማንቀሳቀስ ያልቻሉትንም በማውደም እንዲሁም ለዘራፊዎች ክፍት በማድረግ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስበት መደረጉን የፓርኩ ሥራ ኃላፊዎች አስረድተዋል።

በአሁን ወቅት አካባቢው ከቡድኑ ወረራ ነጻ መውጣቱን ተከትሎ በተሠራው የመልሶ ማቋቋም ሥራ ፓርኩ ወደ ሥራ የተመለሰ ሲሆን፤ አሁን ላይ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ከባለፈው ሐምሌ ወር ጀምሮ ሰባት ነጥብ ሰባት ሚሊየን ዶላር የሚያወጡ ምርቶችን ወደ ውጭ ለመላክ አቅዶ ከሰባት ነጥብ አራት ሚሊየን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ማግኘቱን የገለጹት የፓርኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አህመድ ሰኢድ፤ ከተገኘው አጠቃላይ የውጭ ምንዛሪ ውስጥ ሶስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላሩ ፓርኩ በመልሶ ማቋቋም ወደ ሥራ ከተመለሰ በኋላ ያገኘው መሆኑን አስረድተዋል።

እንደ ዋና ሥራ አስኪያጁ ገለጻ ፓርኩ በ2014 በጀት ዓመት 13 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት አቅዷ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ላይ በሚገኝበት ወቅት ጦርነቱ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰበት ቢሆንም ካለፉት ሦስት ዓመታት የተሻለ አፈጻጸም ማስመዝገብ ችሏል። ከዚህም ባለፈ የተቀመጠውን ዓመታዊ የኤክስፖርት እቅድ ለማሳካት በቀሪ ጊዜያት ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ውጤት ለማስመዝገብ እየተሰራ ነው።

ፓርኩ ከደረሰበት ውድመት አገግሞ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራ እንዲገባና ውጤታማ እንቅስቃሴ እንዲያደርግ በፓርኩ ውስጥ የሚገኙ ካምፓኒዎች በጎ ምላሽ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው መሆኑን ያስታውሱት አቶ አሕመድ፤ መንግሥትና ሌሎችም ኢንዱስትሪ ፓርኮች አስፈላጊውን እገዛ በማድረጋቸው ምስጋና ይገባቸዋል። ፓርኩ ከጦርነቱ አስቀድሞ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሰራተኞች የነበሩት ሲሆን በጦርነቱ ማግስት ወደ ሥራ የተመለሱት ግን ሁለት ሺ አንድ መቶ ያህሉ ሠራተኞች ብቻ ናቸው። ቀሪ ሠራተኞችን ወደ ሥራ ለመመለስም ካምፓኒዎች በሙሉ አቅማቸው እየሠሩ ይገኛሉ።

አካባቢው ከአሸባሪው የሕወሓት ወረራ ነጻ ወጥቶ ፓርኩ ወደ ሥራ ሲመለስ ካምፓኒዎች ሠራተኞችን እንዲመልሱና በጦርነቱ ምክንያት ሳይከፈላቸው የቆየውን ደመወዝ እንዲከፍሉ ለማድረግ ሥራዎች መሠራታቸውን የሚጠቁሙት አቶ አሕመድ፤ ካምፓኒዎች በጦርነቱ የደረሰባቸውን የንብረት ጉዳት ከግምት በማስገባት የሚያገግሙበት ጊዜ ለመስጠት በማሰብ የሰባት ወራት የሼድ ኪራይ እፎይታ መሰጠቱን አመላክተዋል። ምንም እንኳን የሼዶቹ ኪራይ እፎይታ መሰጠት አገሪቱን በርካታ ገንዘብ የሚያሳጣት ቢሆንም ካምፓኒዎች በደረሰው ጉዳት ተስፋ ቆርጠው ወደ ኋላ እንዳይመለሱና ሠራተኞችም እንዳይበተኑ የተወሰነ ውሳኔ ነው።

በጦርነቱ ከፍተኛ ጉዳት ቢደርስባቸውም በቁጭት ወደ ሥራ መግባታቸውን በፓርኩ የሚገኙ ካምፓኒዎች ሲገልጹ፤ አብዛኛው ምርታቸውን በአጎዋ አማካኝነት ወደ አሜሪካ ገበያ ይልኩ የነበረና በአሁን ወቅት ደግሞ አገሪቱ ከአጎዋ ተጠቃሚነት መሰረዟ የገበያ ማጣት ስጋት ፈጥሮባቸዋል። በኢንዱስትሪ ፓርኩ ከሚገኙ አምራች ኩባንያዎች አንዱ የሴቶች የእጅ ቦርሳ እያመረተ ወደ ውጭ ገበያ የሚልከው የፑንግ ኩንግ ፋብሪካ ተጠቃሽ ነው።

የፋብሪካው የሰው ኃይልና ጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊ አቶ ያሬድ እንዳላማው እንደሚገልጹት፤ ፋብሪካው ከምርቱ ዘጠና አምስት በመቶ የሚሆነውን ኢትዮጵያ የነበራትን ከኮታ እና ቀረጥ ነጻ የገበያ እድል ተጠቃሚነት በመጠቀም ወደ አሜሪካ ገበያ ሲልክ ቆይቷል። አሁን ግን አገሪቱ ከአጎዋ ተጠቃሚነት በመሰረዟ የገበያ እጦት ይገጥመናል የሚል ስጋት ገብቶናል ይላሉ።

ፋብሪካው አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በአማራና አፋር ክልሎች በከፈተው ጦርነት ፓርኩ ላይ ውድመት እስካደረሰበት ጊዜ ድረስ አንድ ሺ አስራ ስድስት ሰራተኞች የነበሩት መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ አሁን ላይ ስምንት መቶ ሰማኒያ የሚሆኑት ሠራተኞች ወደ ሥራ ገበታቸው ተመልሰዋል። ሆኖም ግን አሁን ላይ ከገዢው ምንም አይነት የምርት ትዕዛዝ እየመጣ ባለመሆኑ ስጋት ገብቷቸዋል።

ፑንግ ኩንግ የሴቶች ቦርሳ አምራች ፋብሪካ በጦርነቱ ምክንያት ከአራት መቶ ሺ ዶላር በላይ አጠቃላይ ጉዳት እንደደረሰበት የሚናገሩት አቶ ያሬድ፤ የምርቱ ዋና ገዢ ማይክል ኮርስ ኩባንያ አሜሪካ ስለሚገኝ ድርጅቱ በጦርነቱ ከደረሰበት ጉዳት ባለፈ ኢትዮጵያ ከአጎዋ ተጠቃሚነት እንድትወጣ በመደረጉ አዲስ ትዕዛዝ እየተቀበለ አለመሆኑን ጠቅሷል። በአሁን ወቅትም ቀደም ሲል የተቀበሉትን ትዕዛዝ በማምረት ላይ እንደሚገኙና ተጨማሪ ትዕዛዝ ለማግኘትና ምርቱን ለመላክ የሚወጣውን ወጪ መጋራት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ከገዢው ጋር ድርድር እያደረጉ እንደሆነም ተናግረዋል። ድርድሩ ውጤት የማያመጣ ከሆነ ግን ድርጅቱ የገበያ እጦት ሊገጥመው እንደሚችል ያላቸውን ስጋት አስረድተዋል።

የትራይባስ ብሪጅ ቴክስ ኢትዮጵያ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ አዲሱ ማሞ እንደሚሉት ደግሞ፤ ፋብሪካው ሙሉ ልብሶችን በማምረት በአጎዋ አማካኝነት ወደ አሜሪካ ገበያ ሲልክ ቆይቷል። በአሁኑ ጊዜ ቀደም ብሎ ተቀብለውት በጦርነቱ ምክንያት የዘገዩ ትዕዛዞችን በማምረት ላይ የሚገኙና ኢትዮጵያ ከአጎዋ ተጠቃሚነት በመሰረዟ ምክንያት አዲስ ትዕዛዝ እየተቀበሉ አለመሆኑን አንስተው በቀጣይ አማራጭ የገበያ መዳረሻዎችን ለመፈለግ ጥረት እያደረጉ እንደሆነም አስረድተዋል።

አውሮፓ ላይ የገበያ እድሎች ቢኖሩም ፋብሪካው በግባትነት የሚጠቀማቸው ጥሬ እቃዎች ከውጭ ስለሚመጡ ያለውን ፉክክር ሰብሮ ለመግባት የሚያስችል የዋጋ ተወዳዳሪነት መፍጠር ከባድ ነው። በአሁን ወቅትም ትራይባስ ብሪጅ ቴክስ ኢትዮጵያ በጦርነቱ ምክንያት የሰላሳ ሶስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር ቀጥተኛ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን አቶ አዲሱ አስታውሰው በተጨማሪም በወቅቱ አምርተው መላክ ባለመቻላቸው ተቀብለውት የነበረው ትዕዛዝ ተሰርዟል። በዚህም ከአንድ ሺ በላይ ሠራተኞችን መቅጠር ያስችል የነበረው የማስፋፊያ ሥራን ለማቋረጥ ተገደዋል።

ፋብሪካው የተቋቋመው ምርቶችን ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ በመሆኑ በመንግሥት በኩል መፍትሔዎች ካልተቀመጡ የፋብሪካው ህልውና አደጋ ላይ ሊወድቅ ስለሚችል አሁን ያሉትን ሠራተኞች ይዞ ለመቀጠል አዳጋች መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ይሁንና የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አሕመድ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ከኮታ እና ቀረጥ ነጻ የገበያ እድል ተጠቃሚነት ወይም አጎዋ መሰረዟን ተከትሎ የተፈጠረውን የምርት መዳረሻ ገበያ ማጣት ስጋትን ለመፍታት አማራጭ የገበያ እድሎች እየተፈለገ ነው። አብዛኞቹ የፓርኩ ባለሀብቶች ምርታቸውን በአብዛኛው የሚልኩት ወደ አሜሪካና አውሮፓ በመሆኑ የኢትዮጵያ ከአጎዋ ተጠቃሚነት መታገድ በአምራቾች ላይ ችግር ፈጥሯል። ነገር ግን በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በኩል አማራጭ የገበያ መዳረሻዎችን ለማስፋት እየተሠራ ነው።

ለሦስት ሳምንት ያህል ዱባይ ኤክስፖ ላይ እየተሳተፉ እንደነበር ያስታወቁት አቶ አሕመድ፤ በቆይታቸውም ከዱባይ ባለሀብቶች ጋር ምክክር በማድረግ የገበያ እድል ለመፍጠር ጥረት መደረጉንም ጠቁመዋል። በተጨማሪም ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የተወከለ ቡድን የገበያ አማራጮችን ለማየት በቅርቡ ወደ ሕንድ ማምራቱም ሌላኛው አማራጭ ሊሆን እንደሚችል አንስተው ሙከራዎቹ ውጤት ያመጣሉ የሚል ተስፋ እንደተጣለባቸው አስታውሰዋል። አማራጮችን ለመፈለግ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን ተከትሎ በኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገኙ ካምፓኒዎች በሙከራ ደረጃ ምርቶችን ወደ አውሮፓ ለመላክ አማራጭ የሙከራ ምርቶችን እየሠሩ ይገኛሉ።

ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ እንደ አውሮፓውያን የዘመን ቀመር በ2017 የተገነባ ሲሆን፤ በጂቡቲ ወደብና በኮምቦልቻ ደረቅ ወደብ አቅራቢያ መገኘቱ ተመራጭነቱን ከፍ እንዳደረገው ተነግሯል። ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ በአጠቃላይ አስር ሼዶች ያሉት ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል ዘጠኙ ለባለሀብቶች የተላለፉ ስለመሆናቸው ከፓርኩ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ምንም እንኳን በርካታ መሰረተ ልማቶችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በጦርነቱ የወደሙ ቢሆንም በአሁን ወቅት ጦርነቱ ካደረሰባቸው ጉዳት ማገገም እንዲችሉና በጦርነት ማግስት ወደ ሥራ መግባት እንዲችሉ እየተደረገ ያለው ጥረት አበረታችና ተስፋ ሰጪ ነው። ይሁንና ወደ ምርት የገቡ መሰል ኢንዱስትሪ ፓርኮችን በልዩ ሁኔታ ትኩረት ሰጥቶ በማገዝ በሙሉ አቅማቸው ማምረት እንዲችሉና ሰፊ የሥራ እድል እንዲፈጥሩ ብሎም በቂ ትርፍ እንዲያስገኙ የገበያ መዳረሻዎች ማፈላለግና ማስፋት ለነገ የሚተው ተግባር አይደለም።

# ጎሜ

# ፖለቲካውን የእውቀት እንጂ የዘውግ ቤት አታድርጉት!

ሙሉቀን ታደገ

ሁሌም በማለዳ የሰፈራችን ሰዎች የሚቀሰቅሰው ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ነው። በጠዋቱ ተነስቶ ይጮሃል። በጠዋቱ የጀመረውን ጩኸቱን የሚያቆመው ሲተኛ ብቻ ነው ። ከጩኸቱ ብዛት ልቡ ፈንድቶ አለመሞቱ እያለ ሁሉም የሰፋራችን ሰው በሃዘን ከንፈሩን ይመጣል። ደረቱንም ይደቃል።

ትንሽ የታሪክ እና ፖለቲካ ቀለም የነካው ሰው ይልቃል አዲሴ የሚናገረውን ንግግር የወፈፌ ንግግር ነው ብሎ አያልፈውም። ሐረግ በሐረግ እየተነተነ ይመለከተዋል እንጂ። የሰፈራችን መሪዎች እና ተፎካካሪ ቡድኖች የይልቃል አዲሴን ነቆራ ስለሚጠሉ ይልቃል አዲሴን በፊታቸው ካዩ እንዳይሰድባቸው በማሰብ ፊታቸውን አዙረው መሄድን ይመርጣሉ።

አንድ ቀን የእድራችን መሪ የሆነውን አቶ መሐመድ ይልማ የሰፈራችን ሰላም እና እድገት በማስመልከት እንዲሁም የእድራችንን ወርሃዊ ስብሰባ ለማካሄድ በማሰብ ከገበያው መካከል ባለው ትልቅ ዋርካ ስር ሕዝቡን ሰበሰበ። ተሰብሳቢዎችም ከዋርካው ስር ለዘመናት ከማይጠፉት ድንጋዮች ላይ አቧራቸውን በቅጠል እያራገፉ ተቀመጡ። በዚህ ጊዜ ስብሰባውን ለመታደም ማን ቢመጣ ጥሩ ነው ፤ ይልቃል አዲሴ !። ይልቃል አዲሴ መሐመድ ይልማን ፊት ለፊት አገኘው። መሐመድ ይልማ የእድሩን ወርሃዊ ስብሰባ አቋርጦ አይሄድ ነገር ችግር ነው። የይልቃል አዲሴን ስድብ እና ነቆራ እያዳመጠ አይቀመጥ ነገር ችግር ነው። ሕዝብን ሰብስቦ ምንም ሳይሉ መበተን ችግር ስለሆነበት እየተሽማቀቀም ቢሆን ስብሰባውን አስጀመረ። የፈሩት ይደርሳል፤ የጠሉት ይወርሳል ማለት ይሄ አይደል።

እንደተለመደው አቶ መሐመድ የእኛን ሰፈር ሰው የሚደልልባቸውን ቃላት ተጠቅሞ ጎሳችን በቋንቋው እንዲማር፣ እንዲዳኝ ብሎ ሲጀምር ይልቃል አዲሴ በጩኸት ንግግሩን አቋረጠው። ሁሉም የእድሩ አባላት ፊታቸውን ወደ ይልቃል አዲሴ አዞሩ። ይልቃል ንግግሩን እንዲህ ብሎ ጀመረ፤ ብልህን ሰው ለማሞኘት መሞከር ትርፉ ትዝብት ነው። ዛሬም እንደዚህ ቀደሙ ጉራህን ቸርችረህ ልትሄድ ነው። አልፈቅድልህም ! ጉራውን ተወውና የእድሩ እና የሰፈራችን ሰው ምንድን ነው የሚፈልገው ብለህ ጠይቅ ። መጀመሪያ አንተ እና ጓደኞችህ ሕዝቡን ተረዱት። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሕዝብ የተቸገረው በልቶ ማደር ነው። ብሄር፣ ጎሳ ወዘተ ምናምን አያስፈልገውም። ከምግብ እና ከምግብ ውጭ ሌላ ምንም አትበሉን። በልተን ስለምናድርበት ስልት እና ብልሃት ብቻ አቅጣጫ ጠቁሙን። በረሃብ ልናልቅ ነው !

ወገቡን እከክ እያደረገ ይልቃል ንግግሩን ቀጠለ፤ ከመቶ አመታት ወዲህ ሰፈራችንን ባስተዳደሩ አባቶቻችን የተጀመረ እና አሁን ላይ ያሉ የእኛ ሰፈር መሪዎች እንደጥሩ ነገር ተቀብለው የሚያስሄዱት አንድ ነገር አለ። ይህም ምንድን ነው፤ ሰፈራችን ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቅረፍ ከሰፈራችን ባህል፣ ወግ፣ ሃይማኖት፣ አስተሳሰብ፣ ስነ ልቦና ወዘተ በመነሳት ፖሊሲዎችን እና እስትራቴጂዎችን ከመቅረጽ ይልቅ በባህል፣ ወግ፣ ሃይማኖት፣ አስተሳሰብ፣ ስነ ልቦና ወዘተ ምንም የማንመሳሰላቸው የአውሮፓ እና የኤዥያ አገራትን የፖለቲካ ፍልስፍናን መስመር በመስመር በመኮረጅ ወይም ቀድቶ በማምጣት ለአገራችን ህግ ማድረግ ይቀናቸዋል ። ለምሳሌ የ1923ቱ ህገ መንግስት ከጃፓን የተቀዳ እንደሆነ ይታወቃል። የ1960ዎቹ ተማሪዎቹ የትግል መርህ እና ስትራቴጂዎች የተቀዱት የኮሚኒስት ፍልስፍና መነሻ ማህጸን ከሆነችው ራሺያ ነው።

የ1960ዎቹ ፖለቲከኛ ነኝ ባይ ወግ ጠራቂዎች አንዳቸውም የኢትዮጵያን ሕዝብ ችግር መነሻ ምንድን ነው? የሚለውን አልተረዱም። ፋብሪካ የሌላትን አገር በምናባቸው ከበለጸጉ አገራት ጋር በማስተካከል «ላባደር እና ወዛደር» የሚሉ ቃላትን በመተንተን ወግ ይጠርቁ ነበር። አሰሪ እና ሰራተኛ በሌላባት አገር ለወዛደር እና ለላባደር መብት እንታገላለን አሉን። በሌለ ነገር እየተነታረኩ ጊዜአቸውን ማባከናቸው አልቆጭ ብሎአቸው እርስ በርስ በመገዳደል የአገሪቱን የሰው ኃይል እና ንብረት ማጥፋት ስራዬ ብለው ተያያዙት። ይሄም እስካሁን አገሪቱ ለገባችበት ምስቅልቅል ዋናው ምክንያት ሆኖ እናገኘዋለን።

በንጉሱ ዘመንም ሆነ እስከዛሬ ድረስ በአገሪቱ በሚገኙ ቢሮዎች አርሶ አደሮች ተቀጥረው ሲሰሩ ታይቶም፤ ተሰምቶም አይታወቅም። በንጉሱ እና በደርግ ዘመን እንኳን አርሶ አደር የሚሰራበት ቢሮ ሊኖረን ይቅርና የተማሩት አካላት እንኳን የሚሰሩባቸው ቢሮዎች ባለመኖራቸው የዳኝነት ስነ ስርዓት እንኳን የሚካሄደው በዛፍ ጥላ ነበር። እውነታው ይህ ሆኖ እያለ የ1960ዎቹ ትውልድ ከምዕራባዊያን የሰሙትን ቋንቋ በቀጥታ ገልብጠው ወደ አገራችን በማምጣት ስሙን የማይጽፍን አርሶ አደር በቢሮ እንደሚሰራ አድርጎ ለራሳቸው በመንገር ለአርሶ አደሩ ቢሮክራሲ የሚል ታርጋ ለጠፉለት። በቢሮክራሲ ስምም መሬቱን ነጠቁ። ከእርስቱም አፈናቀሉት። የማይችሉትን ፖለቲካ እያነኮሩ የጭቁኑን የአርሶ አደር ልጆችን ሜዳ ላይ በተኑ።

በአገራችን የፖለቲካ ማሳ ውስጥ የበቀሉ አረሞዎች ከምዕራባዊያን ቃላትን እየተዋሱ አገርን የማተራመስ ዛራቸው አርጅቶ ከመቃብር አፍፍ ላይ ሲደርስ ተመልከተን እፎይ ልንል ነው ብለን ስናስብ አሁን ላይ ደግሞ የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከመገንጠል በሚል ሌላ አጀንዳ በማምጣት ለሺህ ዘመናት አብሮ እና ተካበብሮ የኖረን ሕዝብ ለማባላት ላይ ታች ሲኳትኑ እያየን ነው። ከእነኚህም መካከል አንዱ አቶ መሐመድ ይልማ ነው።

የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ የብሔር ፖለቲካ አራማጆችም እንደ ላባደሩ እና ወዛደሩ እንዲሁም ቢሮክራሲ የሚባሉት የፖለቲካ ፋሽኖች መጥፋታቸው የማይቀር ነው። እነኚህ ፖለቲከኞች መርከብ ውስጥ የተደበቁ አይጦች አይነት ናቸው። መርከብ ውስጥ ተደብቀው የሚራቡ አይጦች መርከቡ በሰመጠ ጊዜ መውጣታቸው የማይቀር ነው።

ይልቃል ንግሩን ቀጠለ፤ ኢትዮጵያ የቃል ኪዳን ምድር መሆኗን የዘነጉ በብሔር ስም እየነገዱ ኢትዮጵያን በብሔር ስም ሊበታትኗት የሚራኮቱ ፖለቲከኛ ነኝ ባይ ወግ ጠራቂዎች ስመለከት፤ ሰማይ እንደሚታየው ቅርብ መስሎአቸው ሊመቱት ድንጋይ ሽቅብ እንደሚወረውሩ ህጻናት ይመስሉኛል። መቼም የማይሆን ምኞት!

በእርግጥ የዘውግ ፖለቲካ ፍቅርም፣ ሃይማኖትም ምንም አያውቅም። ሰዎችን ከሰውነት አውጥቶ እብድ የሚያደርግ እና አንዱን ከአንዱ በጥርጣሬ አስተያየት የሚያባላ በውስጡ አጋንቶች የሰፈሩበት የፖለቲካ መቆመሪያ ማሽን ነው። ይሁን እንጂ የቃል ኪዳኗን ምድር ኢትዮጵያን በብሔር ግጭት ለማጥፋት መሞከር ከቤርሙዳ ትርያንግል የገባችን መርከብ ለማውጣት እንደመሞከር ነው።

በዚህ ወቅት ሁሉም በዋርካው ስር የተገኘው ተሰብሳቢ ለወፈፌው ይልቃል አዲሴ አጨበጨበ። አቶ ሙሐመድ በጭንቀት አይኑ ፈጠጠ። «ሕዝብን በተፈጥሮው ተለዋዋጭ ነው ፤ ሕዝብን ለማሳመን ቀላል ቢሆንም በእምነቱ ማግኘት ግን በእጅጉ አዳጋች ነው።» የሚለውን የኒኮሎ ማኪያቬሊን ፍልስፍና አስታወሰ። በሕዝቡ የነበረውን ተቀባይነት ያጣው አቶ መሐመድ ይልቃል አዲሴን በጠባቂዎቹ ተደብድቦ እንዲባረር አዘዘ። ሕዝቡም እሱን የምትደበድቡት እኛን ጨርሳችሁ ነው ብሎ በአንድ ላይ ተነሳ። በዚህ ጊዜ አቶ መሐመድ ሕዝቡን መልሰው ማታለል ያዙ።

ሕዝቡም ይልቃል አዲሴ ንግግሩን ካላስጨረሳችሁት እኛ የእናንተን ዲስኩር ተቀምጠን አናደምጥም አለ። አቶ መሐመድም እየጨነቃቸውም ቢሆን ወፈፌው ይልቃልን እንዲናገር ፈቀዱ።

ይልቃል አዲሴ ሕዝቡ ያስገኘለትን እድል ለመጠቀም ጉሮሮውን ጠረግ ጠረግ እያደረገ ንግግሩን ቀጠለ። እንድናገር ሕዝብ ከፈቀደለኝ የእኛ ሰፈር ገዥዎች ሁለንተናዊ ባህሪ ከኒኮሎ ማኪያቬሊን አስተሳስብ ጋር እያገናኘሁ አብራራለሁ አለ። ከኒኮሎ ማኪያቬሊን ፍልስፍናዎች አንደኛው እና ብቸኛው የወደድኩለት «ገዥዎች አገዛዛቸውን መመስረት ያለባቸው በረቂቅ አይነት አሰራር ሳይሆን ታሪካዊ ሃቅን በመመርመር ነው ! » የሚለውን ነው። ስለእውነት ይህን የኒኮሎ ማኪያቬሊን ፍልስፍና የሚያዳምጥ አንድ ሰው ቢኖር ኖሮ የእኛ ሰፈር ከብሔር እና ከጎሳ ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ ችግሮች አይኖሩም ነበር። ይሁን እንጂ መሪውም፣ ተመሪውም እንዲሁም ተፎካካሪ ፓርቲዎችም እውነተኛውን የአገራቸውን ታሪክ ከመመርመር ይልቅ ሴራን እንደ ብልሃት ስለሚቆጥሩት በሚፈጠሩት ሴራ ረሃባችንን በአግባቡ እንዳናስበው እያደረጉን ነው። ይህ የማኪያቬሊን አስተሳሰብ ስለእውነት ሁሉም ወግ ጠራቂ ፖለቲከኛ ነኝ ባይ በትክክል ተገንዝቦ የፖለቲካው መርህ ሊያደርገው ይገባል።

ነገር ግን መሪዎቻችን እና የማህበረሰብ አንቂዎቻችን እንደለጋስነት ራስን የሚጎዳ ነገር የሚለውን የማኪያቪሊን አስተሳሰብ ሳያላምጡ ጨልጠው የዋጡ ይመስለኛል። ይህን ስል በአመክንዮ እንጂ በግብዝነት አይደለም። ለምሳሌ አቶ ካሳሁን ጎይቶም የተባለው ሰው በተፈናቃይ አርሶ አደርነት ስም የሰፈራችንን መውጫ መግቢያ ግጥም አድርጎ እንዲያጥር ያደረጉት መሪዎቻችን እና ተፎካካሪዎቻቸው ናቸው። ምክንያቱም ተፈናቃይ የተባለው አርሶ አደር በስሙ ከወሰደው ግማሹን መሬት በጉቦ መልኩ ለእነሱ ስለሚሰጣቸው ነው።

ሌላው የእኛ ፖለቲከኞች የእውነት የማኪያቬሊን ተከታዮች ስለመሆናችሁ ማሳያው ደግሞ አሁን ላይ በእኛ ሰፈር ባለፋብሪካዎች ባለሰልጣናት እና ተፎካካሪዎች ናቸው። አስመጭ እና ላኪዎችም እነሱ ናቸው። እነኚህ አካላት ከራሳቸው ትርፍ ውጭ ሌላው ረሃብ ቅንጣት ያህል አያስጨንቃቸውም። የሰረቁት እንዳይታወቅባቸው ለመጡበት ጎሳ ተቆርቋሪ በመመሰል የጎሳ ግጭት ፈጥረው ድሃውን ያጫርሳሉ። ሌብነታቸውንም በጎሳዎች እልቂት ይደብቃሉ።

ባለስልጣናት አምባገነን ህሊናቸው የጎደፈ ከሆነ ለወንጀለኛ ጠበቃ እንደሚሆኑ እና ህሊናቸው ንጹህ ከሆነ ደግሞ ለወንጀሎች ቀጭ እንደሚሆኑ ይታወቃል። አሁን ላይ በእኛ ሰፈር ግን ማን አምባገነን ማን ንጹህ እንደሆነ መለየት አቅቶናል። ማን በማን እንደሚጠየቅ ግራው ግብቶናል! ከዚህ በፊት ገዥ እና ተፎካካሪ ፓርቲዎችን አንዱ የአንዱን ችግር እየነቀሱ ያሳዩን ነበር። አሁን ግን የአንዳቸውን ወንጀል አንዳቸው ማጋለጥ ሲገባቸው አንዳቸው የአንዳቸውን ችግር ሲሸፋፈኑ ስንመለከት ባለትዳር ውሽማማቾችን ያስታውሱን ይዘዋል እያለ እየተናገረ እያለ በትምህርቱ ጎበዝ እንዲሆን አብሾ የተሰጠው ቀዥቃዣው ማስረሻ ዲባባ ማንም ሳይፈቅድለት ከተሰብሳቢዎች መካከል በመነሳት ለይልቃል አጨበጨበ። የራሱንም ንግግር ጀመረ።

ማስረሻ ዲባባ እንዲህ ሲል ጀመረ ፤ ኢትዮጵያን እናጥፋት በማለት ለሚታወቀው የኦስትሪያው ዲፕሎማት የሮማን ፕሮቻስኪ ሌጋሲ አስቀጣይ፤ ባልተጠራችሁበት አቤት ባይ ገዳይ አስገዳይ ጎሰኞች እኛን የቸገረን ነገር በልቶ ማደር ነው። ስለእውነት ለእኛ የምታስቡ ከሆነ እንዴት በልተን እንደምናድር በር ዘግታችሁ በደንብ ተወያዩ። ስትፈልጉም ተደባደቡ። ነገር ግን ለራሳችን በራሳችን ለችግራችን መፍትሄ ለማፈላለግ የምናደርገውን እሩጫ እናንተ በምትፈጥሩት የጎሳ ግጭት አታጨናግፉቡን ሲል በንዴት ጦፎ ተናገረ።

> ለእኛ የምታስቡ ከሆነ እንዴት በልተን እንደምናድር በር ዘግታችሁ በደንብ ተወያዩ። ስትፈልጉም ተደባደቡ። ነገር ግን ለራሳችን በራሳችን ለችግራችን መፍትሄ ለማፈላለግ የምናደርገውን እሩጫ እናንተ በምትፈጥሩት የጎሳ ግጭት አታጨናግፉቡን

ሃጢያትና ትዕቢት ለእውር ህሊና ለመጀመሪያ ጊዜ ጣፋጭ ናቸው። ቆይተው ግን የሚያስከትሉት ጦስ ከኮሶም የሚመር ነው። አሁን ላይ በብሔር ስም ለመነገድ የምትሞክሩ በአገራችን የፖለቲካ ማሳ ውስጥ የበቀላችሁ እንክርደዶች፤ ዛሬ ላይ ራሳችሁን ስንዴ ስላስመሰላችሁ እንክርዳድነታችሁ ተደብቆ ይቀራል ማለት አይደለም። እንክርዳድ መሆናችሁ ሲታወቅ ሁሉም ይደፋችኋል።

ማስረሻ ንግግሩን ቀጥሎ መልካም ሰው ቢሞትም ቢኖርም ሊደርስበት የሚችል ጉዳት የለም። ጥሩ ነገር ለመስራት ሞክሩ። ጥሩ የሰራ በምድርም በሕዝብም ይወደዳል። በሰማይም ከፈጣሪው ዛሬ ፈረሰብኝ ፤ ነገ ፈረሰብኝ ብሎ ከማይጨነቅበት ዘላለማዊ የሆነ ማንም የማይነጥቀው ጽዱ እና ጽኑ ካርታና ፕላን ያለው እንዲሁም ግንባታው ያለቀለት ቦታ ይሰጠዋል ብሎ ወደ መቀመጫው ሲመለስ ሕዝቡም በጭብጨባ ተቀበለው።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## የሰዓሊያኑ ጥምረት ለስዕል ጥበብ ዕድገት

**ተገኝ ብሩ**

ሰዓሊ በቀለሙ ዓለምን ይተረጉማል። በብሩሹ ስለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ግኝቶች ሁሉ በተገለጠለት ጥልቀት ይገልፃል። ስዕል ከፍ ያለ ክህሎት ከነጠረና ጥልቅ ሀሳብ ጋር ተዋህዶ በአንድ ገጽ የሚታይበት ጥበብ ነው። ከሌሎች የኪነጥበብ ዘርፎች ቀዳሚ የኪነ ጥበብ ዘርፍ መሆኑ የሚነገርለት ስዕል የታሪክ አሻራን በጉልህ አድምቆ የማሳየትና ዘመናትን ተሻግሮ የመታየት አቅሙ ከፍተኛ ነው።

ሸራን ወጥረው ቀለምን አዋህደውና የታያቸው ረቂቅ ሀሳብ በብዙ የሚገልፁት ሰዓሊያን የኪነ ጥበቡ ድምቀቶች ናቸው። እነዚህ ልዩ ጥበበኞች በተናጥል ከሚያደርጉት ጥረት የሚያገኙትን ለውጥና ውጤት ይበልጥ ከፍ ለማድረግ በማሰብ ጥምረትን እንደ አንድ መንገድ ይወስዱታል። የኢትዮጵያ ሴት ሰዓሊያን ማህበርም ለዚሁ ጥምረትና አብሮ መስራት ተሰባስቦ የጋራ አላማ ለማሳካት የሚደረግ ጥረት አንዱ ማሳያ ነው። በዛሬው የዘመን ጥበብ ገፃችን የማህበሩ ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴ ለመዳሰስ ወደናል መልካም ንባብ።

በአገራችን የስዕል ጥበብ ቀድሞ የመጀመሩ ያህል ዛሬ ካለበት ደረጃ ጋር ሲነፃፀር አዝጋሚነቱ ፍንትው አድርጎ ያሳያል። አልያም በሚፈለገው መልኩ አድጎና ሰዓሊው ተጠቃሚ አድርጎ መጓዝ አልቻለም። በእርግጥ ስዕል ጥበብ እጅግ ከፍተኛ ፋይዳ ያለውና በኪነጥበባዊ ጠቀሜታው የጎላ ቢሆንም የጥቅሙ ያህል እድገቱ የተፋጠነ አይደለም። ለዚህ ደግሞ በዘርፉ የሚስተዋለው ችግር ለእድገቱ ማነቆ ተደርጎ ይወሰዳል።

በዘር የሚታዩ ችግሮችን በጋራ በመቋቋም የተሻለ ስራ ለመስራትና የስዕል ጥበብ ለማሳደግ የሚተጋው የሴት ሰዓሊያን ማህበር የተመሰረተው በ1988 ዓ.ም ነው። ከዘርፉ ከባድነትና ካሉበት ውስብስብ ችግሮች አንጻር ለየብቻ ከመጋፈጥ በጋራ በማህበር ተደራጅቶ መስራት መፍትሄ ነው ብሎ የተደራጀው የኢትዮጵያ ሴት ሰዓሊያን ማህበር፤ በሰዓሊ መምህር እመቤት አወቀ ሀሳብ አመንጪነት ነው የተቋቋመው። ማህበሩ ሴት የስዕል ባለሙያዎችን በጋራ በማደራጀት በዘርፉ ተወዳዳሪና በጎ ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆን እንዲችሉ የማድረግ አላማ ሰንቋል።

ማህበሩ ይህ ታላቅ አላማ በመያዝ ዛሬ ላይ ከስዕል ትምህርት ቤት ወጥተው ወደ ስዕል ሙያ መቀላቀል ለሚፈልጉ ሴቶች መንገድ አመላካች፣ ልምድና ተሞክሮን አጋሪ፣ የጀመሩትን አዲስ ስራ ወደ ሕዝብ ማቅረቢያ ምቹ ሁኔታ ፈጣሪ ሆኗል። አንጋፋና ወጣት ሴት የስዕል ባለሙያዎችን ያቀፈው ማህበሩ በሚያደርጋቸው ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ በአገሪቱ የስዕል ጥበብ ላይ የራሱን አሻራ በማሳረፍ ላይ ይገኛል።

ሴት ሰዓሊያኑ ማህበር መስርተው በጋራ መስራታቸው ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያስገኘላቸው ቢሆንም ያለሙትን ለማሳካት በስዕል ሙያ ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮች ፈተና ሆኖባቸዋል። ሴት ልጅ ካለባት ድርብ ኃላፊነት በተጨማሪ ያላትን ተስጥዖ ለማውጣት እንድትችል ትልቅ አስተዋፅኦ እያበረከተ መሆኑን የሚናገሩት የማህበሩ ፕሬዚዳንት አርቲስት ስናፍቅሽ ዘለቀ ዓላማው ለማሳካት ብዙ ጥረቶችን እያደረገ መሆኑን ያስረዳሉ።

ሴት ሰዓሊያን ከተቋማት ጋር በመነጋገር የስዕል ስራዎቻቸው የሚያቀርቡበት መድረክ በማዘጋጀት ከሕዝብ ጋር እንዲገናኙ የማድረግ ስራ እየሰራ እንደሆነና የሚፈለገውን ያህል ባይሆንም በዚህም ሰዓሊያኑ ተጠቃሚ እንዳደረገም ይናገራሉ።

በተለይ ሴቶች የመስራት አቅም እያላቸው በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ለሕዝብና ለራሳቸው ማበርከት የሚችሉትን እንዳይወጡ የሚያደርጋቸውን ምክንያቶች በመቅረፍ በአንድ ላይ ሆነው ለጠንካራ ስራ እንዲበቁና ለኪነጥበቡም አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያደርጋል። ማህበሩ በዚህ ሁሉ ጥረቱ የሚፈልገውን ማድረግ እንዳይችል ጋሬጣ የሆኑበት ችግሮች መኖራቸውም በማሳያነት ያነሳሉ።

ከተመሰረተ ከ24 አመት በላይ የሆነው ይህ ማህበር ዛሬ ድረስ ቋሚ የሆነ የሰዓሊያኑ መገናኛና መቀመጫ ቢሮ፣ የሰዓሊያን የጋራ መስሪያና አውደ ርዕይ ማሳያ ቦታና



ለስዕል ጥበብ የሚረዱ የተለያዩ ግብዓቶች የሚያገኙበት መንገድ የለውም። በዚህም በዘርፉ ነጥሮ ለመውጣትና የማህበርተኞችን አቅም ለማሳደግ የዘርፉ ችግሮች ፈተና እንደሆነባቸው ይገልፃሉ።

የማህበሩ አባል የሆኑ ሴት ሰዓሊያን ስራዎቻቸው በተለያየ መንገድ በራሳቸው በግል ጥረትና ምቹ ባልሆነ ሁኔታ የተሰራው ስዕል ማሳያ ቦታ በማጣትና የማህበሩ አባላት ይህን ችግር ተቋቁመው የተሰሩት ስራ ገበያ ማጣት የማህበሩ ዋንኛ ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው።

በዓመት ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ በስዕል አውደ ርዕዮች፣ መደበኛ የስዕል ማሳያና መሸጫ ጋለሪዎችና በሚዘጋጁ በልዩ ልዩ መሰል መርሀ ግብሮች ላይ የማህበሩ አባላት ስዕልና የእደ ጥበብ ውጤቶችን ለሕዝብ ያቀርባሉ። እጅግ ውስን በሆነ ቦታና ጊዜ መቅረቡ ደግሞ ተደራሽነቱን ይቀንሰዋል። ሰዓሊው በአዳዲስ ፈጠራ ሀሳቦች መሪነት የሚያዘጋጀው ስዕል ቋሚ የሆነ ማሳያና መሸጫ ቦታ አላገኘለትም። ይህ ችግር የማህበሩ አባላት የተሻሻሉ አዳዲስ ስራዎችን ሰርተው ወደ ሕዝቡ ማቅረብ እንዳይችሉ አድርጓቸዋል።

ሰዓሊ፣ የስዕልና ግራፊክስ ዲዛይን መምህርና የማህበሩ አባል የሆነችው ወይዘሮ ሩት አድማሱ የሴት ሰዓልያን ማህበር ለ5 አመት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርታለች። ስዕል የሰዎችን ውስጣዊ ጥልቅ ሀሳብ ማሳያ ልዩ ጥበብ መሆኑንና በአንጻሩ ግን ጥበበኛው በሚፈለገው መልክ ተጠቃሚ እንዳልሆነ ትገልፃለች።

የስዕል ጥበብ እንደ አገር ሲታይ በግለሰብ ደረጃ እድገቱ እጅግ አስገራሚ የሆነ ለውጥ እንዳለው የምትገልጸው ሩት ይህ በሁሉም መሰባሰቦች ውስጥ እንዲታይ ግን በዘርፉ የሚታዩ ችግሮች መቅረፍ ይገባል። ስዕል ማበርከት የሚገባውን የላቀ ጠቀሜታ እንዲሰጥ ሁኔታዎች ምቹ መሆን አለባቸው የምትለው ሰዓሊና መምህርትዋ ሩት ችግሮቹ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያዊያን ጥበበኞች ናቸው። ለዚህ ማሳያው የቀደሙ አባቶቻችን የጥበብ አሻራቸው ያሳረፉባቸው አክሱም፣ ላሊበላ፣ፋሲል ግንብ፣ በእምነት ተቋማትና ታሪካዊ ቦታዎች ላይ በልዩ ልዩ ቀለማት ተስለውና ተቀርጸው ዛሬ ድረስ የሚያስደምሙ ስራዎቻቸው ማስረጃ ነው።

ስዕል በቂ የሆነ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ እንዳይሰጥ እንዲሁም መሰል የስዕል ማህበራትና ሳዕሊያን እንዳይጠቀሙ ያደረገበት ምክንያት ሩት ታስረዳለች። በአገር ደረጃ ለስዕል ጥበብ ትኩረት ተሰጥቶ አለመሰራቱ፣ ለስዕል ስራ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ላይ የበዛ ቀረጥ መጣሉ፣ የስዕል ማሳያ ቦታዎች በቂ አለመሆንና አሁን ላይ እየተገነቡ ያሉ ፓርኮች ላይ ያሉ ጋለሪዎች ለሙያተኛው ምቹ በሆነ መልኩ ስራዎቹን እንዲያሳይና እንዲያቀርብ ዕድል አለማግኘቱ ወይም ለሙያተኛው ምቹ ሁኔታ አለመፈጠሩ ዋንኛ ምክንያቶች ናቸው።

ማህበረሰቡ ለስዕል ስራ ያለው አተያይም ሌላው ቀጥተኛ ባይሆንም በስዕል ሙያ ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪው ጉዳይ ነው። ሰዓሊ እራሱን የጣለ፣ ፀጉሩን ያንጨባረረ፣ ስለ ሰዎችና የሚኖርበት ዓለም ጉዳይ የማይሰጠውና ተራ ሕይወትን የሚመራ አድርጎ በተሳሳተ መልክ ማሰቡ በሚዲያ ተፅዕኖ የመጣ እንጂ እውነታው ሌላ መሆኑን ሙያተኞቹ ይገልጻሉ። በምናያቸው ድራማዎች፣ ፊልሞችና የስነ ጽሁፍ ውጤቶች ሰዓሊያን የሚሳሉበት ገጸ ባህሪ ህብረተሰቡ ሙያውን በተሳሳተ መንገድ እንዲረዳው አድርጎታል።

የኢትዮጵያ ሴት ሰዓሊያን ማህበር ፕሬዚዳንት ስናፍቅሽ ዘውገ፣ ስዕል ጥበበኛ እጆች የታደሉ ባለሙያዎች የሚገኙበት ዓለም መሆኑና ለዚህ ትልቅ መስክ የሚገባውን ሊደረግለት እንደሚገባ ያነሳሉ። የስዕል ታላቅነት ትልቅ ደረጃ በተለያየ መልኩ ይንፀባረቃል የሚሉት ፕሬዚዳንትዋ በማሳያነት በአገራችን ብሎም በዓለም ታዋቂ የሆኑትን የጥበብ ሰው እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ይጠቅሳሉ።

ዘመን ተናጋሪና ታሪክ አስረጂ የሆነውን የስዕል ጥበብ ለማሳደግና ማህበረሰቡ ለስዕል ጥበብ የሚሰጠው ክብርና ፍቅር ከፍ እንዲል ከትምህርት ቤት ጀምሮ ህጻናት የስዕል ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ ቢቻለልና በስዕል ጥበብ ትልቅ ቦታ የደረሱ ኢትዮጵያዊያንን የማስተዋወቁ ስራ ቢሰራ መልካም መሆኑንም ይነገራል።

ለሕዝብ ጠቃሚ የሆነውን ጥበብ ለሚያፈልቀው ሰዓሊ የሚገባውን ማግኘት ይገባዋል የሚል የጸና እምነት አላቸው። ጥበብ ለሽያጭ ተበሎ የሚከወን ወይም የሚሰናዳ ባይሆንም የጥበበኛው ህያውነት የሚያረጋግጡ ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸው ግድ ይላል። አንድ ሰዓሊ ስዕል መተዳደሪያና የገቢ ምንጩ ነውና ሕይወቱን ለመምራትና የተሻሉ ስራዎችን ሰርቶ ለህዝብ ማቅረብ እንዲችል ቀድሞ ያቀረባቸው ስራዎቹ ሊሸጡለትና የድካሙን ያህል ሊያገኝበት ይገባል።

ሰዓሊው አንድ የተዋጣለት ስራ ሰርቶ ለማጠናቀቅ ሶስት ወርና ከዚያ በላይ ይወስድበታል። ስዕሉን ለመስራት የወሰደበትን ጊዜ፣ ለስዕል ስራው ያወጣውን ወጪና ስዕሉን ለመስራት የተጠቀመበት እውቀት፣ ሀሳብና ክህሎቱን ተጠቅሞ ለሕዝብ ያቀረበውን ስራ ጥረቱን በሚመጥን መልኩ ገዢ ካላገኘ ሌላ ፈጠራ የታከለበት የነጠረ ስራ ለመስራት አቅምና ሞራል ያሳጣዋል።

ማህበረሰቡ በሚዘጋጁ የስዕል አውደ ርዕዮች ላይ ተሳትፎ የማድረግ ልምዱ ቢዳብር፣ ለሰዓሊ የስዕል ማሳያ ቦታዎች ቢመቻቹለት፣ ሰዓሊው ለስዕል ስራው የሚጠቀምባቸው መሳሪያዎች ቀረጥ ቢቀንስና ለዘርፉ መነቃቃት አሉታዊ ሚና ይጫወታል እንደ ስዕል ባለሙያዎቹ ሀሳብ።

በባለሙያዎቹ ለስዕል ጥበብ ማበብ እንደ መፍትሄ ከተቀመጡት ውስጥ አንዱ ዘርፉ ከቱሪዝም ጋር ማገናኘትን ነው። ቱሪዝም ከስነ ጥበብ ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው። ስዕል ደግሞ የቱሪስት መስህቦችን በማስተዋወቅ ረገድ የላቀ ድርሻ አለው። አገራችን በቱሪዝም ሀብት የታደለች መሆንዋ ደግሞ ለዚህ ምቹ ያደርጋታል። የቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች ላይ የተለያዩ ደረጃቸው የጠበቁ የስዕል ጋለሪዎች ቢመቻቹና አሁን ላይ በስፋት እየተሰሩ ያሉ ጋለሪዎች ለባለሙያው ምቹ ቢሆኑ የተሻለ ውጤት ማግኘት ይቻላል።

በሌላ በኩል ያልታየው ዋንኛ ጉዳይ ስዕል ሰፊ ተደራሽነት ያለው መስክ ስለሆነ ለውጭ ምንዛሬ ማግኛ መንገድም ሊሆን ይችላል። ሰዓሊው ስራዎቹን ቢያቀርብ ለአገር የውጭ ምንዛሬ ምንጭም መሆን ይችላል።

ማህበሩ ከስዕል ስራ በተጨማሪ በተለያዩ ማህበራዊና አገራዊ ጉዳዮች በመሳተፍ አገራዊ ኃላፊነቱም በመወጣት ላይ ይገኛል። በተለይ የስዕል ጥበብን ለሌሎች በማስተማር፣ የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ስልጠናዎችን መስጠትና አገራዊ ጉዳዮች ላይ በንቃት በመሳተፍ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችም በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

የስዕል ጥበብ በራስ እይታ የተለያየን የፈጠራ ስራ በቀለም አድምቆና ልዩ ውበት ሰጥቶ ለማህበረሰቡ ማቅረብ በዚያም የላቀ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማስገኘት ነው። የኢትዮጵያ ሴት ሰዓሊያን ማህበር ልምድና ተስጥኦ ያላቸው ድንቅ ሰዓሊያን ስራዎቻቸው ምቹ ሁኔታ አግኝተው ለገበያ ቢቀርብላቸው ከራሳቸው አልፈው ለአገር ኢኮኖሚ የላቀ ፋይዳ ይኖረዋል።

ሰዓሊ የስዕልና የግራፊክስ ዲዛይን መምህር የሆኑት ወይዘሮ ሩት አድማሱ የሌሎች አገሮች ተሞክሮ ልምድ ቢወሰድ ለዚህ መልክም መሆኑን ያስረዳሉ። ለዚህም የጀርመንዋ ከተማ በርሊን እና የቻይናዋ ቤጂንግ ማሳያ አድርገው ያነሳሉ። ከተሞቹ የጥንት መንደሮቻቸውን ለይተው ለኪነ ጥበብ ባለሙያዎች በመስጠት የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ቅርሶችን እየጠበቁና እየተንከባከቡ የራሳቸውን ስራ እንዲሰሩና የሰሩትን የኪነ ጥበብ ስራ ማሳያ እንዲሆን ይደረጋል።

በዚህም አገራቱ የጥንት መንደሮችና ታሪካዊ ቦታዎች የቱሪስት መዳረሻ እንዲሆን በማልማት ለቱሪዝም ዘርፍ እድገትና ለገቢ ምንጭነት ማዋል እንደቻሉ ይጠቁማሉ። ይህንን ተሞክሮ ወደ አገር ቤት በመመለስ ዘርፉንና ቱሪዝሙን ማጠናከር የሰዓሊያንና የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችን ህልም ማሳካት ችግሮችም መቅረፍ ያስችላል።

አሁን ላይ በከተማችን አዲስ አበባ እየተሰሩ ያሉ የስዕል ማሳያ ጋለሪዎች መዘጋጀታቸው መልካም ቢሆንም የጋለሪዎቹ ባለቤት ተለይቶና ለሰዓሊያን ምቹና ቀላል ተደርገው ቀርበው ለማሳየትና ስራዎቻቸው ከሕዝብ ጋር የሚያገናኙባቸው መድረኮች ቢሆኑ መልካም እንደሆነ አስተያየትዋን ትሰጣለች።

የስዕል ጥበብ አገራዊ ፋይዳው የጎላ ነውና በዘርፉ የተነሱ ዋና ዋና ችግሮችን በመለየት መፍትሄ ሊበጅለት ይገባል። አገርናና ሕዝብን የመቀየር ታሪክናና ማንነትን የማሳየት ትልቅ አቅም ያለው የስዕል ጥበብ ሙያተኞቹን በማገዝ ለፈጠራቸው ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ለእድገቱ ሊሰራ ይገባል መልዕክታችን ነው።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ማሕበራዊ እሴቶችን ስክፉ ጊዜ ማስፈያ

አንተነህ ቸሬ

ወቅታዊው የኑሮ ውድነት የሕብረተሰቡን የመኖር አቅም በእጅጉ እየፈተነው ነው። የዋጋ ንረት በየጊዜው ማሻቀብ እንጂ ዝቅ ማለት አልሆነለትም። የዋጋ ንረቱ እንኳን ቅናሽ ማሳየት ይቅርና ባለበት መቀጠልም አልቻለም። አሁን ያለው የዋጋ ንረት ከእስካሁኑ ሁሉ የከፋ እንደሆነ እየታየ ነው፤ ፈጣን የማስተካከያ እርምጃዎች ካልተወሰዱ ነገም ከዛሬውም የባሰ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም። አልፎ አልፎም ቢሆን በመገናኛ ብዙኃን የሚደመጡ የነዋሪዎች አስተያየቶችና አቤቱታዎች በምሬቶች የተሞሉ አሳዛኝና አሳሳቢ ናቸው።

እጅግ የሚያስገርመው ነገር አገሪቱ ከበቂ በላይ የምታመርታቸው ምርቶች ሳይቀሩ ዋጋቸው ሰማይ መድረሱ ነው። ለአብነት ያህል የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከበቂ በላይ ተመርተው ከማሳ የሚያነሳቸው አጥተው ለብክነት እንደሚዳረጉ አርሶ አደሮች ደጋግመው ሲናገሩ ሰምተናል። በከተሞች ያለው የእነዚህ ምርቶች ዋጋ ግን ‹‹ጆሮ አይስማ›› የሚያሰኝ ነው። አትክልትና ፍራፍሬ ለማሳያነት ያህል ተጠቀሱ እንጂ በሌሎቹ ምርቶች ላይ ያለውም የዋጋ ንረት የሚቀመስ አይደለም።

መንግሥትም ለኑሮ ውድነቱ በየጊዜው ምክንያቶችን ሲያቀርብ ይስተዋላል። አንድ ጊዜ ‹‹በዓለም አቀፍ ደረጃ የታየ የዋጋ ንረት … የነዳጅ ዋጋ መጨመር››፣ ሌላ ጊዜ ‹‹የስግብግብ ነጋዴዎች ድርጊት››፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ‹‹ኢኮኖሚያዊ አሻጥር›› … እያለ ይናገራል። እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ግን ኑሮ ናላውን ላዞረው ሕብረተሰብ ምንም ፋይዳ የላቸውም፤ አይኖራቸውምም። ሁነኛ ሰሚ ጆሮ ባያገኙም ‹‹ኑሮውን አልቻልነውም … የዋጋ ንረቱ መፍትሄ ሊበጅለት ይገባል …›› የሚሉና ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሲደመጡ የቆዩ የዜጎች ድምፆች ዛሬም እያተስተጋቡ ይገኛሉ።

መንግሥት ችግሩን ለመፍታት የወሰደው እርምጃ በቂ አለመሆኑ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ጭምር ተነግሯል። ምክር ቤቱ መጋቢት 27 ቀን 2014 ዓ.ም የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርን የስምንት ወራት የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ባዳመጠበት ወቅት ሚኒስቴሩ የዋጋ ንረትን እያባባሱ ያሉ አካላትን ለይቶ እርምጃ መውሰድ እንዳልቻለ የምክር ቤቱ አባላት ተናግረዋል።

‹‹ … ሁል ጊዜ ‹ሌባ አለ፤ ንግዱን የሚያበላሹት ሌቦችና ሕገ ወጦች ናቸው›› ይባላል። ይህን ንግግር የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትሩን ጨምሮ ከፍተኛ ባለሥልጣት ሲናገሩት ሰምተናል። ይሁን እንጂ ‹ሌቦቹ እነዚህ ናቸው›› ተብለው አልተለዩም፤ አስተማሪ እርምጃ ሲወሰድባቸውም አናይም … ሁልጊዜም ቢሆን ችግር ሲፈጠር የሚጎዳው ሕብረተሰቡ ነው። አሁንም በኑሮ ውድነቱ የሚሰቃየው ሕዝቡ ነው … በየቦታው በተዋቀሩ ሸማቾች ማሕበራት ‹የለም› የሚባለው ስኳርና ዘይት መርካቶ በችርቻሮ ጭምር ሲሸጥ ይታያል። ይህን ማስተካከል ደግሞ የሚኒስቴሩ ስራ ነው። ሥልጣኑ በእጃችሁ ላይ እስካለ ድረስ በሕገ ወጦች ላይ እርምጃ መውሰድ የተሳናችሁ ለምንድን ነው? በንግዱ ሥርዓት ላይ ሕገወጥነትን እያስፋፉና የዋጋ ንረትን እያባባሱ የሚገኙ ግለሰቦችና ተቋማት ላይ ከወሬ በዘለለ በተግባር ልትሰሩ ይገባል›› በማለት በምሬት ተናግረዋል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትሩ አቶ ገብረመስቀል ጫላ በበኩላቸው፤ በመንግሥት ስለተወሰዱ እርምጃዎች ሲጠቅሱ የኑሮ ውድነቱን ያባባሱ 103ሺ 901 ሕገ ወጦች ላይ በየደረጃው እርምጃ መወሰዱን ተናግረዋል። እንግዲህ ከዚህ ቀደም ከሰማነው የ‹‹እርምጃ›› ጋጋታ አንፃር ‹‹ተወሰዱ›› ተብለው በሚኒስትሩ ከተነገሩት እርምጃዎች መካከል ሱቆችን ማሸግ እንዲሁም ሸቀጦችን መውረስ እንደሚገኝበት ግልፅ ነው። መንግሥት ከዚህ ቀደምም ቢሆን ‹‹ሕገ ወጥ የዋጋ ጭማሪ ያደረጉ ሱቆች ታሸጉ›› ብሏል። እንዲህ ዓይነቱ እርምጃስ ዘላቂ መፍትሄ ይሆናል? የአቅርቦት እጥረት በመፍጠር ተጨማሪ የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት እንዲፈጠር አያደርግም? ሱቆችን ማሸግ/መዝጋት አዋጭነቱ ምን ያህል እንደሆነም ሊታሰብበት ይገባል።

ሱቆች ሲታሸጉ የሚታሸገው ምርት/ሸቀጥ በአቅርቦት ላይ የሚፈጥረው የራሱ ጫና ይኖራል። ይህ እርምጃ የአቅርቦት ሰንሰለቱን እንደሚጎዳው ልብ ሊባል ይገባል። እንዲያውም የዋጋ ንረትን ሊያባብስ የሚችልበት እድል አለ። በተጨማሪም ሱቆችን ማሸግ የመጨረሻ አማራጭ ሆነው ከሚጠቀሱ እርምጃዎች መካከል አንዱ በመሆኑ የመጨረሻ አማራጮችን ከመተግበር አስቀድሞ ሌሎች እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል። ነጋዴው እንደሆነ ሱቁ ለተወሰነ ጊዜ ቢታሸግበትም በየጊዜው ዋጋ እየጨመረ የሰበሰበው ትርፍ ሱቁ ተዘግቶ በቆየባቸው ቀናት ያልሸጠውን ያካክስለታል። ሱቆች ሲታሸጉ በሚፈጠረው የአቅርቦት እጥረት የሚጎዳው ሸማቹ ነው።

የዋጋ ንረቱ የፈጠረውን የኑሮ ውድነት ለመቋቋም መንግሥት ኃላፊነት እንዳለበት አካል ከሚወስዳቸው የመፍትሄ እምጃዎች ባሻገር፣ ሕብረተሰቡ ለረጅም ጊዜያት የገነባቸውን ማሕበራዊ እሴቶችና መስተጋብሮችን ለክፉ ጊዜ ማለፊያ መፍትሄነት ሊጠቀምባቸው ይችላል። ከእነዚህ እሴቶች መካከል አንዱ የሕብረተሰቡ የመረዳዳት ባህል ነው። ከወቅታዊ የኑሮ ውድነት አንፃር ይህ የመረዳዳት ባህል እጅግ አስፈላጊ ነው። የተሻለ ገቢና የኑሮ ደረጃ ያላቸው ዜጎች በአነስተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙትን ወገኖቻቸውን እንዲደግፉ ያስፈልጋል።

በአንዳንዶቹ ምርቶችና አገልግሎቶች ላይ የሚታየው የዋጋ ንረት ደግሞ ጠዋትና ከሰዓት በኋላ ሰፊ የዋጋ ልዩነት እስከማሳየት የደረሰ ነው። ኧረ እንዲያውም ሻጭና ገዥ ዋጋ ተስማምተው ገዥ ‹‹ገንዘብ ይዤ ልመለስ›› ብሎ ገንዘቡን ይዞ እስከሚመለስ ድረስ የእቃው ዋጋ ጨምሮ የሚገኝበት አጋጣሚም እንደተፈጠረ ሰምተናል። ትናንት 10 ብር ከፍለን የጠጣነው ሻይ ዛሬ 15 ብር ሆኖ ሲገኝ የዋጋ ንረቱ መንስዔና ሂደት ግራ ያጋባል። እንዲህ ዓይነት የሸቀጦችና የአገልግሎቶች ዋጋ መናር ደግሞ ‹‹የዋጋ ንረት›› ተብሎ ከሚገለፅ ሃሳብ ባሻገር የሕብረተሰቡ የሞራል እሴት እየተሸረሸረ ስለመሄዱም አመላካቾች ናቸው።

‹‹አገር ማለት ሰው ነው›› በሚባለው ብሂል ከተግባባን ሰው የሌለበት ኑሮ ደግሞ ከአገር እንደሚያጎድል እንስማማለን። ስለሆነም ገንዘብ ያለው ሲበላና ሲጠጣ፤ ገንዘብ የሌለው ደግሞ እየተራበና እየተጠማ እንደሆነ ማስታወስ አለበት። ብዙ ወገኖቹ እየተቸገሩ ብቻውን በልቶ ብቻውን እየኖረ ያለ ሰው ‹‹አገር ማለት ሰው ነው›› ብሎ ቢናገር ንግግሩ ከቀልድና ሹፈት የዘለለ ትርጉም አይኖረውም።

ሌላው በዚህ ወቅት መጎልበት ያለበት እሴት እውነትን የመናገርና ለአጥፊዎች ከለላ ያለመስጠት ተግባር ነው። የዋጋ ንረት እንዲባባስ በማድረግ ሕዝቡ የኑሮ ቀንበር ይበልጥ እንዲከብደው ያደረጉ በርካታ ሕገ ወጦች አሉ። እነዚህን ህገ ወጦች ያለምንም ይሉኝታ ማጋለጥና ለሕግ ማቅረብ ይገባል። በግዴለሽነት አልያም በሌላ ምክንያት ለእነዚህ ሕገ ወጦች የሚደረግ ምህረት አገራዊ ጉዳትና ኪሳራ ያስከትላል። ኑሮ እንዲወደድ ያደረጉ ሕገ ወጦችን በቸልታ እየተመለከቱ ‹‹ኑሮ ተወደደ›› ብሎ ማማረር ኢ-ፍትሃዊ ነው። ስለሆነም እውነትን መናገርና ሌባን አለመደበቅ ይገባል። ስለሆነም የመጨረሻው ውሳኔያቸችን መሆን ያለበት ማሕበራዊ መስተጋብሮቻችን ማጠናከር ላይ መሥራት ነው። መልካም እሴቶችን ለክፉ ጊዜ ማለፊያነት መጠቀምም ያስፈልጋል። ሰላም!

# ዓለም አቀፍ

## ተጨማሪ ዘጠኝ የኮቪድ-19 ምልክቶች ይፋ ሆኑ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ በኮሮና ቫይረስ የተያዘ ሰው የሚያሳያቸው ምልክቶች ላይ ተጨማሪ ዘጠኝ ምልክቶች ተጨመሩ። እነዚህ ምልክቶች ከዚህ በፊት የነበሩትን የሚያሰፉና ተጨማሪ ነገሮችን ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ ናቸው።

የዩኬ የጤና ደህንነት ኤጀንሲ ባዘጋጀው አዲስ መመሪያ ውስጥ የጉሮሮ ህመም፣ የጡንቻ ህመም እና ‘ተቅማጥ’ ከተካተቱት አዳዲስ የኮሮረና ቫይረስ ምልክቶች መካከል ናቸው።

ይህ መመሪያ የወጣው ወረርሽኙ ከተከሰተ ሁለት ዓመታት ካለፈው በኋላ ሲሆን እንግሊዝ ውስጥ ደግሞ ይደረግ የነበረው የነጻ ምርመራ ከተቋረጠ ከቀናት በኋላ ነው። ነገር ግን የዩኬ የጤና ደህንነት ኤጀንሲ ባስተላለፈው የማስጠንቀቂያ መልእክት አዳዲሶቹ ምልክቶች ከጉንፋን ብዙም ያልተለዩ መሆናቸውን አሳስቧል።

ከዚህ በፊት የሚታወቁት የኮቪድ-19 ምልክቶች ትኩሳት፣ የማያቆም ሳል፣ የሽታ እና የመቅመስ ስሜቶቻችን መጥፋት እንዲሁም ድካም የሚጠቀሱ ናቸው። ወረርሽኙ ባጋጠመበት የመጀመሪያዎቹ ወራት ወቅት የስርጭቱን አካሄድ መረዳትና ምልክቶቹን መለየት ከባድ የነበረ ሲሆን አሁን ላይ ግን ዓለም ስለቫይረሱ ማወቅ ከሚገባው አብዛኛውን ነገር አውቋል። የዓለም ጤና ድርጅትም ቢሆን ከረጅም ጊዜ በፊት ምልክቶች ብሎ ያስቀመጣቸው ነገሮች በርካታ ናቸው።

ነገር ግን ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ ትክክለኛ ምልክቶቹ የትኞቹ ናቸው እንዲሁም ምን አይነት ምልክቶችን የሚያሳይ ሰው ነው ምርመራ ማድረግ ያለበት የሚሉት ጥያቄዎች መከራከሪያ ሆነው ቆይተዋል።

ለምሳሌ ራስ ምታት የኮሮና ቫይረስ ምልክት ተደርጎ ሊቆጠር የሚችል ቢሆንም ራሱን ያመመው ሰው በሙሉ ግን የኮሮና ቫይረስ ምርመራ ማድረግ አይችልም። ምክንያቱም ራስ ምታት ከኮሮና ቫይረስ ውጪ በበርካታ ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል።

ትኩሳት፣ ሳል፣ ማሽተት ማቆም አልያም ጣእም ማጣት በርካቶችን የማያከራክሩ ምልክቶች ሲሆኑ አሁን ላይ ደግሞ ዘጠኝ ተጨማሪ ምልክቶች እንዲጨመሩ ተደርጓል።

እነዚህም ትንፋሽ ማጠር፣ ድካም፣ የሰውነት መላሸቅ፣ ራስ ምታት፣ የጉሮሮ ሕመም፣ ከአፍንጫ የሚወጣ ፈሳሽ [ንፍጥ]፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ፣ ተቅማጥ እና አጠቃላይ የጤንነት ስሜት ማጣት ናቸው።

ዩኬ ውስጥ በኮቪድ የተያዙ ሰዎች ቁጥር 4.9 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን መንግሥት በነጻ ሲያከናውነው የነበረው ምርመራም ባሳለፍነው ሳምንት ተጠናቋል። የዩኬ የጤና ደህንነት ኤጀንሲ እንደሚለው ሰዎች አሁንም ቢሆን በተቻላቸው መጠን ከቤታቸው ላለመውጣት መሞከርና ከሌሎች ሰዎች ጋር



ያላቸውንም ንክኪ መቀነስ አለባቸው። በተለይ ደግሞ እነዚህን ምልክቶች የሚያሳይ ሰው ምርመራ ማድረግና እራሱን ከሰዎች መለየት እንዳለበት ኤጀንሲው አሳስቧል።

## አልሻባብ የሶማሊያን ከፍተኛ ባለሥልጣናት ለመግደል እያሴረ መሆኑ ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አልሻባብ የሶማሊያን ፕሬዚዳንት እና ጠቅላይ ሚኒስትር ለመግደል እያሴረ መሆኑን የአገሪቱ ደህንነት አስታወቀ። የሽብር ቡድኑ ለመግደል ያቀደው ፕሬዚዳንት መሀመድ ፋርማጆን እና ጠቅላይ ሚኒስትር መሀመድ ሮብለን ነው።

በሶማሊያ እስላማዊ መንግሥት ለመመስረት በሚል የሚንቀሳቀሰው አልሻባብ የሽብር ቡድን የአገሪቱን ከፍተኛ ባለሥልጣናት የመግደል እቅድ እንዳለው ተገልጿል። የሶማሊያ ደህንነት በትዊተር ገጹ ባወጣው የማስጠንቀቂያ መልዕክቱ “አልሻባብ ፕሬዚዳንት መሀመድ ፋርማጆን እና ጠቅላይ ሚኒስትር መሀመድ ሮብለን የመግደል እቅድ አውጥቷል” ብሏል።

መሀመድ ማሂር የተሰኘው የአልሻባብ የሽብር ቡድን ከፍተኛ አመራር ፕሬዚዳንቱን እና ጠቅላይ ሚኒስትሩን



ለመግደል የቤት ስራ ወስዶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑንም የአገሪቱ የደህንነት ተቋም አስታውቋል። የሽብር ቡድኑ የአገሪቱን ከፍተኛ ባለሥልጣናት ለመግደል ያቀደው በሶማሊያ እስላማዊ መንግሥት የመመስረት እቅድ ስላለው መሆኑን ድርጅቱ ገልጿል።

ሶማሊያ የእንደራሴዎች ምክር ቤት እና ፕሬዚደንታዊ ምርጫ ለማካሄድ ባሳለፍነው ዓመት እቅድ የነበራት ቢሆንም በኮሮና ቫይረስ ምክንያት አራዝማለች። ምርጫው በመራዘሙ ምክንያትም በአገሪቱ ለተፈጠረው አለመረጋጋት ዋነኛው ምክንያት ሲሆን በፕሬዚዳንቱ እና በጠቅላይ ሚኒስትሩ መካከል ግጭት እንዲፈጠርም አድርጓል።

አሜሪካም የሶማሊያ መሪዎች ምርጫውን አራዝማችኋል በሚል በአገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ላይ የጉዞ እቀባን ጨምሮ ሌሎች ማዕቀቦችን ጥላለች። አልሻባብ የተሰኘው የሽብር ቡድን በሶማሊያ እና ጎረቤት አገራት ዜጎች እና ተቋማት ላይ በርካታ ጉዳቶችን በማድረስ ላይ ሲሆን ባሳለፍነው ሳምንት በሞቃዲሾ ባደረሰው የሽብር አደጋ የ48 ሰዎች ሕይወት ማለፉ ይታወሳል።

በሶማሊያ ጠንካራ የመንግሥት የደህንነት ተቋማት እንዲመሰረቱ በሚል በአፍሪካ ሕብረት አስተባባሪነት ኢትዮጵያን ጨምሮ ከምስራቅ አፍሪካ አገራት የተውጣጡ ሰላም አስከባሪዎች በመቋዲሾ መሰማራታቸው ይታወሳል።

# ስፖርት





## ስፖርት ለሰላምና ለልማት በዓለም አቀፉ የስፖርት ቀን

**ብርሃን ፈይሳ**

ከማዝናናትና ጤናን ከመጠበቅ ባለፈ በርካታ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎች ያለው ስፖርት፤ ከሰው ልጆች መሰረታዊ ጉዳዮች መካከል አንዱ ሆኗል። ሰላምን እና ወዳጅነትን የሚሰብከው ዘርፉ ዓለምን የመለወጥ አቅም ያለው ሲሆን፤ ይህንንም በተለያዩ ሁኔታዎች አስመስክሯል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ይህንኑ ምክንያት በማድረግ እአአ ከ2014 ጀምሮ በየዓመቱ መጋቢት 28 ዓለም አቀፍ የስፖርት ቀን በሚል እንዲከበር ወስኗል። በዚህም መሰረት በየዓመቱ ስፖርት ለሰላምና ለልማት እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ ይዘከራል።

ስፖርት ለማሕበራዊ ለውጥ፣ ልማት እና ሰላም በሚል በሚከበረው በዚህ ዕለትም በስፖርት ከሚታወቁት ቢጫ እና ቀይ ካርዶች ባሻገር ነጭ ካርድን በማሳየት ስፖርት ለሰላም ያለውን አስተዋጽኦ ያመላክታል። በመላው ዓለም የሚከበረው ይህ ቀን በዓለም አቀፍ የስፖርት ማሕበራትም ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠዋል። ዓለም አቀፉ የኦሊምፒክ ኮሚቴ ስፖርትና ኦሊምፒክ፤ ምን ያህል ሕዝብን ከሕዝብ እንደሚያቀራርብ ያሳያል።

የስፖርት ለልማት እና ለሰላም ቀንም በዓለም ለዘጠነኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ ተከብሯል። በውይይቱ ላይም የክልል ባህልና ስፖርት ቢሮ ኃላፊዎች፣ የተጠሪ ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች፣ የአገር አቀፍ ስፖርት ማሕበራት ፕሬዚዳንቶች፣ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተውጣጡ የስፖርት ባለሙያዎች፣ በስፖርት ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶችና የስፖርት ባለሙያዎች ተሳታፊ ሆነዋል።

በመርሃ ግብሩ ላይ የተገኙት የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፤ ስፖርት ከግለሰብ ጀምሮ ማሕበረሰብ እና አገራትን የያስተሳስር ቁልፍ የግንኙነት መሳሪያ እንደሆነ ጠቁመዋል። ስፖርት የዓለምን ከፍተኛ ኢኮኖሚ የሚያንቀሳቅስ የልማቱ እምቅ አቅም ነው። በአሁኑ ጊዜ ዓለም ከቀዝቃዛ ጦርነት እንዲሁም በግጭቶችና ቀውሶች ውስጥ የምትገኝ ቢሆንም፤ ስፖርት በግጭት ውስጥ ያለፈውን ሕብረተሰብ ሥነልቦና አክሞ በማረጋጋት ተስፋን ያለመልማል። በግጭት ቀጠና የሚገኝ ማሕበረሰብንም ከስጋት ወጥቶ ማሕበራዊ ግንኙነቱን እንዲያጠናክር አቅም የመፍጠር ኃይል እንዳለው ገልጸዋል።

ኢትዮጵያም ከገባችበት አስቸጋሪ የግጭት ሁኔታ ወጥታ ሁለንተናዊና ዘላቂ እርቀ ሰላም ለማረጋገጥ ስፖርት የተለየ ድርሻ እንዳለውም ሚኒስትር ዴኤታው ጨምረው ጠቁመዋል። ለዚህ ጉዞ ውጤታማነትም በርትቶ መስራት ተገቢ ነው። ስፖርት በራሱ ልማት ሲሆን፤ ለሁለንተናዊ ልማት በር የሚከፍት ድልድይ በመሆንም ያገለግላል። በመሆኑም በቅንጅት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

## ኢትዮጵያ የሴካፋ ማጣሪያ ውድድርን ታስተናግዳለች

**ብርሃን ፈይሳ**

ኢትዮጵያ ከ17ዓመት በታች የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎችን ታስተናግዳለች። የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ እግር ኳስ ማሕበር (ሴካፋ) የዓመቱን የውድድር መርሃ ግብሮችና አስተናጋጅ አገራትን አሳውቋል።

በበርካታ የምስራቅና ጥቂት የመካከለኛው አፍሪካ አገራት እግር ኳስ ፌዴሬሽኖች የተዋቀረው የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ እግር ኳስ ማሕበር (ሴካፋ) ከአህጉሩ የእግር ኳስ ማሕበራት መካከል አንጋፋው ነው። እአአ 1973 የተመሰረተው ማሕበሩ ኢትዮጵያን ጨምሮ 12 አገራትን በአባልነት አቅፏል። ማሕበሩ በርካታ ቀጠናዊ ውድድሮችን በስሩ የሚያካሂድ ሲሆን፤ ከ17 ዓመት በታች የአፍሪካ ዋንጫ ተሳታፊ የሚሆነውን ቡድን ለመለየትም የማጣሪያ ጨዋታዎችን ያከናውናል። የዚህን ዓመት የማጣሪያ ውድድርም በኢትዮጵያ አዘጋጅነት እንደሚካሄድ ማሕበሩ በድረገጹ አስታውቋል።

ማሕበሩ የዓመቱን የውድድር መርሃ ግብር እና አዘጋጅ አገራትን ያስታወቀ ሲሆን፤ በተያዘው ዓመት ሰባት ውድድሮች ይደረጋሉ። ውድድሮቹን ለማዘጋጀት አገራቱ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረትም የስራ አስፈጻሚው ውሳኔ መስጠቱንም የማሕበሩ ዳይሬክተር አውካ ጌቼዮ አስታውቀዋል። በዚህም መሰረት ኡጋንዳ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚደረገውን የሴካፋ ሴቶች ዋንጫ በቀጣዩ የፈረንጆች ወር የመጀመሪያዎቹ ቀናት ታስተናግዳለች። በተጨማሪም የዞኑን የፓን አፍሪካ የትምህርት ቤቶች ውድድርም በአገሯ ታካሂዳለች።

ለረጅም ጊዜያት የትኛውንም የሴካፋ ውድድር ሳታስተናግድ የቆየችው ሱዳን ደግሞ የከ20 ዓመት በታች የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ እንደምታስተናግድ ታውቋል። ሌላኛዋ የማሕበሩ አባል ታንዛኒያ በበኩሏ የካፍ ሴቶች ቻምፒዮንስ ሊግ ማጣሪያን፣ ከ23 ዓመት በታች የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያን እንዲሁም በዚሁ የእድሜ ክልል የካጋሜ ዋንጫን ታስናዳለች።

ማሕበሩ ውድድሮቹ የሚካሄዱባቸውን ጊዜያት በቅርቡ የሚያስታውቅ መሆኑንም በዳይሬክተሩ በኩል አመላክቷል።


## የጨረታ ማስታወቂያ

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ጤና ጽ/ቤት የቂርቆስ ጤና ጣቢያ ለ2014 ዓ.ም ለተቋሙ የሚያስፈልጉ፡- መድኃኒቶችን እና ሪኤጀንቶች፣ የደንብ ልብሶች፣ የተለያዩ ህትመቶች፣የደንብ ልብስ ስፌቶችን፣የጽዳት ዕቃዎችን፣የጥገና ዕቃዎች፣የጄኔሬተር ሰርቪስ/ጥገና፣የሕክምና መሣሪያዎች ፣ የግድግዳ ቀለም መቀባት፣ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል ፡፡

ስለዚህ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት የሚችል ማንኛውም ሕጋዊ የንግድ ድርጅት ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ዕለት አንስቶ ባሉት 10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በጤና ጣቢያው ቅጥር ግቢ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 206 በሥራ ሰዓት በመቅረብ የማይመለስ ብር 100.00 ( አንድ መቶ ብር ብቻ) በመክፈል እና የጨረታውን ዝርዝር የያዘ ሰነድ በመውሰድ መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እየገለጽን ጨረታው በ10ኛው የሥራ ቀን ከቀኑ በ11፡30 ተዘግቶ በ11ኛው የሥራ ቀን ከጠዋቱ በ4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡

**ተጫራቾች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶች፡-**

1. በግብር ከፋይነት የተመዘገቡ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፤
2. የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ማቅረብ የሚችሉ፣ ለጨረታ ማስከበሪያ መያዣ የሚወዳደሩበትን ጠቅላላ ዋጋ 2 ፐርሰንት በጤና ጣቢያው ስም በተዘጋጀ ሲፒኦ ማስያዝ ያለባቸው ሲሆን፤ እንዲሁም ለጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማት አስፈላጊውን የትብብር ደብዳቤ ለማወዳደር በሚከፈተው ፖስታ ማለትም በኮፒው ውስጥ በማያያዝ ማቅረብ አለባቸው፤
3. በተጫራቾች መመሪያ መሠረት በአቅራቢዎች ሊስት ላይ በድረ-ገጽ የተመዘገቡ መሆን አለባቸው፡፡
4. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ዋጋ ዝርዝር ጤና ጣቢያው ባቀረበው የዋጋ ሰንጠረዥ ላይ በመሙላት እና በእያንዳንዱ ገጽ ላይ የድርጅቱን ማህተም በማድረግ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒውን በሰም በታሸገ ፖስታ ማቅረብ አለባቸው፤
5. ናሙና ለሚያስፈልጋቸው ቁሳቁሶች ሁሉም ተጫራቾች ናሙና ከጨረታው ሰነድ ጋር በጋራ ማቅረብ አለባቸው፤
6. ማንኛውም ተጫራች መወዳደር የሚችለው ከንግድ ፈቃዱ ጋር ተያያዥነት ባላቸው አቅርቦቶች/ አገልግሎቶች ላይ ብቻ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

ጤና ጣቢያው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ የሚቀርቡት ዋጋዎች ተጨማሪ እሴት ታክስን/ ተርን ኦቨር ታክስን ያካተቱ መሆን አለባቸው፡፡

አድራሻ ፡- ከሜክሲኮ ወደ ቄራ በሚወስደው መንገድ ከገነት ሆቴል ወደ ሽመልስ ሀብቴ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በሚወስደው መንገድ 200ሜትር ገባ ብሎ ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር፡- 0115536456/0115156192 በመደወል መጠየቅ የሚቻል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ**
**የቂርቆስ ጤና ጣቢያ**

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም፡- ሞላ ብርሃኑ አንቺቢ<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ 03 የቤት ቁጥር አዲስ ,ን/ስ/ላፍቶ , አዲስ አበባ , ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር፡- LTM/11859/2014<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 17/06/2014 E.C. | | |
| 3 | ምልክት፡- | 4 | የምልክቱ መግለጫ፡-የቃልና ምስል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት፡- ጥቁር እና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ ጠቅላላ ሆስፒታል (GENERAL HOSPITAL) |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 44 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች፡- | | |
| | የአጠቃላይ ሆስፒታል አገልግሎት(ምድብ 44) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል። ስለሆነም፣ ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ፣ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን። ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ሕግ ይጠየቃል።

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**
**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-209- 29/7/2014 (7/4/2022)**

## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት አስቴር ታደሰ እና በፍ/ባለዕዳ እነ ሕይወት ተስፋዬ ሽበሺ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 265330 በ23/2/2013 ዓ.ም እና መ/ቁ 228416 ሀምሌ 30 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 347 የሚገኝ የሆነው ቤት ካርታ ቁጥር 4115011642/50 የሆነ የቤት ስፋት በሰነድ 413 ካ/ሜ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 161,792.70 (አንድ መቶ ስልሳ አንድ ሺ ሰባት መቶ ዘጠና ሁለት ከሰባ ሳንቲም) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሰኔ 6 ቀን 2014 ዓ.ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ4፡30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡ የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሦስት የሥራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን፤ እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬት የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢፌዴሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ**
**አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**